«በሥራችን ስኬታማ ለመሆን ራዕያችን ላይ ሁልጊዜ ትኩረት ማድረግ አለብን»

ወ/ት ሳምራዊት ፍቅሩ
የራይድ መስራችና ሥራ አስፈፃሚ



ገጽ 6

ኑሮ - ከቤተመንግሥት እስከ ጎዳና



ገጽ 16


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

81ኛ ዓመት ቁጥር 267 ግንቦት 27 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




## በሐምሌ ወር የሚደረገው የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያ የኑሮ ውድነቱን እንዳያባብስ ቁጥጥር እንደሚደረግ ተገለጸ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በሐምሌ ወር በሚደረገው የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያ ሰበብ በማድረግ የኑሮ ውድነቱ እንዳይባባስ ቁጥጥር እንደሚደረግ የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ገለጸ። የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያው ለኑሮ ውድነት ሰበብ ሊሆን እንደማይችል ተገልጿል።

በነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን የነዳጅ ውጤቶች ግብይት ስታንዳርድ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ለሜሳ ቱሉ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሐምሌ ወር የሚደረገውን የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያ ሰበብ በማድረግ የኑሮ ውድነቱ እንዳይባባስ አስፈላጊው ቁጥጥር ይደረጋል።

ነዳጅ በዋጋ ላይ ያለው ተጽዕኖ በራሱ ልክና ሚዛን መታየት አለበት ያሉት አቶ ለሜሳ፤ ትክክለኛና ሳይንሳዊ ተፅዕኖው ምን ያህል እንደሆነ በፕላንና ልማት ኮሚሽን በተደረገው ጥናት ውስን ተጽዕኖ አለው፡፡ ነገር ግን እንደ ሰበብ በመውሰድ በተለያዩ የፍጆታ ዕቃዎች ላይ የሚደረገው ጭማሪ ልኩን ያለፈነውና ሊታረቅ እንደሚገባ አሳስበዋል።

እንደ አቶ ለሜሳ ገለጻ፤ ነዳጅ ላይ አምስት ብር ሲጨመር በሰበቡ ነጋዴው 15 ብር የሚጨምርበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ በመሆኑም በነዳጅ ዋጋ ማስተካከያ ሰበብ የኑሮ ውድነቱ እንዳይባባስ 12 የሚደርሱ ባለድርሻ አካላት ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡ ለውጤታማነቱ በየደረጃው ያሉ የአስተዳደር፣ የፍትህና የጸጥታ አካላት በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል።

የነዳጅ ዋጋ መሸጫ ዋጋው ማስተካከያ የዓለም የነዳጅ ዋጋን ያገናዘበ በማድረግ በነዳጅ ግብይት ላይ የሚፈጸመው ህገ ወጥነትና ብክነትን ማስቀረት ዓላማ

«በሐምሌ ወር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ጎመጁ ኦይል ኢትዮጵያ
gomeju
OIL ETHIOPIA





the prime powerhouse
+251-1 1 6501010
+251-1 1 6501717
www.gomejuoil.com





## የተምች ወረርሽኝ በአራት ክልሎች ላይ መከሰቱ ተገለጸ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- የተምች ወረርሽ በአራት ክልሎች ላይ መከሰቱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በጋምቤላ ክልል ብቻ በአምስት ወረዳዎች በሰባት ሺህ 446 ሄክታር መሬት ላይ ተከሰቷል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር የእፅዋት ጥበቃ ዳይሬክተር አቶ በላይነህ ንጉሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ አሁን ላይ በኢትዮጵያ አራት ክልሎች ላይ በ 11 ሺህ 229 ሄክታር መሬት ላይ የተምች ወረርሽኝ ተከስቷል፡፡

ተምች በኢትዮጵያ ሲከሰት የመጀመሪያው እንዳልሆነ የተናገሩት አቶ በላይነህ፣ የዘንድሮው ለየት የሚያደርገው

«የተምች ወረርሽኝ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## የሚኒስትሮች ምክር ቤት የ2015 የፌዴራል መንግሥት ረቂቅ በጀት 786 ነጥብ 61 ቢሊዮን ብር እንዲሆን ውሳኔ አሳለፈ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የሚኒስትሮች ምክር ቤት የ2015 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ረቂቅ በጀት 786 ነጥብ 61 ቢሊዮን ብር እንዲሆን ውሳኔ አሳለፈ።

«የሚኒስትሮች ምክር ቤት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565




## ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለተለያዩ ግለሰቦች ሹመት ሰጡ

- አምባሳደር ሬድዋን የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ሚኒስትር ሆነዋል

ገጽ 4

ዜና

# የሰብዓዊ መብት ትምህርት ለልጆች መሰጠቱ ለመብት ተቆርቋሪ ሆነው እንዲያድጉ ያግዛል

- ኢሰመኮ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የሰብዓዊ መብት ትምህርት በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ መካተቱ ልጆች ለሰብዓዊ መብት መከበር ተቆርቋሪ ሆነው እንዲያድጉ ያግዛል ሲሉ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) አስታወቀ፡፡

የኢሰመኮ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ቀረጻ አስተባባሪ ዶክተር መቅደስ ታደለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሰብዓዊ መብት ትምህርት በሥርዓተ ትርምህርት ውስጥ እንዲካተት በመደረጉ በቀጣይ ለተማሪዎች ይሰጣል። ይህም ልጆች ስለሰብዓዊ መብቶች ጥልቅ ዕውቀትና ክህሎት ኖሯቸው እንዲያድጉ ይጠቅማል።

ኢሰመኮ የሰብዓዊ ትምህርት በዜጎች ዘንድ እንዲሰርጽ ማድረግ አንዱ ተግባሩ ነው ያሉት ዶክተር መቅደስ፤ የሰብዓዊ መብት ጉዳይ በሥርዓተ ትምህርት ተካቶ መሰጠቱም የጉዳዩን ምንነትና ትውልዱ ከህጻንነቱ ጀምሮ እንዲረዳና እንዲጠብቀው ያደርጋል ብለዋል።

ስለጉዳዩ በቂ ዕውቀት ያለው ትውልድ ደግሞ ለሰብዓዊ መብት መከበር ተቆርቋሪ የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር መቅደስ ገለጻ፤ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ከግብረ ገብ ትምህርት ጋር ከሰባት እስከ 10ኛ ክፍል ላሉት ተማሪዎች ደግሞ ከሥነዜጋ ትምህርት ጋር በጣምራ የሰብዓዊ መብት ትምህርት ተካቶ እንዲሰጥ ለማድረግ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በቅርበት እየተሠራ ይገኛል።

በተለይ በመጽሐፍ ዝግጅቱ ላይ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በቅርበት እየተሠራ መሆኑን አስታውሰው፤ ሥርዓተ ትምህርቱ የልጆችን ዕድሜ በሚመጥንና ከልጆቹ የቀን ተቀን ሕይወት ጋር የተገናኙ እንዲሆኑ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

ልጅነት የእያንዳንዱ ግለሰብ የወደፊት ማንነታቸው የሚቀረጽበትና ጊዜ ነው ያሉት አስተባባሪዋ፤ በዚህ ወቅት የሰብዓዊ ትምህርት መሰጠቱ ተማሪዎች ስለዕኩልነት፣ ስለሰው ልጅ ክብር፣ ስለመቻቻል፣ ስለሰላምና አንድነት በተገቢው መንገድ እንዲያውቁ ይጠቅማል ብለዋል፡፡

ሰብዓዊ መብትን ማክበርና ማስከበር በዋናነት በመንግሥት ላይ የተጣለ ኃላፊነት ቢሆንም ሁሉም ዜጋ ህግን አክብሮ በመንቀሳቀስና የዜጎች ሰብዓዊ መብት እንዲከበር የመታገል ኃላፊነታቸው አለበት ያሉት ዶክተር መቅደስ፤ ኮሚሽኑም በሰብዓዊ መብት ጉዳዮች ላይ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማደሳደግ የየተለያየ ጥረቶችን እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

የዚህ ሥራ አንዱ አካል የሆነ የምስለ ችሎት ውድድር በተማሪዎች መካከል መካሄዱን ጠቁመው፤ ውድድሩ በሕግና ሰብዓዊ መብቶች ባለሙያዎች የሚዳኝ ከሞላ ጎደል የመደበኛ ፍርድ ቤት ክርክር ሥርዓትን የሚከተል አስተማሪ የውድድር አይነት ነው ብለዋል።

ተወዳዳሪ ተማሪዎች ተገቢው ስልጠና ከተሰጣቸው በኋላ ምናባዊ በሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጉዳይ ተመስርተው አመልካችና ተጠሪን በመወከል የጽሑፍና የቃል ክርክር ማድረጋቸውን ጠቁመዋል።

ተወዳዳሪ ተማሪዎች በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ ጥናት እንዲያደርጉና በቂ ዕውቀት እንዲያገኙ ጥሩ አጋጣሚ የፈጠረ እንደነበር ተገልጿል።

የዘንድሮው የሰብዓዊ መብት የተማሪዎች ውድድር ምናባዊ ጉዳይም ትኩረቱን አሳሳቢ እየሆነ በመጣው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችና አካል ጉዳተኞች መብቶች ላይ ያደረገ እንደነበር ኢሰመኮ አሳውቋል።

# የሀገርን ዕድገት በሚገባው ልክ ለማፋጠን የከተማ መሬት አያያዝ ሥርዓትን ማዘመን ይገባል

- የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የሀገርን ሁለንተናዊ ዕድገት በሚገባው ልክ ለማፋጠን የከተማ መሬት አያያዝ ሥርዓትን ማዘመን እንደሚገባ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ከሁለት መቶ በላይ ለሆኑ ለፌዴራልና ለክልል የከተማ መሬትና ፕላን ዘርፍ አመራርና ባለሙያዎች የሥልጠናና ምዘና መርሃ ግብር አስጀምረዋል።

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ፋንታ ደጀን በወቅቱ እንደገለጹት፤ የከተማ መሬት ሀብታችን ከብልሹ አሰራር በጸዳ ሁኔታ ለማልማትና የነዋሪዎችን የፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋጋጥ የዘርፉን የመረጃ አያያዝን ማዘመን ያስፈልጋል፡፡


ወቅቱ የሚጠይቀውን ሥራ በማከናወን የሀገርን ሁለንተናዊ ዕድገት ወደ ተሻለ ደረጃ ማሸጋገርና የከተማ መሬት መረጃ አያያዝ ሥርዓትን ግልጽነት እንዲኖረው ማድረግ ይገባል ብለዋል፡፡

የመሬት አስተዳደር ሥርዓትን ለማዘመን በዘርፉ ላሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ለ45 ቀን የሚቆይ ሥልጠና ይሰጣል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሰልጣኞች በቆይታቸው በቂ ክህሎት እንዲያገኙና በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን እንዲፈቱ ጥረት ይደረጋል ሲሉ አስታውቀዋል።

ውስን የሆነውን የመሬት ሀብታችንን በሚፈለገው ልክ ለመጠቀም ከብልሹ አሰራር የጸዱና በሙያቸው የበቁ ባለሙያዎችን ማፍራት ያስፈልጋል። ይህ ጥረትም ዘርፉን ለማሻሻል ትልቅ ሚና ይጫወታል ብለዋል።


አቶ ፋንታ ደጀን

ፎቶ - በናሆም አየለ


ዶክተር ዋቅጋሪ ነጋሪ

በሀገር ደረጃ እየተተገበረ የሚገኘው የከተማ መሬትና ማናጅመንት ስራ በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ከመቅረፍ አኳያ የማይተካ ሚና አለው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በዚህ ረገድ አስፈላጊው የምዝገባ፣ የቁጥጥርና የዋስትና አሰጣጥ ስራችንን ማጠናከር ይገባናል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በከተማም ሆነ በገጠር የመሬት ጉዳይ የዋስትና ጥያቄ የሚነሳበት በመሆኑ ዋስትናን በማረጋገጥ በአግባቡ መመዝገብ በዘርፉ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ወሳኝነት አለው።

በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሥልጠናና ማማከር ዘርፍ ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ዋቅጋሪ ነጋሪ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በከተማ መሬትና ፕላን ዘርፍ የሚሰጠው ሥልጠናው እንዲቀርብ ዋነኛ ምክንያት የሆነው በከተሞች ላይ በተካሄደው ጥናት መሰረት ዘርፉ ብዙ ችግር እንዳለበት በመረጋገጡ ነው።

የአንድ ከተማ ዘመናዊነት መገለጫ የመሬት አያያዝ ሥርዓቱ በመሆኑ በመሬት አያያዝ ረገድ የሚጎሉትን ችግሮች በደንብ ለይቶ ማውጣት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ በዘርፉ ላሉ አመራሮች ሥልጠና መስጠት የመሰረተ ልማትን አጠቃቀም ለማሻሻል ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ እንደሚያግዝ ገልጸዋል፡፡

እንደ ዶክተር ዋቅጋሪ ገለጻ፤ በመሬት ጉዳይ አዲስ አበባ የብዙ ዓለምአቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ በመሆኗ በዘርፉ የሚታይባትን የመሬት አያያዝ ሥርዓት በማዘመን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንድትሆን ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

አዲስ አበባን ልክ እንደሌሎች ዓለም አቀፋዊ ይዘት እንዳላቸው ምርጥ ከተሞች በከተማ መሬትና ፕላን ዘርፉ ተወዳዳሪ ለማድረግ በዘርፉ ያሉ አመራሮችንና ባለሙያዎችን በብዛት ማሰልጠን ያስፈልጋል ብለዋል።


ዶክተር ዲማ ነገዎ

# አገራዊ ውይይቱ አገሪቱ በዚህ ወቅት ለሚገጥማት መሰናክሎች ጭምር መፍትሄ እንደሚሆን ተገለጸ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች እንዲሁም አገራዊ ውይይቶች በዚህ ወቅት ለሚስተዋሉ ችግሮችና መሰናክሎች ጭምር መፍትሄ ይዘው ሊመጡ እንደሚችሉ ተገለፀ።

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ ዶክተር ዲማ ነገዎ በተለይ ለኢትዮጵ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት አገራዊ ውይይት በኢትዮጵያ መደረግ የነበረበት ከሃያና ሰላሳ አመታት ቀደም ብሎ ቢሆንም አሁን መደረጉ በበጎ የሚታይ ነው።

አገራዊ ውይይት መደረግ የነበረበት ከዚህ በፊት መሆን እንዳለበትና የዘገየ ጉዳይ ሆኖ እያለ አሁን መደረግ የለበትም የሚለው ሃሳብ ትክክል ካለመሆኑም ባሻገር በአገሪቱ ሰላም እንዳይመጣና ከዚህም በላይ መግባባት እንዳይፈጠር የሚያደርግ መሆኑን አንስተዋል።

ንግግሩና ውይይቱ ለነገ የሚባል ጉዳይ ባለመሆኑ በችግሮቻችን ምክንያት የበርካታ ሰዎች ህይወትና ንብረት እንዳይጠፋ በወቅቱ መደረግ እንዳለበት አስታውቀዋል።

ከዚህም ባሻገር አሁን በአገሪቱ ውስጥ የሚስተዋሉ ችግሮችን ይበልጥ በማወሳሰብ ነፍጥ አንግበው በዱር በገደሉ በመግባት የሚፋለሙ ወገኖች በመሳርያ ኃይል ውጤት እንደማይመጣ አውቀው ወደ ውይይቱ ሊመጡ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ከመንግስት ጋር የሚፋለሙ አካላት ወደ ውይይት ለመምጣት መከናወን ያለባቸው ተግባራት እንዳለ የተናገሩት የፖለቲካ ምሁሩ፣ አገራዊ ውይይቱ ለነዚህ አካላት አሁንም ዝግ ሊሆን እንደማይገባ አውስተዋል።

አንድ አንድ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ፖለቲከኞች አገራዊ ውይይቱ አሁን መከናወን እንደማይችል መስበክና መንግስት ውይይቱ እንዲካሄድ የሚያደርገውን ጥረት ለማስተጓጎል የሚያደርጉት ጥረት አግባብ እዳልሆነ ጠቁመዋል። ይልቁንስ ውይይቱ እንዲደረግ ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸውና በሚችሉት አግባብ እንደየ አቅማቸው ማገዝ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

በአገራዊ ጉዳዮቻችን ላይ የተለያዩ እሳቤዎችና ልነቶች እንዳሉ የተናገሩት ዶክተር ዲማ፣ የሚስተዋሉ ልዩነቶች ላይ አብዛኛው ማህበረሰብ የሚስማማበትን እንዲሁም የሚግባባበት ሀሳብ ለማመንጨት የሚያስችል መደላድል የሚፈጥር መሆኑን ተናግረዋል።

የአገራዊ ውይይቱ ዋነኛ አላማም አገር ወደፊት የምትቀጥልበትና ችግሮቻችንን በምን አግባብ መፍታት አለብን የሚሉ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ፤ ወሳኝና አንኳር የሆኑ አገራዊ ጉዳዮቻችንን ነቅሶ በማውጣት በዚህ ምክንያት የሚነሱ አለመግባባቶች የሚቀረፉበት መንገድ መሆኑን አንስተዋል።

በአገሪቱ ለዘመናት ለዘለቀው ድህነትና ኋላ ቀርነት ዋነኛ ምክንያቶች ግጭት፣ አለመግባባት እንዲሁም አንድነቶቻችን ላይ የተመሰረቱ አገራዊ እሳቤዎች በመሸርሸራቸው በመሆኑ፤ ይህ ችግር ከመሰረቱ ሊቀርፍ የሚችለው ውይይት መሆኑን በማመን ለዚህም ተግባራዊነት ሁሉም የድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ ዶክተር ዲማ ነገዎ ጥሪ አቅርበዋል።

# በብሄራዊ ደረጃ የካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ ውድድርን 40 የቡና አምራች አርሶ አደሮች አሸነፉ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በብሄራዊ ደረጃ የካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ ኢትዮጵያ ውድድርን ለመጀመርያ ጊዜ 40 የቡና አምራች አርሶ አደሮች አሸናፊ ሆኑ። የአርሶ አደሮቹ ማሸነፍ ዘርፉን እንደሚያበረታታ የቡናና ሻይ ባለሥልጣን ገለጸ።

የቡናና ሻይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አዱኛ ደበላ እንደገለጹት፣ በብሄራዊ ደረጃ በተካሄደው የካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ ኢትዮጵያ ውድድር በቀጥታ ተሳታፊ ከነበሩት የቡና አምራች  አርሶ አደሮች መካከል 40 የሚሆኑ አሸናፊ መሆናቸው ዘርፉን ያበረታታል።

የቡና አምራች አርሶ አደሮች በቀጥታ በውድድሩ መሳተፍ እንዲችሉ መደረጉም አምራቾችን ባመረቱት የቡና ምርት ተወዳድረው በሚገኘው የተሻለ የግብይት ዋጋ ያለ ደላላ ጣልቃ ገብነት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። በተጨማሪም የተሻለ ጥራትና መጠን ያለው ቡና ለማምረት ስንቅ የይሆናቸዋል ሲሉም ዶክተር አዱኛ ተናግረዋል።

ለቡና አምራች አርሶ አደሮች በኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና አማራ ክልሎች የቡና ምርታማነትንና የጥራት ደረጃን በማሳደግ ምርታማነትን



**ዶክተር አዱኛ ደበላ፤**



**ቅድስት ሙሉጌታ፤**

የመጨመርና በአያያዝ ችግር የሚፈጠረውን የቡና ጥራት መጓደል የሚቀንሱ ሥልጠናዎቹ እየተሰጡ ነው። ይህም ከአምራቾቹ ልዩ ጣእም  ያላቸውን ተወዳዳሪ የሆኑ የቡና ምርትን  ለማግኘት እንደሚረዳ ዶክተር አዱኛ ተናግረዋል።

የካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ ኢትዮጵያ ዋና ስራ አስኪያጅና የኢትዮጵያ ተወካይ ቅድስት ሙሉጌታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ በካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ የሚወዳደሩት ማህበራትና ዩኒየኖች ብቻ ነበሩ።

በ2014 የተካሔደው የካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ ኢትዮጵያ ውድድር ከቀደሙ ውድድር የተለየ ነው ያሉት ተወካይዋ ፣ በውድድሩ የቡና አምራች ገበሬዎችና አርሶ አደሮች በቀጥታ ምርታቸውን አቅርበው ተሳታፊ ሆነውበታል ብለዋል።

አምራቾቹ መሳተፍ ብቻም ሳይሆን 40 ሚሆኑት የቡና አምራች አርሶ አደሮችም በምርታቸው የጠእም ልኬት ተወዳድረው ማሸነፍ ችለዋል ብለዋል።

የቡና ገበሬዎችና አርሶ አደሮች በውድደሩ በቀጥታ መሳተፋቸውና አሸናፊ መሆናቸው ለዘርፉ መነቃቃትን ይፈጥርላቸዋል። አምራቾቹ በቀጥታ በየካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ ኢትዮጵያ ውድድር ተወዳድሮ ባሸነፉበት ምርት በተሻለ ዋጋ ተሸጦ ከሚገኘው ሽያጭ ተጠቃሚ ለመሆን ያስችላቸዋል።

እንደ ቅድስት ገለጻም፣ እንደ አገር የካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ ኢትዮጵያ ውድድር የኢትዮጵያን የቡና ምርት ጥራት እንዲያድግና በዓለም ገበያ ዘልቆ ተመራጭ ቡና እንዲሆንም ያደርጋል ሲሉ ተናግረዋል።



ፎቶ - በአዩብ ተፈሪ

# የደሴ ከተማ የፍኖተ-ሰላም መረዳጃ እድር ከ1 ሺ 500 በላይ መጻህፍት ለአብርሖት ቤተመጻህፍት አስረከበ

**በሀይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፣ ከተመሰረተ 81ኛ ዓመቱ የሆነውና በደሴ ከተማ የሚገኘው የፍኖተ-ሰላም መረዳጃ እድር 1ሺ 512 መጻሕፍት ለአብርሖት ቤተመጻህፍት አስረከበ።

የፍኖተ ሰላም ዕድር አባል አቶ ዘሪሁን ማንደፍሮ ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት አብርሖት ቤተ-መጻህፍት በለጸገ ማለት ትውልድ በለጸገ፣  አገር እና ታሪክ ቀጠለ ማለት ነው ።  ትውልዱ  ነገ የተሻለ ህይወት እንዲኖር ማመቻቸት ነው ብለዋል።

እነዚህ መጻህፍት የተሰባሰቡት ከዕድሩ አባላትና ልጆች ከቤተሰቦቻቸው  በውርስ ያገኟቸውን ጭምር በማምጣት ጭምር የተሰባሰቡ መሆናቸውን ገልጸዋል። የአብርሆት  መጻህፍት መጠናከር ወጣቱም  ከሱስ ነጻ እንዲሆንና አገር እንዲረከብ የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አብርሖት ቤተመጻህፍትም ቀጣይነት ላለው ትውልድ የራሱ የሆነ አሻራ ለማስቀመጥ የተነሳ ስለሆነ ዓላማውን ለመደገፍ  ከማህበረሰቡ እና ከእድሩ አባላት በቀጣይም ተመሳሳይ ድጋፎች እንደሚኖሩም ጠቁመዋል።

በቀጣይ ከደሴ ከተማ አስተዳደር ጋር በመሆንም በአዲስ አበባ ያለው የአብርሖት ቤተመጻህፍት ተሞክሮ ለማስፋት  የበኩላቸውን  ጥረት  እንደሚያደርጉም ተናግረዋል።

በአዲስ አበባ ከተማም በርካታ ሰዎችን የሚመሩ እድሮች የሚገኙ በመሆኑ ሁሉም ዕድሮች ያቅማቸውን ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል። ለአብርሖት ቤተመጻህፍትም ሁሉም የአቅሙን ያህል  አንድም ሁለትም  መጻህፍት እንዲያበረክት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ሙዓዘጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በርክክቡ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት በጦርነት በተጎሳቆለችው፤ በፍቅር የምትታወቀው፤ ችግሮችን ተቋቁሞ ማለፍ ላይ ለብዙዎች አርአያ ከምትሆነው ከደሴ ከተማ ድረስ መጻሕፍትን ለአብርሖት ማበርከት ስጦታው ከመጻህፍቱ በላይ ነው ብለዋል።

ከ400 ኪሎ ሜትር ድረስ መጻህፍት ይዘው የመጡትን የዕድሩን አባላት አመስግነው ከአባቶች እና ከእናቶች መጻህፍትን፣ ዕውቀተን እና መልካምነትን ማውረስ እንደሚገባ ያመላክታል ብለዋል።

በአዲስ አበባ የሚገኙ ከ300 በላይ እድሮችም ከደሴ  ከተማ  ተሞክሮ  በመውሰድ  ጥንታዊና መጻሕፍትን እንዲያሰባስቡም ጥሪ አቅርበዋል።

"ሚሊዮን መጻህፍት ለሚሊኒየሙ ትውልድ" በሚል ለአብርሖት ቤተመጻህፍት መጻሕፍት የማሰባሰብ መርሃ ግብሩ እስከ ግንቦት 29 የሚቀጥል መሆኑም ተገልጿል።

# ድርጅቱ ከ40ሺ በላይ ተሽከርካሪዎች ወደ ኤሌክትሪክ መኪና እንዲቀየሩ እየሠራ መሆኑን አስታወቀ

**ማህሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- ራይድ የትራንስፖርት አገልግሎት በስሩ ያሉ ከ40ሺ በላይ የሚልቁ አሽከርካሪዎች መኪናዎቻቸውን በኤሌክትሪክ ሃይል ወደሚሰራ መኪና እንዲቀይሩ እየሰራ መሆኑን አስታወቀ።

የራይድ መስራችና ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወ/ት ሳምራዊት ፍቅሩ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ ድርጅታቸው በስሩ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ከ40ሺ በላይ የሚሆኑ አሽከርካሪዎች ከባንክና ከመኪና አምራች ኩባንያዎች ጋር በማስተሳሰር መኪናዎቻቸውን ዘመናዊና በኤሌክትሪክ ሃይል ወደሚሰራ ተሽከርካሪ ለመቀየር እየሰራ ነው።

እንደዋና ሥራ አስፈፃሚዋ ገለፃ፤ የተሽከርካሪዎቹ መቀየር ከጊዜ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የነዳጅና የተሽከሪካሪ መለዋወጫ ወጪን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። በተለይም አገሪቱ ለነዳጅና ለተሽከርካሪ መለዋወጭ የምታወጣው የውጭ ምንዛሬ በመታደግ ለሌላ የልማት ሥራ እንድታውለው ለማድረግ የጎላ ሚና አለው። በተጨማሪም በከተሞች የሚስተዋለውን ከፍተኛ የበካይ ጋዝ ልቀትን ለመከላከል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ከነዳጁ ባሻገር መለዋወጫዎችን ከውጭ በበርካታ ቢሊዮን ዶላር በማውጣት እያስመጣች በመሆኑ የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንዲባባስ ምክንያት እንደሆነ ዋና ስራ አስፈፃሚዋ አስረድተዋል። ይህም ሀገሪቱ ለዘመናት የኢኮኖሚ ጥገኛ እንድትሆን ያደረጋት መሆንኑም አብራርተዋል። ‹‹በመሆኑም ጥገኝነታችንን እየቀነስን ለመምጣት ከውጭ የሚመጣውን እዚሁ የሚተካበትን መንገድ መፍጠር አለብን። አንደኛው ደግሞ በነዳጅ ከሚነዳው መኪና ወደ ኤሌክትሪክ መኪና መሸጋገር አዋጭ ነው›› ብለዋል።

እንደእንግሊዝ ያሉ በኢኮኖሚ ያደጉ ሀገራት ሳይቀሩ ተሽከርካሪዎቻቸውን ሙሉ ለሙሉ በኤሌክትሪክ ሃይል ወደሚሰሩ ለመቀየር አቅደው እየሰሩ መሆኑም አመልክተዋል። ‹‹እርግጥ ነው በእኛ ሀገር በአሁኑ ወቅት ካለው የሃይል እጥረት አኳያ ሙሉ ለሙሉ ወደዚህ ሥርዓት መግባት ያስቸግራል። ያም ቢሆን  ግን ከነዳጁ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ነው የምንታደገው›› በማለት ተናግረዋል። ስለሆነም የተሽከርካሪዎቹን ቁጥር ከዚህ በላይ ከመጨመራቸው በፊት በኤሌክትሪክ



ፎቶ በገባቦ ገብሬ

**ወ/ት ሳምራዊት ፍቅሩ**

መተካቱ ለኢኮኖሚው ማንሰራራት ወሳኝ ሚና እንዳለውም አስረድተዋል።

ድርጅታቸው ከሶስት ዓመታት በፊት ለሙከራ አንድ በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሰራ ዘመናዊ መኪና በ1 ነጥብ1 ሚሊዮን ብር ማስመጣቱን አስታውሰው በአሁኑ ወቅት ግን ዋጋው ወደ ሁለት ሚሊዮን ብር መጠጋቱን ጠቁመዋል። በመሆኑም ድርጅታቸው በስራቸው የሚሰሩ የተሽከርካሪ ባለቤቶችን ከባንክና ከመኪና አምራቾች ጋር በማስተሳሰር የድልድይነት ሚና እንደሚጫወት አስገንዝበዋል። ‹‹አሽከርካሪዎችን ከመኪና አምራቹና ከባንክ ጋር በማስተሳሰር  የራይድ ቤተሰብ የሆኑ መኪናቸውን እንዲቀይሩ እንረዳለን›› ብለዋል።

በመሆኑም የሚችል አሽከርካሪ ስድስት ወር ቆጥቦ፤ ሌላው ደግሞ 20 ና 30 በመቶውን ቅድሚያ ከፍሎ መኪናውን መግዛት እንደሚችል ተናረዋል። ድርጅታቸው ለአሽከርካሪዎቹ እንዲህ አይነቱን ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ ለህብረተሰቡ የሚሰጠው የትራንስፖርት አገልግሎቱን ቀልጣፋ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አስረድተዋል።

እንደ ወ/ት ሳምራዊት ገለፃ፤ ራይድ በቅርቡ አገልግሎቱን ወደ  ክልሎች እና ምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ለማስፋት እየሰራ ይገኛል።  ድርጅቱ ከተቋቋመበት ካለፉት ሰባት ዓመታት ወዲህ ከ43ሺ በላይ የሚሆኑ ተሽከርካሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ የቻለ ሲሆን 500 ለሚሆኑ ዜጎች ደግሞ ቋሚ የስራ እድል ፈጥሯል።

ዜና

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለተለያዩ ግለሰቦች ሹመት ሰጡ

**- አምባሳደር ሬድዋን የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ሚኒስትር ሆነዋል**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በትናንትናው ዕለት ለተለያዩ ግለሰቦች ሹመት ሰጥተዋል።

ሹመት ከተሰጠባቸው የመንግሥት የሥራ ኃላፊነት ቦታዎች መካከል የብሔራዊ ደሕንነት አማካሪ ሚኒስትር፣ የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ የፕሮጀክቶች ክትትል፣ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ይገኙበታል።

በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ዋና ኦዲተርና ምክትል ዋና ኦዲተር ሾመዋል።

**በዚህ መሰረትም፡-**

- አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደሕንነት አማካሪ ሚኒስትር
- አቶ ካሊድ አብዱራሂማን በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ የፕሮጀክቶች ክትትል
- አቶ ወንድሙ ሴታ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ፣
- አቶ ሄኖስ ወርቁ የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር

በተጨማሪም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚከተሉትን ሹመቶች እንዲጸድቁ ጠይቀዋል፡፡

- ወይዘሮ መሰረት ዳምጤ- የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ዋና ኦዲተር
- አቶ አበራ ታደሰ - የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ምክትል ዋና ኦዲተር

መረጃው የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ነው።

# በሐምሌ ወር ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ማድረጉን የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የዋጋ ማስተካከያው በሚተገበርበት ወቅት አነስተኛ ገቢ ባላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የጎላ ተጽዕኖ በማያደርስ መንገድ መፈጸም መቻል እንዳለበት ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ለሜሳ ገለጻ፤ በታለመለት የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያው አነስተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን መደገፍ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቶች በኩል ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ መመሪያ ወጥቶ ለተግባራዊነቱ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

የከተማ አውቶብሶች፣ የሸገር ትራንስፖርት፣ ድጋፍ ሰጭ አውቶብሶች፣ ፐብሊክ ሰርቪስ፣ ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ ሦስት ያሉ በታሪፍ የሚሰሩ አገር አቋራጭ አውቶብሶች፣ ከ12 ሰው እስከ 40 ሰው የሚጭኑ መለስተኛ ተሽከርካሪዎች፣ የታክሲ አገልግሎት የሚሰጡ ሚኒባሶችና ባጃጆች የድጋፉ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ገልጸዋል።

ከዋጋ ጋር የተያያዘ፣ የነዳጅ መሰረተ ልማትና ሎጂስቲክስ፣ ከትራንስፖርት አሰራር፣ ክትትልና ቁጥጥር ጋር ተያይዞ የሚመጡ ችግሮች ተዳምረው በነዳጅ ግብይት ዙሪያ በርካታ ችግሮች መስተዋላቸውን ጠቁመዋል።

በነዳጅ ላይ የነበረውን የቁጥጥርና የክትትል ስርዓት መልክ ለማስያዝ ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በመነጋገር መመሪያ ወጥቶ ችግሩ እንዲቀረፍ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያው በጊዜ የተገደበና የታለመለት የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ የጅምላ ድጎማን በማስወገድ ወደ ዋጋ ማረጋጊያ ፈንድ ስርዓቱ መመለስና የተከማቸውን 132 ቢሊዮን ብር ዕዳ በሂደት ማቃለልን ዓላማ ያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

# የከባቢ አየርን የሚበክሉ ነገሮችን በመከላከል ረገድ ሁሉም የበኩሉን ሚና እንዲወጣ ጥሪ ቀረበ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- የከባቢ አየርን የሚበክሉና ሙቀት የሚጨምሩ ነገሮችን በመከላከል ረገድ ሁሉም ግለሰብና ተቋም የበኩሉን ሚና እንዲወጣ ጥሪ ቀረበ።

በዓለም ለ49ኛ ጊዜ በኢትጵያ ለ29ኛ ጊዜ የሚከበረው የዓለም አካባቢ ቀን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀው የአካባቢ ጥበቃ አውደ ርዕይ ትናንትና በወዳጅነት አደባባይ ተከፈተ።

የግሎባል ግሪን ግሮውዝ ኢንስቲትዩ የኢትዮጵያ ዳይሬክተር ዶክተር ገመዶ ዳሌ በአውደ ርዕይው መከፈቻ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ የሰው ልጅ የሚኖርበት የተለየ ምድር የለውምና ሁሉም ለራሱ ሲል ምድርን ከብክለት የጸዳች አድርጎ መጠበቅ አለበት። በተለይም የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት መከላከል የሁሉም ግዴታ ሊሆን ይገባል ብለዋል።

የሰው ልጅ የዕለት ተዕለት አኗኗር ሂደት ተፈጥሮን በሚያናጋ መልኩ መከናወን የለበትም። በተለይ በካይ ጋር ልቀትን በመቆጣጠር ሙቀት የሚጨምሩ ነገሮችን የመከላከል ኃላፊነቱ የሁሉም ሊሆን ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

እንደ ዶክተር ገመዶ ገለጻ፤ የዓለም የአካባቢ ጥበቃ ቀን "አንድ ምድር ብቻ በሚል መሪ ቃል በዘላቂነት ከተፈጥሮ ጋር በስምምነት መኖር እንደሚገባ መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው። ስለዚህ የሰው ልጅ ያለችውን አንድ መኖሪያ ምድር በመንከባከብና አየር ንብረቷን በመጠበቅ ሕይወቱን ሊያስቀጥል ይገባል።

በተለይም ሁሉም ሰው የተራቆቱ ቦታዎችን በአረንጓዴ አሻራ በመሸፈን ብክለት በሚቀንስ አጠቃቀም ዘላቂነትን ማረጋገጥ ይኖርበታል ያሉት ዶክተር ገመዶ፤ ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን የሚተገብሩ መንግሥታትና ተቋማት የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት በመቀነስ፣ አሮጌ ኮምፒተሮችንና ጊዜ ያላፈባቸው ኬሚካሎች በጥንቃቄ በማስወገድ ለችግሩ መፍትሄ ማበጀት አለባቸው ብለዋል።

የትምህርት ተቋማትም የማሕበረሰቡን ንቃት ህሊናና የመፈፀም አቅም የሚጨምሩ ጥናቶችን ማቅረብ እንዳለባቸው ጠቁመዋል።



ዶክተር ገመዶ ዳሌ



ዶክተር ማርጋሬት ኦዱክ

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራምን ወክለው የተገኙት ዶክተር ማርጋሬት ኦዱክ እንደገለጹት፤ የሰው ልጅ ጤናው ተጠብቆ በሰላምና በደህንነት እንዲኖር ከፈለገ ምድርን ከብክለት የፀዳች ማድረግ ይጠበቅበታል።

ለሁሉም አንድ የሆነች ምድር ከብክለት የጸዳች ማድረግ የህልውና ጉዳይ እንጂ የውዴታ ጉዳይ አለመሆኑን ገልጸው፤ ሁሉም ህብረተሰብ እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

የሰው ልጆች ድርጊት የተነሳ የተበከለች ምድር ሳይሆን የጸዳች ምድር ለትውልድ ለማስተላለፍ ሁሉም የበኩሉን ሚና መጫወት አለበት፤ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የአረጓዴ ልማትን ተግባራዊ በማድረግና አመራር በመስጠት የምታከናውነው ስራ የሚበረታታ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍሬነሽ መኩሪያ በበኩላቸው፤ ለሶስት ዓመት በአሬንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የተተከሉ ችግኖች ከብክለት የፀዳች ኢትዮጵያን ለትውልድ ለማስተላለፍ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ስራ ተሰርቷል ብለዋል፡፡

የወደጅነት ፓርክ፣ አንድነት ፓርክ ፣እንጦጦ ቱሪስት መዳረሻ፣ ኮይሻና ጎርጎራ እንዲሁም ወንጪ ፕሮጀክቶችም የሀገራችን ገጽታ የቀየሩ የአረንጓዴ ልማቶች መሆናቸውን ጠቁመው፤ በቀጣይም ተመሳሳይ የአረንጓዴ ልማትና የገጽታ ግንባታ ስራዎች እንደሚከናወኑ ተናግረዋል።

አካባቢን መጠበቅና አየር ንብረት እንዳይጎዳ መንከባከብ የሁሉም ኃላፊነት ነው በዚህ ረገድ ባለሥልጣኑ በተለያዩ ጊዜያት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

በወዳጅነት አደባባይ የተከፈተው ዓውደ ርዕይ እስከ ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ እንደሚቆይ ታውቋል።

# የተምች ወረርሽኝ በአራት ክልሎች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ስፋት ባለው ሁኔታ በ11 ሺህ 229 ሄክታር መሬት ላይ መከሰቱ ነው ብለዋል፡፡

ተምቹ ከደቡብ የሀገሪቱ ክፍል መነሳቱን የገለጹት አቶ በላይነህ፣ አሁን ላይ በኦሮሚያ ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና በጋምቤላ አካባቢዎች ተከስቷል፡፡

የተምች ወረርሽኙ እንደሚከሰት ቀድሞ የታወቀ ነበር ያሉት ዳይሬክተሩ፣ በተከሰተባቸው አካባቢዎች መንግሥት፣ የክልሎቹ መንግሥታት በኬሚካል መርጫ እና ማህበረሰቡ በባህላዊ የመከላከያ ዘዴ በመጠቀም በቅንጅት የመከላከሉን ስራ በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ እስካሁንም የ11 ሺህ 400 ሊትር ገደማ የኬሚካል ርጭት ተካሂዷል ብለዋል፡፡

በተሰራው የተቀናጀ የመከላከል ስራም እስካሁን ተምቹ የከፋ ጉዳት አላደረሰም፣ እስካሁንም 11 ሺህ 271 ሄክታሩን በኬሚካል፣ 11 ሺህ 637 ሄክታር መሬት ደግሞ በባህላዊ መንገድ ተምቹን የመከላከል ስራ ተሰርቷል፡፡ በአጠቃላይ 23 ሺህ 219 ሄክታር ሜሬት ላይ የመከላከል ስራ መሰራቱን ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል፡፡

ለተምች መከላከሉ በማህበረሰቡ ዘንድ በስፋት ጥቅም ላይ የዋለው የባህላዊ የመከላከል ዘዴ እንደሆነና ውጤትም እንዳመጣ አቶ በላይነህ ጠቁመዋል፡፡

የመርጫ መሳሪያና የኬሚካል ስርጭትም ክልሎች ያላቸውን ተጋላጭነት መሰረት በማድረግ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ህብረተሰቡ በኬሚካል ከመከላከል የልቅ የጎንዮሽ ጉዳት የሌለውን የባህላዊ ዘዴ እንዲጠቀምመ አቶ በላይነህ ጠይቀዋል፡፡

በጋምቤላ ክልል ብቻ የተምች ወረርሽኝ በአምስት ወረዳዎች ውስጥ በሰባት ሺህ 446 ሄክታር መሬት ላይ መከሰቱን የጋምቤላ ክልል እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታውቋል።

የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ኩዌት ሉል እንደተናገሩት፣ ወረርሽኙ በአምስት ወረዳዎች ውስጥ በሚገኝ ሰባት ሺህ 446 ሄክታር መሬት ላይ ተከሰቷል፡፡

እንደ አቶ ኩዌት ገለጻ፣ የተከሰተውን የተምች ተባይን ለማጥፋት በተደረገ ጥረት በባህላዊና ፀረ-ተባይ በመርጨት አንድ ሺህ 376 ሄክታር ሰብልን ለመቆጣጠር ተችሏል፡፡ በአሁኑ ወቅት ወረርሽኙን በባህላዊና በዘመናዊ የመከላከያ ዘዴዎች ለመቆጣጠር ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

በክልሉ ወረርሽኙ የተከሰተባቸው አምስቱ ወረዳዎችም በዲማ፣ በላሬ፣ በኢታንግ፣ በጎደሬና በጋምቤላ መሆናቸውን አቶ ኩዌት ገልጸው፣ በሩዝ ሰብል ላይ የተከሠተ በአምስት ሺህ ሄክታሩ መሆኑንና ቀሪው በበቆሎ ሰብል ላይ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

በቢሮው የዕጽዋት ጥበቃ ዳይሬክተር አቶ አብዱረህማን ሁሴን በበኩላቸው፣ በክልሉ በቀጣዩ የምርት ዘመን በመኸር እርሻ 148 ሺህ 786 ሄክታር በማልማት ከአራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት ታቅዶ እስካሁን 72 ሺህ 708 ሄክታር በዘር መሸፈኑንም ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አብዱረህማን ገለጻ፣ ከግንቦት ወር ጀምሮ በአምስት ወረዳዎች የተምች ወረርሽኝ በመከሰቱ የምርት እጥረት እንዳይከሰት ቢሮው በትኩረት እየሠራ ነው።

ህብረተሰቡ የተለያዩ ባህላዊና ዘመናዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ተምቹ የከፋ ጉዳት እንዳያደርስ የመከላከል ስራውን እያከናወኑ መሆኑን የገለጹት አቶ አብዱረህማን፣ የክልሉ መንግሥት ባለሙያዎችን ማሰማራቱንና ፀረ-ተባይ ኬሚካል ማሰራጨቱን ተናግረዋል።

በዲማ ወረዳ ተምቹ የተከሰተው በወረዳው በሚገኙ ሁለት ቀበሌዎች ኮይና ከርከን ቀበሌ ሲሆን በአምስት ሺህ ሄክታር መሬት የሩዝ ማሳ ላይ ጉዳት እያደረሰ ነው። በዲማ ወረዳ የኮይ ቀበሌ የተምች ወረርሽኝ ከግንቦት ወር መግቢያ ጀምሮ እንደተከሰተ አቶ አብዱረህማን ገልጸው፣ ነዋሪዎቹ በባህላዊ መንገድ ለመከላከል አዳጋች እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

አቶ አብዱረህማን አክለውም፣ በቀጣይ የምርት መቀነስ ሊያጋጥም ይችላል የሚል ሥጋት እንዳደረባቸው ተናግረዋል፡፡

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 9ኛ መደበኛ ስብሰባ በ2015 የፌዴራል መንግሥት ረቂቅ በጀት ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

የፌዴራል መንግሥት የ2015 በጀት ዓመት የበጀት ዝግጅት በአስር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ የተቀመጡ ግቦችን ከማስፈጸም አኳያ፣ የሀገር ደህንነትን ከማስጠበቅ፣ የተፈናቀሉ ዜጎችን ከመርዳትና የወደሙ መሰረተ ልማቶችን እና አገልግሎቶችን መልሶ ከማቋቋም፣ ቀጣይ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን አቅጣጫዎችና ዓላማዎችን ማሳካት ማእከል በማድረግ እንዲሁም፤ የ2015-2019 የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና የፊስካል ማዕቀፉን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቶ የቀረበ መሆኑን ተመልክቷል።

በዚህም መሰረት ለ2015 በጀት ዓመት ለመደበኛ ወጪ ብር 347 ነጥብ 12 ቢሊዮን፣ ለካፒታል ወጪ ብር 218 ነጥብ 11 ቢሊዮን እንዲሁም ለክልል መንግሥታት ድጋፍ ብር 209 ነጥብ 38 ቢሊዮን እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 12 ቢሊዮን የተያዘ ሲሆን፤ አጠቃላይ የፌዴራል መንግሥት የ2015 ረቂቅ በጀት 786 ነጥብ 61 ቢሊዮን ብር ሆኖ ቀርቧል፡፡

ከ2014 በጀት ዓመት በጀት ጋር ሲነጻጸር የብር 111 ነጥብ 94 ቢሊዮን ወይም የ16 ነጥብ 59 በመቶ እድገት አሳይቷል፡፡

ምክር ቤቱም በቀረበለት የፌዴራል መንግሥት የ2015 ረቂቅ በጀት ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የቅዳሜ መፅሄት

# አገልግል

## ‹‹በሥራችን ስኬታማ ለመሆን ራዕያችን ላይ ሁልጊዜ ትኩረት ማድረግ አለብን››

ወ/ት ሳምራዊት ፍቅሩ

የራይድ መስራችና ሥራ አስፈፃሚ



ገጽ 6



## ስኬትን ያጐናጸፈ የነፍስ ጥሪ

ገጽ 13



## ኑሮ - ከቤተመንግሥት እስከ ጎዳና

ገጽ 16

## ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# በመጠጥ ግዥ ላይ የሚስተዋለው የመረጃ መዛባትና መፍትሄው

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ በተለይ በሀገሪቱ የመጣውን ፖለቲካዊ ለውጥ ተከትሎ ብቃት ያለውና አገልጋይነትን የተላበሰ የሰው ኃይል በመገንባት፣ ፍትሐዊና ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ዕውን አድርጎ ተደራሽ አገልግሎት በመስጠትና ግብርን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር ለከተማዋ ዕድገትና ብልጽግና የሚያስፈልጋትን ገቢ በብቃት መሰብሰብ የሚያስችል ተልዕኮ በማንገብ ተግቶ እየሠራ ይገኛል። በዚህም መዲናዋ የሚያስፈልጋትን ገቢ ከግብር ወይም ከታክስ በብቃት በመሰብሰብ የራሷን ወጪ በራሷ የመሸፈን አቅሟ ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ እየተሻሻለ መጥቷል።

ይሁን እንጂ የከተማዋ ኢኮኖሚ የሚያመነጨው ገቢ በብቃት ከመሰብሰብ አንፃር አሁንም የሚስተዋሉ ክፍተቶች አሉ። ለዚህ ደግሞ እንደ ዋና ምክንያት የሚጠቀሱት ግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ስለግብር ያለው የግንዛቤ ማነስ፣ የመረጃ መዛባት፣ ማታለልና ማጭበርበር እንዲሁም ግብር መሰወር ድረስ የዘለቁ የተዛቡ አመለካከቶች የራሳቸው አስተዋጽዖ አላቸው። በነዚህ ጉዳዮች ላይ የጠራ ግንዛቤ መፍጠር፣ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ የከተማዋ ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት ለመሰብሰብና ኢኮኖሚውን ለማፋጠን የማይተካ ሚና ይጫወታል።

ከዚህ አኳያ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የመጠጥ ግዥ ላይ ያለውን የመረጃ መዛባት ለማስተካከል ከመጠጥ ፋብሪካ ተወካዮች ጋር ከሰሞኑ ውይይት አድርጓል፡፡ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የሕግ ተገዥነት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ኮማንደር አህመድ መሀመድ የውይይት መድረኩን በከፈቱበት ወቅት፤ በመጠጥ አምራቾች፣ በወኪል አከፋፋዮችና በመጠጥ ንግድ ላይ የተሰማሩ ግለሰብ ነጋዴዎች መካከል የሚታየውን የመረጃ መዛባት መነሻ በመለየት መፍትሔ ለመስጠት የተዘጋጀ መድረክ መሆኑን ይገልፃሉ።



ከግራ ወደ ቀኝ ኮማንደር አህመድ መሀመድ እና አቶ ተስፋዬ ቱሉ፤



የውይይቱ ተሳታፊዎች፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ የመረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ ልደቱ የመወያያ ሰነድ አቅርበዋል። በሰነዱም ያልተጠቀሙበትን ወይም ግዥ ያልፈፀሙበትን መረጃ እንደገዙ አድርጎ ማስተላለፍ፣ መረጃ ከተላለፈ በኋላ አቤቱታ ማቅረብና ቀድሞ ከተላለፈው መረጃ መቀነስ፣ የግዥ ውል ወይም የደንበኝነት ግንኙነት የሌለው ግብር ከፋይን ግዥ ፈፅሟል በማለት መረጃ መላክና አቤቱታ ሲቀርብ መረጃውን ሰርዞ ማቅረብ እንዲሁም ንግድ ፈቃዳቸውን በዘጉ ግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር ሽያጭ ተፈፅሟል በማለት መረጃ ማስተላለፍ የመሳሰሉት በመጠጥ ግዥ ላይ የሚስተዋሉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች እንደሆኑ ጠቅሰዋል፡፡

ውይይቱን በገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ስርዓት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተስፋዬ ቱሉ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ የሕግ ተገዥነት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ኮማንደር አህመድ መሀመድ በጋራ የመሩት ሲሆን፤ በዘርፉ የታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ በገቢዎች ሚኒስቴር እና በአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ በኩል ሊሠሩ የሚገባቸውን ብሎም ከአልኮል መጠጥ አምራች ድርጅቶችና ከወኪል አከፋፋዮች እንዲሁም ከቸርቻሪ ነጋዴዎች ይጠበቃሉ ያሏቸውን ሥራዎች አስቀምጠዋል፡፡

ግልጽ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ፣ ያልተገባ ተግባር ላይ በተሰማሩ አካላት ላይ ርምጃ መውሰድ፣ ግብይት በደረሰኝ ማድረግ ያለውን ጠቀሜታ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ መሥራት፣ ከሌሎች አጋር አካላት ጋር ውይይት እና ምክክር ማድረግ እንዲሁም ተጠያቂነትን መዘርጋት በገቢዎች ሚኒስቴር እና በአዲስ አበባ ከተማ አስታዳደር ገቢዎች ቢሮ በኩል እንዲሠሩ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

በአንጻሩ በአልኮል መጠጥ አምራች ድርጅቶችና ወኪል አከፋፋዮች በኩል ለራስ፣ ለሀገር፣ ለሚያከፋፍሉት ቸርቻሪ ነጋዴ ታማኝ መሆን፣ የሽያጭ ባለሙያ ሠራተኞቻቸውን ስነ-ምግባር መከታተል እና ደረሰኝ አልፈልግም ለሚል ቸርቻሪ ነጋዴ የአልኮል መጠጥ ምርቶችን ባለመስጠት የሚጠበቅባቸውን ሀገራዊ ኃላፊነት መወጣት እንደሚጠበቅባቸው አቅጣጫ ተቀምጧል። በተጨማሪም ከቸርቻሪ ነጋዴዎች ግዥ የሚፈጽሙበትን መረጃ በስርዓቱ በመያዝ እና ያለ ደረሰኝ ሽያጭ ባለማከናወን ጤናማ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ ሊመሩ ይገባልም ተብሏል። በውይይት መድረኩ የገቢዎች ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ከፍተኛ አመራሮች፣ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲሁም የመጠጥ ፋብሪካ ተወካዮች ተሳትፈዋል፡፡

## አድራሻ፡-

ስልክ የቢሮ ኃላፊ 0115575790
የጽ/ቤት ኃላፊ 0115575741
የሞ/ኮ/ስ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575748
የታ/ጉ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575608
የህግ ማ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575604
Facebook page: Addis Ababa revenue bureau
Web site: http//aarevenue.gov.et
P.O. Box 27400 code 1000

**የላቀ ገቢ ለአዲስ አበባችን ብልፅግና!**

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

# «በሥራችን ስኬታማ ለመሆን ራዕያችን ላይ ሁልጊዜ ትኩረት ማድረግ አለብን»

*- ወይዘሪት ሳምራዊት ፍቅሩ*
*የራይድ መስራችና ሥራ አስፈፃሚ*



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

ማህሌት አብዱል

**የዛሬው የዘመን እንግዳችን ከሥራ ፈጣሪ ሴቶች መካከል አንዷ የሆነችው ወይዘሪት ሳምራዊት ፍቅሩ ናት። እንግዳችን ተወልዳ ያደገችው አሰላ ከተማ ውስጥ ነው። የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን የተከታተለችው እድገት በሥራ በተባለ እና ጭላሎ ተራራ በሚባል ትምህርት ቤት ነው። በማይክሮሊንግ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኮሌጅ በሶፍትዌር ኢንጅነሪንግ ዲፕሎማ እንዲሁም ሂልኮ በተሰኘ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኮሌጅ ደግሞ በኮምፒዩተር ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪ አግኝታለች። ገና በወጣትነቷ ጀምሮ ተቀጥረው ለሚሰራበት ሙዚቃ ቤት የራስዋን የሽያጭ ሪፖርት የሚያቀርብ ሶፍትዌር ከመስራት ጀምሮ የተለያዩ ሥራዎችን የሚያቀላጥፉ ቴክኖሎጂዎችን ለኢትዮጵያ በማስተዋወቅ ግንባር ቀደም ሆናለች።**

**ለሽንፈት እጅ የማትሰጠው እንግዳችን በሴትነቷና በወጣትነቷ ምክንያት በተደጋጋሚ የሰራቻቸው የምርምር ሥራዎች ተቀባይነት ባያገኙም ለኢትዮጵያ አዲስ የሆነና በቴክኖሎጂ የታገዘ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሥርዓት በመፍጠር ረገድ ፈር ቀዳጅ መሆን ችላለች። በአሁኑ ወቅት ከ40ሺ በላይ ለሚሆኑ አሽከርካሪዎች የሥራ በር በከፈተው በራይድ የትራንስፖርት አገልግሎት ከ500 ለማያንሱ ዜጎችም ቋሚ የሥራ እድል ፈጥራለች። ከሰሞኑ ደግሞ የምርጥ አፍሪካዊ ቢዝነስ ባለራዕይ ሽልማት አሸናፊ ሆናለች። አዲስ ዘመን ጋዜጣም ወጣቷን ሥራ ፈጣሪ የዛሬው የዘመን እንግዳ አድርጎ እንደሚከተለው ይዞ ቀርቧል።**

**አዲስ ዘመን፡- ወደ ቴክኖሎጂ ፈጠራ የገባሽበትን አጋጣሚ አስታውሺንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**ወይዘሪት ሳምራዊት፡-** እንደሚታወቀው ተወልጄ ያደኩባት አሰላ ለአዲስ አበባ ቅርብ፣ አንባቢና ንቁ ማህበረሰብ ያለባት ትንሽ ከተማ ብትሆንም ለቴክኖሎጂ ግን ነዋሪዎቿ የዚያኑ ያህል ቅርብ አልነበሩም። እኔ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በምማርበት ጊዜ እቅዴ የነበረው ሜዲካል ዶክተር መሆን ነው። ምክንያቱም ደግሞ የነበረው አንድ ሆስፒታል ብቻ ስለነበር ብዙ ህብረተሰብ አገልግሎት ማግኘት ሲቸገር እመለከት ስለነበር ነው። አንዲት አጋጣሚ ግን የልጅነት ህልሜን የሚያስቀየር ነገር ፈጠረች። ይኸውም አንድ ቀን ከእናቴ ጋር ገበያ እየሄድኩ ሳለ አንድ የኮምፒዩተር ማሰልጠኛ ማዕከል ጋር በአጋጣሚ እናቴ ቆማ ሰው ሰላም እያለች ባለችበት ቅስበት እኔ ማዕከሉ ውስጥ ባለው ኮምፒዩተር ላይ አይኖቼ አተኩረው ቀሩ። ሰዎች ቁጭ ብለው በኮምፒዩተሩ ሲፅፉና የተለያዩ ሥራዎችን እየሰሩ ተመለከትኩኝ። በተለይ የሚንቀጠቀጠው እስክሪኑ የበለጠ ጥያቄ አጫረብኝ እናቴን ስለምንነቱ ስጠይቃት እንደማታውቀው ነገረችኝ። ቀጠልኩና ኤሌክትሪክ ኢንጂነር ወደሆነውና አዲስ አበባ የሚኖረው ወንድሜ ጋር ደወልኩና ስላየሁት ነገር ጠየኩት። እሱም ኮምፒዩተር መሆኑንና ስለምንነቱ አብራራልኝ።

ክረምት ላይ ወንድሜ ጋር ስመጣ የበለጠ በተግባር በታገዘ ሁኔታ ስለኮምፒዩተር ማወቅ ቻልኩኝ። እኔም በዚህ ቴክኖሎጂ እጅግ ስለተመስጥኩኝ ብዙ ጥያቄዎች መጠየቅና መመራመር ጀመርኩ። ብዙም ሳልቆይ ደግሞ ስለኢንተርኔት አስረዳኝና ለእህቴ ደብዳቤ እንድፅፍ ነገረኝ። ከዚያ ደግሞ ደብዳቤ እንዴት በፍጥነት ሊደርሳት ቻለ? የሚል ጥያቄ ፈጠረብኝ። በመጨረሻ ይህ ቴክኖሎጂ ሁሉንም ዘርፍ የሚነካና የሚገባ መሆኑን ተረዳሁ። ስለዚህ ኮምፒዩተር ብማር የበለጠ ጠቃሚ መሆኑን ተገነዘብኩኝ። በዚያ መሰረት ማይክሮሊንክ ኮሌጅ በሶፍትዌር ኢንጅሪንግ እንዲሁም ሂልኮ በተባለ ኮሌጅ በመግባት ኮምፒዩተር ሳይንስ አጠናሁኝ። ከዚሁ ጎን ለጎን ግን በተለያዩ ኩባንያዎች ውስጥ ተቀጥሬ ስሰራ ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- በኮምፒዩተር ሳይንስ ከተመረቅሽ በኋላ በቀጥታ በተማርሽበት ሙያ ለምን ነበር መስራት ያልቻልሽው?**

**ወይዘሪት ሳምራዊት፡-** በቀጥታ በተማርኩበት ዘርፍ ሥራ መስራት ያልቻልኩባቸው በርካታ ምክንያቶች ነበሩ።ከሙያዬ ውጭ ተቀጥሬ ስሰራ የነበረው እኔ ወደፊት እደርስበታለሁ ብዬ ላመንኩበት ነገር መሳካት የብዙ ሙያ እውቀት ያሻኛል ብዬ አስብ ስለነበረ ነው። ለዚህ ደግሞ የሚጎድለኝን ክህሎት ማሳደግ ነበረብኝ። አንድን ነገር ሰርቶ ለመሸጥ የመግባባት ክህሎት ያፈልጋል። ስለዚህ ሽያጭ ያለበት ቦታ ላይ ግዴታ መቀጠር አለብኝ ብዬ ወሰንኩኝ። በዚያ መሰረት አንድ ሙዚቃ ቤት ተቀጥሬ ካሴቶችን መሸጥ ጀመርኩኝ። መጀመሪያ ላይ ትንሽ ከባድ ነበር። በተለይም እንደእኛ ሃገር ዝምተኝነትን የሚያበረታታ ማህበረሰብ ባለበት ሀገር ውስጥ ሰዎችን አግባብቶና አሳምኖ እቃን መሸጥ ፈታኝ ነበር። ሆኖም ሽያጭ እየሰራሁ ሲስተም አናሊስት ሆኜ ለሌላም ድርጅት እሰራ ነበር። በዚያ መልኩ ነው አቅሜን ያጎለበትኩት።

የሚገርምሽ በሙዚቃ ቤቱ እየሰራሁ በነበርኩበት ጊዜ የቀኑ በጣም ከፍተኛ የሆነ ሽያጭ እንፈፅም የነበረ ቢሆንም በወረቀት ፅፈን ነበር የምናስገባው። በየቀኑ የሸጥኩትን ስደምርና ስቀንስ ረጅም ጊዜ ይወስድብኝ ነበር። ለባለቤቱ ደግሞ እንዲሁ በእጅ ጽፌ ነበር ሪፖርት አደርግ የነበረው። በተለይም በምደምርበት ጊዜ ብዙ መሳሳቶች ያጋጥሙኝ ነበር። ሁለተኛ ደግሞ ደምበኞች የሚፈልጓቸውን ሙዚቃዎች ያሉና የሌሉ መሆናቸውን የምናረጋግጥበት ስርዓት አልነበረንም። ቶሎ የምናስተናግድበት ሲስተም ባለመኖሩም አንዳንድ ጊዜ ደንበኞቻችንን እናበሳጭ ነበር። በመሆኑም ሁልጊዜ ደምበኞቻችንን እያበሳጨን መዝለቅ የለብንም፤ መፍትሄ መፈለግ አለብኝ የሚል ድምዳሜ ላይ ደረስኩኝ። የሽያጭና የገቢ ዝርዝር ስርዓት በሶፍትዌር መዘርጋት እንደሚገባ አመንኩኝ። እንዳውም ይሄ ለእኔ መልካም አጋጣሚ ነው ብዬ አሰብኩኝ። በወቅቱ ታዲያ ዲግሪዬን እየተማርኩኝ የራሴን ሶፍትዌር ሰርቼ ጨረስኩኝ።

ይህ ሶፍትዌር ኦዲዮና ቪዲዮ ያለው የሽያጭ ስርዓት ነበረው። ስለዚህ ሽያጭ ሲካሄድ ከኢንቬንተሪው ላይ እየቀነሰ ይሄዳል። በተመሳሳይ ሰዓት ደግሞ ምንያህል እንደተሸጠ ሪፖርቱን ማየት ያስችላል። ከዚህም ባሻገር ከስልክ ጋር አገናኘሁትና ባለቤቱ ሲደውል አጠቃላይ የሽያጭመጠንንለማወቅምሆነሌሎችዝርዝርመረጃዎችን የስልኩን ቁጥሮች በመጫን ማወቅ የሚያስችል ነበር። ለምሳሌ 1 ቁጥርን ሲጫን « የዛሬው ሽያጭዎ 100ሺ ብር ነው» ብሎ ማሽኑ በድምፅ ያነብሎታል። ይህንን ሶፍትዌር ሰርቼ ለባለቤቱ ሳቀርብለት በጣም ነው ደስ ያለው። እናም ያቺን የመጀመሪያዬን ሶፍት ዌር በስድስት ሺ ብር ነው ለሙዚቃ ቤት ባለቤቱ ሸጥኩለት። በዚህ ግን በጣም ደስተኛ ነበርኩኝ። ምክንያቱም ለኮሌጅ የምከፍለውን ገንዘብ ማግኘት ችያለሁ፤ ደግሞም በወቅቱ ያ ብር ብዙ ነበር።

በመቀጠልም ለሁለት ኩባንያዎች ሌሎች ሶፍትዌሮችን አዘጋጅቼ ሸጥኩኝ። ከዚያ በኋላ ግን የሚጎሉኝ ክህሎቶች ስለነበሩኝ ወደፊት መቀጠል አልቻልኩም። በእድሜዬም ደግሞ ገና በጣም ወጣት ነበርኩኝና ከብዙ ሰዎች ጋር መተዋወቅ ባለመቻሌ ደግሞ ምርቶቼን ማሳየት አልቻልኩም። ያም ሆኖ ግን የሰራኋቸው ሶፍትዌሮች እግርጌ አድራሻዬን እየፃፍኩ ስለነበር እሸጥ የነበረው ያንን የተመለከተው የሲመንስ ሶፍትዌር ቴክኖሎጂ ባለቤት ደወለልኝ። በዚያ ጊዜ እሱ ብቻ ነበር እንደዚያ አይነት ሶፍት ዌር እየሰራ ይሸጥ የነበረው። ከተቀጣጠርንበት ስፍራ ደርሼ ስደውልለት እንደእኔ አይነት በእድሜም ሆነ በአካል አነስ ያለች ልጅ ስላልጠበቀ ነው መሰል ሲመለከተኝ በጣም ነው የተገረመው። ቢሮው ወስዶ አስጎበኘኝ። የተደራጀና በርካታ ሰራተኞች ያሉት የሶፍትዌር ኩባንያ ሆኖ አገኘሁት። በመሆኑም የፈለከውን ያህል ክፈለኝና ከአንተ ጋር ልሰራ አልኩት።

የሚገርምሽ በወቅቱ እኔ የሰራሁትን ሲስተም ለማሳየት ስመጣ ላፕቶፕ ስላልነበረኝ ትልቁን ሲስተም ዩኒት ተሸክሜ ነው የሄድኩት። እሱ ግን ትጋቴን ስላየ በጣም ተደስቶ ቀጠረኝ። እናም ዲግሪዬን እየተማርኩኝ ጎን ለጎንም እዛ ኩባንያ ውስጥ ተቀጥሬ መስራት ጀመርኩኝ። ቀስ እያልኩኝ ክህሎቴን እያዳበርኩኝ ሌላም ድርጅት ተቀጥሬ ሰራሁ። ተቀጥሬ እየሰራሁ ሳለ ካሜሮን ሃገር ለሰባት ወራት ሄጄ የመስራት እድሉን አግኝቼ ነበር። ከዚያ ስመለስ ግን የራሴን ኩባንያ መክፈት እንዳለብኝ ወሰንኩኝ። ደግሞም እንደተመለስኩኝ በጣም ብዙ ሰዎች ሶፍትዌር እንድሰራላቸው ይጠይቁኝ ነበር። በዚያም በጣም ብዙ ገቢ ማግኘት ጀመርኩኝ። ደመወዜንም አጠራቅሜ ስለነበረ የራሴን ሥራ ለመስራት ዝግጅቴን አጠናቀቅኩኝ። በዚያ ጊዜ ነው ሃይብሪድ ዲዛይንን ያቋቋምኩት።

**አዲስ ዘመን፡- ታዲያ ”ራይድ‘ የተባለውን የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ለማቋቋም የተነሳሽበት አጋጣሚ ምን ነበር?**

**ወይዘሪት ሳምራዊት፡-** የራሴን ሥራ ስጀምር የትኛውም ሶፍትዌር ኩባንያ የሚሰራውን ሥራ ላለመስራት ለራሴ ቃል ገብቼ ነበር። ምክንያቱም በጣም በርካታ እድሎች እንዳሉኝ በመረዳቴ ነው። በተለይም የማያቸውን ችግሮች መፍትሔ የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ማፍለቅ ዋነኛ ትኩረቴ መሆን እንዳለበት ነው ያመንኩት። በመጀመሪያ ደረጃ አዲስ ምርት ማውጣቴ በራሱ ትልቅ እድል ነው። በሌላ በኩል የያዝኩትን ቴክኖሎጂ ለህብረተሰቡ ለማስተዋወቅና ህብረተሰቡ እስከሚረዳው ድረስ ሌላ ቴክኖሎጂ ለማምጣት ፋታ የሚሰጥ ሥራ ነው። ስለዚህ ከራይድ በፊት ሁለት ምርቶችን ለገበያ አቅርቢያለሁ። አንደኛው የጥገና ማኔጅመንት ሲስተም ነው።

ይህንን ሲስተም ለመስራት ምክንያት የሆነኝ የተለያዩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በጎበኘሁበት ጊዜ የነዚህ ፋብሪካዎች የጀርባ አጥንት የሆነውን ማሽን ለማስጠገን የሚያወጡት ጊዜ ወጪና ሁኔታን ለመረዳት ሞክሪያለሁ። እነዚህ ኢንዱስትሪዎች በዓመት አንድ ጊዜ ከወጣላቸው የጥገና መርሐ ግብር ውጭ ማስጠገን የማይችሉ መሆኑንም ለመታዘብ ሞክሪያለሁ። ዓመት ጠብቀው ጥገናውን የማያካሂዱ ከሆነ የምርት መቋረጥና አላስፈላጊ ወጪ ያጋጥማቸዋል፤ ባዘገዩ ቁጥር በደምበኞቻቸው ዘንድ ያላቸውም ተቀባይነት እየቀነሰ ይመጣል። ለምሳሌ በወቅቱ ቆዳ ፋብሪካዎች በየቀኑ ያጡት የነበረው እስከ 40ሺ ዶላር የሚደርስ ገንዘብ ነበር። ስለዚህ ይህንን የጥገና ጊዜ የሚያስታውሳቸው ሲስተም ያስፈልጋቸዋል።

ሌላው ችግር ደግሞ አንዱ ጠጋኝ በምን መንገድ? እንዴትና ምን አይነት ግብዓት ተጠቅሞ ጠገነው? የሚለው የጥገና ታሪክ የመፃፍ ልምዱ ያለመኖሩ ነው። ሌላኛውም መጥቶ ሲጠግን ተመሳሳይ ሁኔታ ነው ያለው። የጥገና ታሪኩ ቢኖር ግን ችግሮች በፍጥነትና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መፍታት ይቻላል። ይህ ሶፍትዌር መሰራቱ ድርጅቶቹ ለጥገና የሚያወጡትን ወጪ እስከ 75 በመቶ ድረስ ሊቀንስላቸው ይችላል። በተጨማሪም በእነዚህ ፋብሪካዎች ብዙ ጊዜ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ስላለ ብቻ አስቀድሞ የግብዓት ግዢ ይፈፀማል። ጥገና በሚደረግት ጊዜ በማከማቻ ውስጥ ያለውን ግብዓት መጠንና አይነት የሚያስታውሳቸው ሲስተም የላቸውም። በዚህ ምክንያት ብዙ አላስፈላጊ ወጪ የሚያወጡ ድርጅቶች መኖራቸውን ታዝቢያለሁ። እኔ የሰራሁት ሶፍትዌር እነዚህን ሁሉ ችግሮች የሚፈታላቸው ነበር።

ይህንን ችግር ይፈታል ብዬ የሰራሁትን ሶፍትዌር ለተወሰኑ ኩባንያዎች በነፃ ሁሉ ሰጥቼ ነበር። ብዙዎቹ ሲስተሙን ቢወዱትም ግን እኔን ማመን ከበዳቸው። ደግሞ ሶፍትዌሩ ጀምሮ በሽያጭም ሆነ ውል የምፈርመው እኔ መሆኔ ብዙ አላስደስታቸውም ነበር። አንዳንዶቹም ቅድሚያ ክፍያ ከከፉሉኝ በኋላ የምጠፋባቸው መስሏቸው የሰጉም ነበሩ። የሚገርምሽ ግን ባሉኝ ጊዜ እያቀረቡክ፤ ሲስተሙም በተሳካ ሁኔታ እየሰራና ምንም ሳያጎድል ህጋዊ ሰብዕና ኖሮኝ ሳለ ውል እንፈራረም ስላቸው ያፈገፍጉ ነበር። ልክ ሲስተሙ ሁለት ወር ሲሞላው ሲቋረጥባቸው ያለስምምነት መቀጠል እንደማልችል አሳወኳቸው። ያንን ደግሞ አቋርጬ ወደ ሌላ ምርት ማምረት ፊቴን

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ



አዞርኩኝ። ይህንን ሥራ ስጀምር ግን ተጨማሪ የሰው ኃይል የማይፈልግ በራሱ ገቢ የሚያመነጭ መፈለግ አለብኝ ብዬ አስብኩኝ። በዚያ መሰረት በአራት ወራት ውስጥ የአጭር መልዕክት የሎተሪ ሲስተም ዘረጋሁኝ። በነገራችን ላይ ሲስተሙን መሰረት በማድረግ ታላቁ ህዳሴ ግድብን ለማስተዋወቅ ጥያቄ አቅርቤ ነበር። ግን በአባይ ስም ምንም አይነት ሎተሪ መስራት አይቻልም ተባለና ተውኩት። በመቀጠል ደግሞ ብዙ የሴቶች ማህበራት ጋርም ሄጄ ነበር። አንዳንዶቹ ወንበርና ጠረጴዛዎቻቸው አቧራ የመታቸውና ሥራ የማይሰሩ ነበሩ። ለዚህ ምክንያት ደግሞ የበጀት ችግር እንደሆነ ነገሩኝ። በአጭር የስልክ መልዕክት ሎተሪ ድርጅታቸውን በማስተዋወቅ እኔ መንግሥት ከሚሰጠኝ 10 በመቶ ድርሻ አምስቱን ብቻ ወስጄ አብረን እንድንሰራ ብጠይቃቸውም አብሮኝ ለመስራት የደፈረ አልነበረም።

በመጨረሻ በሱባ መናገሻ ላይ ከጓደኞቼ ጋር ችግኝ በተከልኩበት ወቅት በአጋጣሚ ከመናፈሻው ሥራአስኪያጁ ጋር ስንነጋገር ድርጅቱ የሚተዳደረው እንጨትና ችግኝ እየሸጠ ብቻ መሆኑን፤ ከመንግሥትም ምንም አይነት ድጋፍ እንደማያገኙ ነገሩኝ። ይህ ሰው ስለአጭር የስልክ መልዕክቱ ሎተሪ ሳጫውተው አብሮኝ ለመስራት እንደሚፈልግ ነገረኝ። የዚያኑ ቀን አብሮኝ አዲስ አበባ መጥቶ ውክልና ሰጥቶኝ አብረን ለመስራት ተስማማን። በወቅቱ የሚያምንብኝ አንድ ሰው መገኘቱ ብቻ እጅግ አስደስቶኝ ነበር። ፕሮፖዛሉን ለብሔራዊ ሎተሪ ካስገባን ከአንድ ሳምንት በኋላ ጠርተውን ሁሉም ነገር ተጠናቆ ለህዝብ ሊለቀቅ ሲል በተመሳሳይ ሰዓት የህዳሴ ግድቡ ሎተሪ ይፋ ሊደረግ ስለሆነ ያንን ሎተሪ ማካሄድ እንደማንችልና ፍቃድ ሊሰጡን እንደማይችሉ ነገሩኝ። መጀመሪያም ቢሆን የአባይ ሎተሪ ሃሳብ አቅርቤ አልተቀበሉኝም፤ እንደገና አሳምኜ የሱባውን ፕሮጀክት ይዤ ስመጣ መከልከሌ እጅግ በጣም አሳዝኖኝ ነበር። ምክንያቱም ለእኔ በጣም ከባድ ነበር።

ከዚያ እንደወጣሁ ግን ከመንግሥት ጋር የማያገናኘኝና ፈቃድ የማይፈልግ ሌላ ሥራ መስራት እንዳለብኝ ራሴን አሳመንኩኝ። በመቀጠል ችግሮችን መፈለግ ጀመርኩኝ። አብረውኝ የሚሰሩትን ሁሉ በየዕለቱ የሚያጋጥማቸውን ችግር እንዲነግሩኝ እወተውታቸው ስለነበረ የታክሲው ችግር ጎልቶ ወጣ። እኔ ራሴ ማታ አምሽቼ ስወጣ ትራንስፖርት ማግኘት በጣም ነበር የምቸገረው። ከሌሊቱ ስድስትና ሰባት ሰዓት ላዳ ተከራይቶ መሄድ በጣም ያስፈራል። ብዙዎቻችን ደግሞ ታርጋ ይዘን አንገባም፤ በዚህ የተነሳ ብዙ ችግር የደረሰባቸው ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን። አንዳንዱም የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ሳይሆን ለሌላ አላማ የሚንቀሳቀስ ይሆናል። ያ ሁኔታ ብዙዎቻችንን ያስጨንቀን ነበር። በተለይ እኔ አምሽቼ ስሄድ በየደቂቃው የደረስኩበትን ስፍራ ለቤተሰቦቼ መልዕክት እልክ ነበር። ልክ እኔ የነበረኝን አይነት ስጋት ጓደኞቼ ላይ ነበር።

ከዚህ በመነሳት ሰውን የሚያስጨንቀውን ነገር የሚፈታ አንድ ኩባንያ ያስፈልጋል የሚል ድምዳሜ ላይ ደረስኩኝ። በተለይ አገልግሎቱን የሚሰጡት ሹፌሮች አድራሻና ማንነት በትክክል ታውቆና ሲስተም ውስጥ እንዲገባ አድርጎ ህብረተሰቡ አስተማማኝ የሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት አንድ ትልቅ እፎይታ ነው ብዬ አመንኩ። ምክንያቱም ችግር ቢፈጠር እንኳን ተጠያቂ የሚሆን ህጋዊ ተቋም መኖሩ ትልቅ ተቀባይነት ይኖረዋል። አዲሱን የራይድ ፕሮጀክቴን ለመስራት አራት ወር ገደማ ነው የፈጀብኝ። ሥራ ስጀምርም በ40ሺ ብር ይዤ ነው የተነሳሁት። ከአራት ወር በኋላ ራይድን ለህዝብ ይፋ ያደረግነው በአጭር የስልክ መልዕክት ነው። መጀመሪያ ላይ እኔ ፊት ለፊት አልወጣሁም። በስልክ ሰይፉ ፋንታሁን ጋር ደውዬ ስለሥራችን ነገርኩት። በስልክ ብቻ ታክሲ ጠርቶ አስተማማኝና ደህንነቱ በተረጋገጠ መልኩ አገልግሎት ማግኘት እንደሚቻል አስረዳሁት። በጣም ደስ አለውና ፕሮግራሙ ላይ አቀረበው።

ወዲያውኑ ደንበኞች የአገልግሎት ጥያቄ እየተበራከተ መጣ። እውነቱን ለመናገር መጀመሪያ ላይ አሽከርካሪው አይመዘገብም ብዬ ነበር የሰጋሁት። መጀመሪያ ቀን ሰባት ተሽከርካሪ ሲገባ በሶስተኛው ቀን 400 ተሽከርካሪ ደረሰ። በዚህ መልኩ ራይድ አሁን ከ43ሺ በላይ ተሽከርካሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል።

**አዲስ ዘመን፡- የትራንስፖርት አገልግሎቱ አዲስ ከመሆኑ ጋር ያጋጠመሽ ችግር ምን ነበር?**

**ወይዘሪት ሳምራዊት፡-** እንግዲህ ራይድ ቶሎ ተቀባይነት ቢያገኝም በመሃል ግን ተግዳሮቶች አልነበሩም ማለት አይደለም። የመሰረተ ልማት ችግር ነበረ፤ በተለይ የኢንተርኔት አገልግሎት መቆራረጥ ጉዳይ ሥራችን ላይ ትልቅ እንቅፋት ፈጥሮብናል። በወቅቱ ከነበሩት ከኢትዮ-ቴሌኮም ሥራአስፈፃሚ ጋር ከተነጋገርን በኋላ ግን በአፋጣኝ ጥገና ተደርጎልን ሥራችንን በተቀላጠፈ ሁኔታ ማካሄዳችንን ቀጥለናል። ከሁሉ በላይ ግን በመገናኛ ብዙሃን ድርጅታችንን ለማስተዋወቅ የምንከፍለው ክፍያ ከፍተኛ መሆኑ እንደጀማሪ ድርጅት እጅግ ተፈታትኖን ነበረ። ለረጅም ጊዜ ደግሞ ለአሽከርካሪዎች ለማስተዋወቅና ስልጠና ለመስጠት ከፍተኛ ወጪ እያወጣን ስለነበርና ገቢም እያገኘን ስላልነበር የግድ ባለሃብቶችን ማሳተፍ እንደሚገባን አመንን። ግን በሥራው አምኖበት ከእኛ ጋር ተባብሮ ለመስራት የሚፈልግ ባለሃብት ማግኘት ሌላው ፈታኙ ጉዳይ ነበር።

በተለይ ሌላ ጀማሪ ኩባንያ ላይ ኢንቨስት የማድረጉ ባህል በእኛ ሃገር አልተለመደም። ሁለተኛ ደግሞ ቴክኖሎጂ ላይ ኃላፊነቱን ወስዶ መዋለንዋዩን ማፍሰስ የሚፈልግ ሰው ማግኘት ከባድ ነበር። ምክንያቱም ቶሎ ትርፍ የሚገኝበት ዘርፍ ባለመሆኑ ነው። ባንኮች ሳይቀሩ በኮላተራልም ቢሆን ማበደር አይፈልጉም። ማይክሮ ፋይናንሶችንም ስንጠይቅ ከ70 ሺ ብር በላይ ሊያበድሩን እንደማይችሉ ነው የነገሩን። ይህ ብር ደግሞ ለእኛ ምንም ሊሰራልን አይችልም። የሚገርምሽ ትልልቅ ኩባንያዎች ሳይቀሩ ቶሎ ትርፍ የሚሰጣቸው ካልሆነ አብረው ለመስራትም ሆነ ለመደገፍ አይፈልጉም። ስለዚህ ውጭ የሚኖሩት የተለያዩ ሰዎች ጋር በመፃፃፍ ስለኢንቨስትመንቱ ማስረዳትና አብረውኝ እንዲሰሩ ወደ መጠየቁ ገባሁ። ከፃፍኩላቸው ሰዎች ውስጥ አንድ ካናዳ ውስጥ የሚኖሩ ሰው ብቻ ነበር ምላሽ የሰጡኝ። እኚህ ሰው ደግሞ በቴክኖሎጂ ላይ 25 ዓመት የሰሩ መሆኑንና ሃሳቤን እንደወደዱት ገለፁልኝ። ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ተገናኝተን አወራን፤ ከጥቂት ቀናት በኋላ ግለሰቡ ቃላቸውን ጠብቀው ያለምንም ህጋዊ ስምምነት በአካውንቴ የተወሰነ ገንዘብ አስገቡልኝ። እኔም ከብዙ ጥረት በኋላ እምነት የሚጥልብኝ ሰው በማግኘቴ የዚያኑ ቀን ራይድን ትልቅ ድርጅት አድርጌ ሰዎቹን ተጠቃሚ ለማድረግ ለራሴ ቃል ገባሁኝ።

ሁለተኛውም ኢንቨስተር በተመሳሳይ መልኩ ድጋፍ አደረገልንና በጣም በትንሽ ብር ትልቅ ድርጅት አደረግነው። ለዚህ ስኬት የበቃሁት በራሴ ብቻ ሳይሆን እንዳልኩሽ የእነዚህ ግለሰቦች ድጋፍ በመታከሉና ጠንካራ የሆኑ ሰራተኞች ስላሉኝ ጭምር ነው። በተለይ ከትንስፖርት ሚኒስቴር ጋር በነበረው ውዝግብ ቢሯችን ሲታሸግ በረንዳ ላይ ሁሉ ቁጭ ብለው ነበር ሲሰሩ የነበሩት። አሁን ከእኛ በኋላ በርካታ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ተበራክተዋል። በዚህ ደስተኛ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ የድርጅትሽ አቅም ምንሳይ ደርሷል? ስምን ያህል ዜጎችስ የሥራ እድል መፍጠር ተችሏል?**

**ወይዘሪት ሳምራዊት፡-** ራይድ ዛሬ ለ43ሺ ተሽከርካሪዎች የሥራ እድል ፈጥሯል። 500 ቋሚ ሰራተኞች አሉን። አብዛኞቹ ሴቶች ሲሆኑ ቁጥራቸው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ደግሞ ገና ከዩኒቨርሲቲ እንደተመረቁ የገቡ ናቸው። ይህ ሁሉ በሰባት ዓመታት ውስጥ የተከሰተ ነገር ነው። ይሄ ሁሉ የሆነው ደግሞ ቴክኖሎጂን በማቀላጠፍ ነው። ለእነዚህ ሁሉ አሽከርካሪዎች የሥራ እድል ተፈጠረ ማለት በሥራቸው የሚተዳደሩ የቤተሰብ አባላትን በሙሉ ነው ተጠቃሚ የሚያደርገው። ብዙ አሽከርካሪ ኑሮውን ከመደጎም አልፎ ተጨማሪ ሃብት አፍርቷል፤ ሌላ መኪና ገዝቷል፤ የራሳቸውን ድርጅት ከፍተዋል። ከሁሉ በላይ በዚህ ድርጅት ውስጥ የሚሰራው አብዛኛው ወጣት መሆኑ ለሌላውም ወጣት መነሳሳት ፈጥሮለታል ብዬ አምናለሁ። ማንኛውም የሥራ ፈጠራ ሃሳብ ያለው ወጣት ከዜሮ ተነስቶ መለወጥና ማደግ እንዲችል አርዓያ ሆነዋል። በአጠቃላይ ራይድ የብዙዎችን አይን ገልጧል ብዬ አምናሁ። ከዚህ ባሻገር ማህበረሰቡ የሥራ ፈጠራ አማራጮችን እንዲመለከት የተለያዩ ስልጠናዎችን እንሰጣለን።

**አዲስ ዘመን፡- የእናንተ ድርጅትን ተከትሉ ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ ኩባንያዎች መከፈታቸው ለእናንተ ድርጅት ስኬት ነው ወይስ ተግዳሮት?**

**ወይዘሪት ሳምራዊት፡-** ለእኔ ተመሳሳይ ድርጅቶች መከፈታቸው ተግዳሮት ወይም ስጋት ሊሆንብኝ አይችልም። ምክንያቱም ራይድ አሁን ያለበት ቦታ ላይ ለመድረስ ብዙ መንገድ መጓዝ ጠይቆታል። ይህም በመሆኑ አሁን ለሚከፈቱት ድርጅቶች መንገድ ጠርገናል። በተለይም ከመንግሥት ድርጅቶች ጋር መጋጨት ቀላል ነገር አይደለም። በመሰረቱ እኔ ይህንን ሥራ ስንጀምር ከመንግሥት ትልቅ ድጋፍ አገኛለሁ ብዬ ነበር። ምክንያቱም ወጣት ሥራ ፈጣሪዎችን ያበረታታሉ፤ ሴቶችም ይደገፋሉ የሚል መርህ ስላለ ነው። ወይዘሪት ሳምራዊት ከዚህ አንፃር ሁለቱንም ታሟላለች። ስለዚህ እንዲህ አይነት ፈታኝ ሁኔታ ያጋጥመኛል ብዬ አልገመትኩም ነበር። ሲመጣ ግን በዚህ ምክንያት ተስፋ ቆርጬ ለመቀመጥ አላማ አልነበረኝም። የእኔ ራዕይ በቴክኖሎጂ ገና ኢትዮጵያን ማስተዋወቅ ነው።

በአሁኑ ወቅት ወደ ምስራቅ አፍሪካ ሥራችንን በማስፋት የሃገራችን ገፅታ መገንባት ነው አልመን እየሰራን ያለነው።እኛ ኢትዮጵያውያን በሩጫና በቡና ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ መታወቅ ያለብን በቴክኖሎጂም መታወቅና የሃገራችንንም ስም ማስጠራት መቻል አለብን። በአጠቃላይ የእኔ ራዕይ ገና በአፍሪካ ጭምር ገናና የሆነ የቴክኖሎጂ ኩባንያ መፍጠር በመሆኑ አሁን ላይ ተመሳሳይ ድርጅቶች መከፈታቸው ለእኔ ስጋት አልሆነብኝም፤ ከአላማዬም ወደኋላ አያስቀረኝም። ገና በጣም ትንሽ ነገር ነው የሰራነው፤ ብዙ አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችንና ቴክኖሎጂዎችን እያሻሻልን ነው የምንሄደው።

በነገራችን ላይ አዲስ አበባ ውስጥ ካለው ችግር ውስጥ ገና 15 በመቶውን ነው ተደራሽ እያደረግን ያለነው። ይህም ቢሆን አውቶብስና ሌሎችም ታክሲ አገልግሎት የሚሰጡትንም ጨምሮ ነው። ስለዚህ ቀሪውን 85 በመቶ የሚሆነውን ህዝብ እንዴት ማገልገል እንዳለብን ነው ማሰብ ያለብን። የምፈልገው ግን ጤናማ የሆነ የሥራ ውድድር እንዲኖር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ግን ከእናንተ በኋላ የተፈጠሩ አንዳንድ ድርጅቶች በአገልግሎት በቅልጥፍናም ሆነ በቴክኖሎጂ ሥራቸውን አስፍተው የያዙ አሉ፤ በዚህ ረገድ ራይድ ምን አስባል?**

**ወይዘሪት ሳምራዊት፡-** በመሰረቱ አሁን ላይ ሌሎቹ ኖሯቸው ራይድ የሌለው አሰራርም ሆነ ቴክኖሎጂ የለም። ልክ እንደሌላው ሁሉ እኛም የኮርፖሬት ወይም የብድር አገልግሎት የምንሰጣቸው ድርጅቶች አሉን። አሁን ላይ ከ500 በላይ የሚሆኑ የኮርፖሬት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አሉን። ለምሳሌ ብጠቅስልሽ የእስራኤል፤ የእንግሊዝ ኤምባሲን፤ መሬት አስተዳደር ማንሳት እንችላለን። ይሄ ቀድሞም የምንሰጠው አገልግሎት ነው። ክፍተት አይቶ መፍትሄ የሚሆን አሰራር ይዞ መምጣት የቢዝነሳችን መርሆም ስለሆነ በዚህ ረገድ ስጋት የሚሆንብን ነገር አለ ብዬ አላምንም። እርግጥ ነው ከኑሮ ውድነቱ፤ የነዳጅ ዋጋ በየእለቱ ከመጨመሩና መንግሥትም ለዘርፉ ድጎማ የማያደርግ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አሽከርካሪዎቹ ላይ የሚፈጠር ጫና መኖሩን እንገነዘባለን። የእነሱን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ከመንግሥት ጋር ከመከራከሩ ጎን ለጎን ገቢያቸው የሚጨምርበት መንገድ እየሰራን ነው ያለነው።

ከሰሞኑ እንዳያችሁት ደግሞ ከኢትዮ-ቴሌኮም ጋር በመተባበር የሲም ካርድ ሽያጭ እንዲሰሩ ማድረግ ጀምረናል። ሲም ካርድ በሸጡ ቁጥር የሚያገኙት ገቢ በተጨማሪ ኮምሽን እንዲያገኙ አድርገናል። ከዚህም ባሻገር የቴሌ ብር ወኪል ናቸው፤ ወኪል በመሆናቸው ትራንዝአክሽን በተካሄደ ቁጥር የሚያገኙት ኮምሽን አለ። ከአስር በላይ በሚሆኑ ሆስፒታሎች የጤና አገልግሎት በቅናሽ እንዲያገኙም ምቹ ሁኔታ ፈጥረናል። በሥራ ላይ አደጋ ቢያጋጥማቸው ቅድሚያ ክፍያ ሳይጠየቁ የጤና አገልግሎት የሚያገኙበትም እድል ተመቻችቶላቸዋል። አንድ ዓመት ያህል የቆጠቡ አሽከርካሪዎች መኪና የሚገዙበት ስርዓት ከባንኮች ጋር በመግባባት ተበጅቶላቸዋል። ግብር መክፈል የተቸገሩትንም እኛ እናግዛለን።በቅርቡ እቁብ የተሰኘ ፕሮጀክት ይፋ እናደርጋለን። ይህንን የቁጠባ ዘዴ ተጠቅመው ራሳቸውን እንዲለውጡ የሚደረግ ነው የሚሆነው። ይህም የሚያሳየው አሽከርካሪዎቻችን ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው እንዲሰሩ የተደረገውን ጥረት ነው። ከሁሉ በላይ በኮድ ሶስት የታክሲ አገልግሎት ህጋዊ ማዕቀፍ እንዲኖረው በማድረግ ራይድ ያበረከተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። ከመንግሥት ጋር ታግለን ህጋዊ አሰራር ባይዘረጋ ኖሮ ዛሬ ላይ እኛም ሆነ ሌሎቹ ትራንስፖርት ሰጪ ድርጅቶች ባልኖሩ ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- እንዳአንቺ እውቀት ኖሯቸው መንገዱ ስለጠፋባቸው ሴቶች ምን መልዕክት ማስተላለፍ ትፈልጊያለሽ?**

**ወይዘሪት ሳምራዊት፡-** የእኛ ባህል ሴትን በጣም የሚጫን ነው። እኔ ግን ፈጣሪ ይመስገን በጣም ከጎኔ ሆነው ሲረዱኝ የቆዩ ቤተሰቦች ናቸው ያሉኝ። ግን ሁሉም ነገር ቤተሰብ ጋር ይቀራል ማለት አይደለም። ወጣ ስትይ ማህበረሰቡ ቶሎ ሊቀበልሽ ይቸግረዋል። እኔም እንዳልኩሽ ምርቴን ይዤ ስወጣ ያለማመን ነገር ነበር። ይህ በራሱ አንድ ተግዳሮት ነበር፤ ግን አንድ የራሴ የሆነ መርህ አለኝ፤ ይኸውም ችግርን በራሱ እንደአንድ እድል መጠቀም ነው። ችግር ከመጣ ራሴን ሞግቼ ካሸነፍኩም ሆነ ከተሸነፍኩኝ ተምሪያለሁ ነው የምለው። የሕይወት ተሞክሮዬም እያደገ ነው የሚመጣው። ይህ ማለት ግን ሁልጊዜ ችግር እያጋጠመኝ እቅዴ እየከሸፈ መኖር አለብኝ ማለት አይደለም። ግን የሰራኋቸውን ስህተቶች ደግሞ እንዳልሰራ ጥንቃቄ አደርጋለሁ፤ ተምሬበት ነው የማልፈው። በሌላ በኩል ለራሴ ግልፅ መሆን እንዳለብኝ አምናለሁ፤ ራሴን አልዋሸውም፤ ጥንካሬዬን እንደማውቀው ሁሉ ጉድለቴንም ጠንቅቄ ነው የማውቀው። ከእኔ በተሻለ ጠንካራ ስብዕና ያላቸውን ሰዎች አናግራለሁ፤ እጠይቃለሁ። በየቀኑ ራሴን እያሳደኩ ነው የምመጣው።

ሌላኛው ትልቁ ነገር ደግሞ ሁለቱም ፆታ እኩል ነው ብዬ አምናለሁ። እኛም እንደወንዶቹ የሚያስብና የሚሰራ ጭንቅላት አለን። ስለዚህ ከእነሱ እኩል የፈለግነው ቦታ ለመድረስ የሚያግደን ነገር አይኖርም። አስቀድሜ እንዳልኩሽ ቀደም ብዬ በሰራኋቸው ሁለት ሥራዎች ማህበረሰቡ አልተቀበለኝም፤ ሶስተኛውን ስጀምር ግን ለተወሰነ ጊዜ ራሴን ደብቄ ነበር። ያ ደግሞ የስትራቴጂ አካል ነው እንጂ ሽንፈት አይደለም። ምርቴ ከታወቀና ከተለመደ በኋላ የእኔ ማንነት ሲታወቅ ማህበረሰቡ ለመቀበል አላዳገተውም፤ እኔም አልታገልኩም። ስለዚህ የተለያዩ ስትራቴጂዎች እየሞከርን ራሳችንን ማሳደግ አለብን። በሥራችን ስኬታማ ለመሆን ራዕያችን ላይ ግን ሁልጊዜ ትኩረት ማድረግ አለብን።

**አዲስ ዘመን፡-ስነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ ሳመሰግን እወዳለሁ።**

**ወይዘሪት ሳምራዊት፡- እኔም አመሰግናለሁ።**

# ማህደረ ጤና

# የኩላሊት እጥበት አገልግሎትን በአምስት እጥፍ የሚያሳድገው ማዕከል

**እፀገነት አክሊሉ**

በኢትዮጵያ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የኩላሊት ታማሚ የበዛ ይመስላል። በቅርብ የምናውቃቸው ሰዎችም የኩላሊት ህመም እንዳጋጠማቸውና ህክምና እንደሚያስፈልጋቸው፤ ወይም ህክምና እየተከታተሉ እንደሆነ መስማትም የተለመደ ሆኗል። ምን አዲስ ነገር ተፈጥሮ ይሆን? የተፈጠረውን አዲስ ነገር፣ ወይንም ደግሞ ሰዎች ሁሉ የኩላሊት ህመም ታማሚዎች የሆኑበትን ምክንያት ከማንሳታችን በፊት "የኩላሊት ተግባር ምንድን ነው?" የሚለውን እንመልከት።

አስቀድመን የኩላሊት ዋናው ተግባር በሰውነታችን ውስጥ ያለውን ተስተካክሎት (ሚዛን) መጠበቅ መሆኑን በመሰረታዊነት መያዙ ተገቢ ነው።

ብዙ ሰው ኩላሊትን ሲያስብ ሽንት ነው ትዝ የሚለው። ነገር ግን ኩላሊት ከዚያ ባሻገር ብዙ ተግባራት አሉት። ለምሳሌ በሰውነታችን ውስጥ የሆርሞን ምርት፣ የንጥረ ነገሮች ምርትና ምጣኔ፣ የሰውነት ፈሳሽን ምጣኔ እና ሌሎች በርካታ ተግባራትን ከሚያከናውኑት የሰውነት ክፍሎች መካከል ኩላሊት ዋናው ነው ማለት ይቻላል። በዚህም መካከልም ኩላሊት ይህን የተስተካክሎት ሥራ ለመሥራት ተፍ ተፍ እያለ ሽንትንም አጣርቶ ተገቢውን የማስወገድ ሥራም እንደሚሰራ ልብ ማለት ይገባል።

ኩላሊት በሚያከናውነው የሰውነትን ተስተካክሎት (ሚዛን) የመጠበቅ ሂደት ውስጥ ሆኖ ደግሞ ተመገብን። ምግብ ኃይል ሆነ፣ ህዋሳት የሚያስፈልጋቸውን ያህል ወሰዱ፤ ኩላሊት የቀረውን ተረፈ ምርት በአንድ መልኩ ይሰበስብና ማጣሪያዎቹን ተጠቅሞ ወደ ማስወገጃ ክፍል ይልካል። ተረፈ ምርቱ በኩላሊት ሚሊዮን ወንፊቶች በኩል ተጣርቶ ያልፍና ከፈሳሽ ጋር ወደ ፊኛ ክፍል ይላካል። እዚያ ከሌሎች ፈሳሾች ጋር ተደባልቆ ሲወጣ ነው ሽንት ሸናን የምንለው።

ጎንና ጎናችን ሥር የተሸጎጡት ሁለቱ ኩላሊቶቻችን የባቄላ ቅርጽ ነው ያላቸው። በመጠን ደግሞ የኮምፒዩተር "ማውዝ" ያክላሉ ይላሉ ባለሙያዎች፤ ከታችኛው የጎድን አጥንቶቻችን ውሽቅ ብለው በግራና በቀኝ ጎናችን የሚገኙት ኩላሊቶቻችን ፈሳሽ ከማመጣጠን እና ተረፈ ምርት ከማስወገድ ሌላ ቫይታሚኖችንና ሆርሞን፤ ካልሺየምና ፎስፌት የሚባሉ ንጥረ ነገሮችን ማምረትና ምጣኔያቸውን የመቆጣጠር ሥራም ይሠራሉ።

በአጠቃላይ ኩላሊት፣ የንጥረ ነገር ሚዛን ማስተካከል፤ ተረፈ ምርት ማስወገድ፣ የደም ማነስ ችግር እንዳይኖር ክትትል ማድረግ፣ የደም ግፊትና የስኳር መጠንም በተዘዋዋሪ የመቆጣጠር ብርቱ ሥራ የሚሠራ እጅግ ጠቃሚ ክፍል ነው።

ኩላሊት ባተሌ ነው። ፋታ የለውም። ቀን ከሌት ይደክማል። ልክ 24 ሰዓት እንደሚሠራ የልብስ ማጠቢያ (ላውንደሪ) ማሽን አድርጋችሁ አስቡት። ለምሳሌ በእያንዳንዱ ኩላሊት ውስጥ በየ30 ደቂቃው ሙሉ ደማችን አንድ ዙር ይታጠባል። 5 ሊትር ደም ማለት ነው። ተረፈ ምርቱን የሚያስወግደው በዚህ የአጠባ ሂደት መሆኑን ደግሞ ለጽሁፉ የተጠቀምንባቸው የተለያዩ ጽሁፎች ያመለክታሉ።

ልባችን ከሚረጨው ደም ውስጥ 20 ከመቶ በቀጥታ ወደ ኩላሊታችን የሚሄደው ያለ ምክንያት አይደለም። ኩላሊት ከባድ ሥራ ስለሚሠራ ነው። ደም ይፈልጋል። በሙሉ ሰውነታችን ከሚዞረው ደም 20 ከመቶ በቀጥታ ወደ ኩላሊት የመሄዱ ነገር የኩላሊትን ባተሌነትን ይጠቁማል።

ይህ ባተሌ የሆነው የሰውነት ክፍላችን ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ይታመማል። የእሱ መታመም ደግሞ የሰውነታችንን ሚዛን እንዳይጠበቅ ከላይ ያነሳናቸው ሥራዎች በሙሉ በአግባቡና በስርዓቱ እንዳይከወኑ በማድረግ ለህመም ይዳርገናል። ታዲያ ኩላሊታችን ችግር ውስጥ ስለመግባቷ በምን ማወቅ እንችላለን?

ኩላሊት አብዛኛውን ጊዜ ጽኑ የኩላሊት ህመም ላይ ካልደረሰ በስተቀር በጠቅላላው ምልክት አያሳይም። ይህ ደግሞ ሰዎች ችግራቸውን በቶሎ እንዳያውቁት ከማድረጉም በላይ ህመሙ ጽኑ ሁኔታ ላይ ሲደርስ ማገገሙ ከባድ እንዲሆን ያደርገዋል።

ብዙ ሰዎች ኩላሊታቸው መታመሙን የሚያውቁት ለሌላ በሽታ ሕክምና ሆስፒታል ሲሄዱ ነው። ሥር የሰደደ ወይም ጽኑ የኩላሊት ህመም ደረጃ ላይ ሲደረስ ግን ኩላሊት በጎ እንዳልሆነ በምልክቶች ማየት ይቻላል። ለምሳሌ እግር ያብጣል፣ ጠዋት ጠዋት ዓይን ያብጣል፤ የፊት ማበጥ ሊያጋጥም ይችላል፣ ቶሎ የድካም ስሜት ይሰማል፣ መጫጫን ያጋጥማል፣ በዚህ መካከል የአጥንት መሳሳትም ሊኖር ይችላል። ይህ የሚሆነው ብዙውን ጊዜ ኩላሊት ፈሳሽ ማመጣጠን ሥራው ሲስተጓጎልበት መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።

በሌላ በኩልም የምግብ ፍላጎት ማጣት፣ የድካምና የማቅለሽለሽ ስሜት መሰማት፣ የደም የግፊት መጠን መጨመር፣ የደም ማነስ ምልክት መታየት ተጨማሪዎቹ በመሆናቸው እነዚህ ምልክቶች ሲታዩ ኩላሊት የከፋ ደረጃ እንደደረሰ ተገንዝቦ ወደ ህክምና ተቋም መምጣትም ያስፈልጋል።

ኩላሊት ዝምተኛ ነው። ወዲያው አክሙኝ አይልም። ይህ ሁኔታ ደግሞ ያዘናጋል። ስለዚህ ማንኛውም ሰው ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ኩላሊቱን ቢታይ ጥሩ ስለመሆኑም ባለሙያዎች ይመክራሉ።

በተለይም የደም ግፊት፣ ስኳር፣ ከፍተኛ ክብደት (ውፍረት)፣ ሌላ ተጓዳኝ ህመም ያለባቸው ሰዎች ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ለኩላሊት ህመም ተጋላጭ ስለሚሆኑ ባይታመሙ እንኳን በየጊዜው ኩላሊታቸውን ቢታዩ ኋላ ከሚመጣው ችግር መዳን ይቻላል።

ለብዙዎቻችን ተራ የሚመስለንን ግን ለኩላሊት ጤናማ መሆን እጅግ በጣም ወሳኝ የሆነው ነገር ሽንት እንደመጣ መሽናት ነው። ሽንት ስንቋጥር ኩላሊት ላይ አላስፈላጊ ጫና እንፈጥራለን። ጫናው እየበዛ ሲሄድ ደግሞ የኩላሊት መድከምን ያመጣል።

ሌላው ለኩላሊት በሽታ ተጋላጭ የሚያደርገን ነገር አመጋገባችን ነው። የከፋ የኩላሊት ህመም ሲኖር የሚመከሩ የአመጋገም ዓይነቶች አሉ። ምክሩ መምጣት ያለበት ግን ከሐኪም ነው። ነገር ግን በደፈናው ፕሮቲን ለኩላሊት ጥሩ አይደለም ብሎ ከመመገብ መራቅ ለሌላ ችግር ለመጋለጥ መወሰንም ስለመሆኑ ማወቅ ያስፈልጋል። ሁል ጊዜ ጠቆር ያለ ቢጫ ቀለም ያለው ሽንት የምንሸና ከሆነ ራሳችንን 'በቂ ውሃ እየጠጣሁ ነው ወይ?' ብለን መጠየቅ አለብን።

ከምንሸናው ሽንት የሚያመጣው ጠረን ከወትሮው የተለየ ከሆነና ጠንከር ካለ ምናልባት የአንዳች ኢንፌክሽን ምልክት ስለሚሆን ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል። በተለይ ሴቶች በዚህ ረገድ ለኢንፌክሽን ስለሚጋለጡ ሽታውን በተለየ ትኩረት ሊያጤኑት ይገባል ።

ብዙ ሰው ውሃ ባለመጠጣት ይታመም ይሆናል እንጂ ብዙ ውሃ በመጠጣቱ ችግር ላይ የሚወድቅ ሰው እምብዛም የለም፤ በመሆኑም በአማካይ በቀን ከ2 እስከ 3 ሊትር ውሃ እንድንጠጣ ይመከራል። ይህን መጠን በአንድ ጊዜ መጠጣት ላይኖርብን ይችላል።

ይህ እንዳለ ሆኖ በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአዲስ አበባ ዋና ዋና ጎዳናዎች ላይ የኩላሊት ህመምተኞችን እያስቀመጡ "የእርዳታ እጃችሁን" ዘርጉ ማለት እየተለመደ ነው። በሌላ በኩልም በቤተሰብ፣ በጓደኛ በቅርብ በምናውቃቸው ሰዎች ላይም የኩላሊት በሽታ እየተከሰተ ይገኛል፤ ለምን እንዲህ በዛ የሚለው ነገር እራሱን የቻለ ጥናትን የሚፈለግ ቢሆንም ሁለት ምክንያቶች ያሉ ግን ይመስላል። አንዱ የአኗኗር ዘይቤያችን መቀየሩ ሲሆን ሌላው ደግሞ የምርመራ አቅማችን መጨመሩ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

በመገናኛ አካባቢ በመኪና ውስጥ ቁጭ አድርገዋት እርዳታ እየተሰበሰበላት ያገኘኋት ወጣት ሀቢባ መሃመድ የኩላሊት ህመም እንዳጋጠማት ካወቀች ቆየት ብላለች። እናም ብዙ ህክምናዎችን አድርጋለች። አሁን በግል ሆስፒታልም የኩላሊት እጥበት (ዲያሊሲስ) ህክምና በመከታተል ላይ ናት። ነገር ግን ከእለት እለት ችግሯ እየባሰ፤ እሷም ለእጥበቱ የምታወጣው ገንዘብ እያጣች በመምጣቷ ነው ጎዳና ላይ ለመውጣት የበቃችው።

"የኩላሊት በሽታ እጅግ ከባድ፤ ነው ለማንም አይስጠው" የምትለው ሀቢባ እሷ ኩላሊቷን ከመታመሟ በፊት ከቤተሰቦቿ ጋር በንግድ ሥራ እንደምትተዳደርና ስለህመሙ ምንም አይነት ግንዛቤ እንዳለነበራት፤ በሽታው እንዳይከሰትባትም ያደረገችው አንዳችም ጥንቃቄ አለመኖሩን ትናገራለች።

አሁንላይቤተሰቦቿእሷንለማዳንብዙመከራእንዳዩና ያላቸውን ጥሪት በሙሉ አሟጠው መጨረሳቸውን ገልጻ በተለይም ህክምናው በመንግሥት ሆስፒታል እንደልብ አለመገኘቱ እሷንና መሰሎቿን ከመኖር ወደ አለመኖር እያሻገራቸው ስለመሆኑ ትናገራለች።

አቶ ጌታሁን አበበም በተመሳሳይ የኩላሊት ህመምተኛ ናቸው። በእድሜያቸው ወደ ሽምግልናው እየደረሱ ያሉት አባት ለዚህ ህመም ከመዳረጋቸው በፊት ደም ግፊትና ስኳር እንደነበራቸው ይናገራሉ። አሁን የኩላሊት ህመሙ ሲጨመር ግን ኑሮን ፈታኝ እንዳደረገባቸውና በዚህ ደግሞ እሳቸው ብቻ ሳይሆኑ መላ ቤተሰባቸው እየተፈተነ መሆኑን ያብራራሉ።

እድል ገጥሞኝ ህክምናዬን በጳውሎስ ሆስፒታል ነው የምከታተለው ያሉት አቶ ጌታሁን እንደሳቸው እድል ሳያገኙ በግል ሆስፒታል ዲያሊሲስ እየተሰሩ ጥሪታቸውን የሚጨርሱ ሰዎች በጣም እንደሚያሳዝኗቸው የመንግሥት ሆስፒታሎች የችግሩን አሳሳቢነት ተረድተው አገልግሎቱን ለሁሉም ተደራሽ ማድረግ ቢችሉ በማለት ይጠይቃሉ።

አሁን "በምኒልክ ሆስፒታል አዲስ የኩላሊት ህክምና ማዕከል ተከፈተ" ሲባል ሰምቻለሁ ያሉት አቶ ጌታሁን ይህ ሁኔታ ምንም እንኳን እሳቸውን የሚጠቅማቸው ባይመስላቸውም ለሌሎች፤ በተለይም ለወጣቶች ትልቅ ችግር ፈቺ እንደሚሆን ተናግረዋል።

የኩላሊት እጥበት ተጠቃሚዎች በመድሃኒት ዋጋ ንረት እንዲሁም በግል የህክምና ተቋማት የተጋነነ ዋጋ ለችግር እየተጋለጡ መሆኑን የተረዳው መንግሥትም፤ በመንግሥት ሆስፒታሎች ይሰጥ የነበረውን የኩላሊት እጥበት አገልግሎት በአምስት እጥፍ የሚያሳድግና ለታካሚዎች ትልቅ እፎይታን የሚሰጥ "የኩላሊት እጥበት ማዕከል" በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል አሰርቶ፤ ባሳለፍነው ሳምንት አስመርቋል።

ማዕከሉ በተመረቀበት ጊዜም የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ እንዳሉት የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ አባላት እንደ አዲስ ሲዋቀሩ ከተሰጣቸው ኃላፊነቶች መካከል አንዱ፤ በተለይም ተላላፊ ባልሆኑ እንደ ኩላሊት ባሉ ህመሞች የሚሰቃዩ፣ ገቢያቸው አነስተኛ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ የሚያደርጉ ሥራዎችን መስራት ነው።

የኩላሊት በሽታ ከእለት እለት ቁጥሩ እየጨመረ መምጣቱን የተናገሩት ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የኩላሊት እጥበት ህክምናውም በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሰዎች ላይ የሚያደርሰውን ጫና ለመቀነስ የከተማ አስተዳደሩ ባለፉት ሁለት ዓመታት ድጎማ ሲያደርግ መቆየቱን ተናግረዋል።

አገልግሎቱ በሶስት የመንግሥት ተቋማትና የግል ሆስፒታሎች እየተሰጠ ያለ ቢሆንም፤ አገልግሎቱ በቂ ባለመሆኑ የዚህ ማዕከል መከፈት በከተማዋ ሲሰጥ የቆየውን የኩላሊት እጥበት ህክምና በአምስት እጥፍ የሚያሳድገው መሆኑን ተናግረዋል።

ከተማ አስተዳደሩ የችግሩን አሳሳቢነት ተረድቶ ማዕከሉን የገነባ ሲሆን፤ ተቀማጭነቱን አሜሪካን አገር ያደረገው የአብ ሜዲካል ሴንተር ደግሞ 30 የኩላሊት ማጠቢያ ማሽኖችን ከነአስፈላጊ ግብዓቶቻቸው አምጥቶ በመግጠም አገልግሎቱ በፊት ከነበረበት ወደ ላቀ ደረጃ እንዲደርስ አድርጓል ነበር ያሉት። በቀጣይም ህንጻው የኩላሊት ንቅለ ተከላን በሚያሟላ መልኩ እንደሚዘጋጅም ጨምረው ተናግረዋል።

ይህ ይበል የሚያሰኝ የታማሚዎችን ብቻ ሳይሆን የቤተሰባቸውንም ተስፋ የሚያለመልም ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። ቃል በተገባው መሰረትም ማዕከሉ ከእጥበት ባሻገር ንቅለ ተከላውንም እንዲያከናውን ይደረጋል የሚል እምነትም አለን።

> **ኩላሊት ዝምተኛ ነው። ወዲያው አክሙኝ አይልም። ይህ ሁኔታ ደግሞ ያዘናጋል። ስለዚህ ማንኛውም ሰው ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ኩላሊቱን ቢታይ ጥሩ ስለመሆኑም ባለሙያዎች ይመክራሉ። በተለይም የደም ግፊት፣ ስኳር፣ ከፍተኛ ክብደት (ውፍረት)፣ ሌላ ተጓዳኝ ህመም ያለባቸው ሰዎች ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ለኩላሊት ህመም ተጋላጭ ስለሚሆኑ ባይታመሙ እንኳን በየጊዜው ኩላሊታቸውን ቢታዩ ኋላ ከሚመጣው ችግር መዳን ይቻላል።**

# ነፃ ሃሳብ



በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# «አሉ! ተባለ! ተባባሉ!»

**«‹አሉ!› እያልን፣ ካልሆነ ሥፍራ አንገኝ»**

እንደ ሀገር ካደከሙን፣ ካጠወለጉን፣ ካታከቱንና ግራ ካጋቡን ወቅታዊ ችግሮቻችን መካከል "አሉ! ተባለ! ተባባሉ!" እንደሚባሉት "የአንደበት ቫይረሶች" የከፋ ወረረሽኝ አጋጥሞናል ለማለት በእጅጉ ያዳግታል። "በአሉ!" የወሬ አውሎ ነፋስ ያልተፍገመገመ፣ ያልቆሰለ ወይንም ተስፋ እስከ መቁረጥ ደርሶ ነገረ ዓለሙ ያልጨለመበት አትዮጵያዊ ወጣት፣ ጎልማሳ፣ ወይንም አረጋዊ/አራጋዊት ፈልጎ ለማግኘት እጅግም አያዳግትም።

ከገጠር እስከ ከተማ፣ ከአደባባይ እስከ የምናኔ ዋሻ፣ ከትምህርት ቤት እስከ ሐኪም ቤት፣ ከላይ ቤት እስከ ታች ቤት፣ ከሀገር ደጅ እስከ ባዕድ ምድር "በተባለ!" ወሬ ቀበቶው ያልላላ፣ ወይንም ማተቡ ያልሰለለ ሰው ማግኘት ተከቻለ አሁንም ያ ሰው "ጀግና" ወይንም የተለየ ፍጡር አለያም ከማሕበረሰቡ ሸሽቶ የሚኖር መጻተኛ መሆን ይኖርበታል። እሱውም ቢሆን "አሉ! ተባለ!" ለሚለው ሹክሹክታ ጆሮውን ያለማዋሱን እርግጠኛ መሆን አይቻልም።

ሀገር "በአሉ! በተባለ! በተባባሉ!" ጤና አጥታ ማደሯ "ኑሯችን ስለሆነ" እመኑ አትመኑ ብሎ ለመሟገት ተከራካሪና አከራካሪ እንጋብዝም። የዕለት እንጀራችን መሸመቻ ገበያው "በአሉ!" ወረርሽኝ ተናግቶና አብዶ ጨርቁን ጥሎ መወፈፉን የሚክድ ሰው ይኖራል ተብሎ አይታመንም። "ቅቤ ሻጭ ድርቅ ማውራቱ"፣ "ጨው ነጋዴ በዶፍ ዝናብ" ማመካኘቱ ባህል እስኪሆን ድረስ ተቀብለን ማቀባበል እንግዳችን አይደለም።

የሚያዛጉ ሰዎች ቁጥር በርከት ብሎ የሚያስተውል ሰው "የቡና ዋጋ መወደድን" በአዋጅ ቢለፍፍ፣ "ኑግ፣ ሰሊጥ፣ ተልባ ወይንም የሱፍ አበባ ከነገ ጀምር እንደማታበቅል ምድሪቱ ምላለች" ብሎ "በአሉ" አውሎ ነፋስ ወሬ በአየሩ ላይ የሚበትነውን ሰው እህ ብለን አድምጠን ዘይት ለመግዛት የወረፋ ሰልፍ የምናራዝም ብዙ ዜጎች አንጠፋም። የሠፈራችን አድባር እማማ አበዛሽ ደጋግመው እንደሚሉት፤ "ጤፍን ያስወደደው፣ ሸቀጦቻችንን ያናረው ሌላ ሳይሆን ‹አሉ!› እያልን የምናሟርትበት አንደበታችንና የወሬ ማመላለሻዋ ሞባይላችን በጥምረት በከፈቱብን ጦርነት አማካይነት ነው።"

የፖለቲካውና የአክቲቪዝሙ አየርና ምህዳርም "በአሉ! በተባባሉ!" ቫይረስ ተለክፎ አልጋ ላይ ከዋለ ሰነባብቷል። "አሉ" ለክፎናል፣ መርዞናል፣ ጤና ነስቶንም ያስቃዠናል። "አሉ!" የሚል መርዶም ይሁን ዜና ሳያቀብልና ሳይቀባበል የዋለ ዜጋ በሀገር ውስጥም ሆነ በባዕድ ምድር ጮኸን ብናጣራም ሰሚ እስከማይኖር ድረስ ሁሉም በደዌው ተሸንፎና ተረትቶ ከተልፈሰፈሰ ሰነባብቷል።

ይህ ርእሰ ጉዳይ ከሦስት ዐሥርት ዓመታት በፊት በሀገር ፍቅር ቴያትር ቤት ለሕዝብ የቀረበን አንድ ድንቅ ተውኔት ያስታውሰኛል። የተውኔቱ ርዕስ "አሉ!" የሚሰኝ ነበር። የቴያትሩ መቼት (Setting) በተቀነበበት አካባቢ የሚኖረው ማሕበረሰብ ማን እንደፈጠረው በማይታወቅ "የወሬ ቱማታ" ቀልብያውን ስቶ "ጉድ ተፈጥሯል" እያለ ሲቀባበል፣ ሲተረማምስና በጭንቀት ተውጦ ሲቃትቱ ተመልካቹ በሳቅ ይንፈራፈር ነበር።

ምናልባትም ይህ ጸሐፊ እጅግ ተማርኮባቸው ደጋግሞ ካያቸው ቴያትሮች መካከል "ከባልቻ አባነፍሶ" ቀጥሎ ሁለተኛው ተውኔት ይህ ሳይሆን አይቀርም። የብርሃኑ ዘርይሁን የቴያትር ድርሰት የሆነውን "ባልቻ አባነፍሶን" እግረ መንገዴን የጠቀሱኩት "ከሰደበኝ መልሶ የነገረኝ ገደለኝ" የሚል ድንቅ አባባል ትዝ ብሎኝ ነው።

"አሉ!" ተብሎ የተጠቀሰው ያ ተውኔት ዛሬ ተመልሶ ለመድረክ ቢበቃ እንኳንስ ተመልካቹ እየተፍነከነከ ሊዝናና ቀርቶ ማግጠጡን እንኳን እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ለምን ቢሉ "ሁሉ ቃልቻ ማን ይሸከም ስልቻ" ሆኖብን ሁሉም ዜጋ ኑሮዬ ብሎ የገበረለት ባህርይው "በአሉ! በተባለ!" ክፉ አየር ስለተበከለ ከኮሜዲነቱ ይልቅ እውነትነቱ ይበልጥ ስለሚጎላ ተመልካች ስለማግኘቱ ዋስትና መስጠት ያዳግታል።

"በአሉ እና ተባለ" ጌሾና እንክርዳድ የተጠመቁ የጊዜያችን ሃሜቶችና ወሬዎች የምን ያህሉን ሰው ናላ እንዳዞሩ፣ የስንቱን ትዳር እንደበተኑ፣ ስንቱን ለበቀልና ለቁርሾ እንደዳረጉ፣ ምን ያህሉን አወፍፈው ጨርቁን እንዳስጣሉት ደፋር ተመራማሪ ተገኝቶ የጥናት ውጤቱን ቢሰንድልን በራሳችን ማፈር ብቻም ሳይሆን ለተከታዩ ትውልድም ትምህርት በሆነ ነበር።

"በአሉ እና ተባለ" ጌሾና እንክርዳድ የተጠመቁ የጊዜያችን ሃሜቶችና ወሬዎች የምን ያህሉን ሰው ናላ እንዳዞሩ፣ የስንቱን ትዳር እንደበተኑ፣ ስንቱን ለበቀልና ለቁርሾ እንደዳረጉ፣ ምን ያህሉን አወፍፈው ጨርቁን እንዳስጣሉት ደፋር ተመራማሪ ተገኝቶ የጥናት ውጤቱን ቢሰንድልን በራሳችን ማፈር ብቻም ሳይሆን ለተከታዩ ትውልድም ትምህርት በሆነ ነበር

ይህ እንደ ሱስ ያስገበረን የማሕበራዊ ሚዲያ ዘመን ከእጃችን ያስጣለን ብዙ እሴቶች ቢኖሩም አንዱና ምናልባትም ተቀዳሚው ጉዳይ "ስግብግብ ጆሮ" እንዲኖረን ማድረጉ ነው። ነፍስ ሄሩ የሙዚቃ ጠቢብ ጥላሁን ገሠሠ "ስግብግብ አለች ጆሮዬ" ብሎ ያንጎራጎረው ዛሬ ከአርካይቭ ወጥቶ ብናደምጠው የሁላችንንም ጓዳና ጎድጓዳ በሚገባ ስለሚዳስስ የምናደምጠው ተሻምተን ይሆን ነበር። ለዘነጉትም ሆነ ትዝ ለማይላቸው አንባቢያን የግጥሙን ጥቂት ስንኞች እናስታውስ።

**«ሰው ሁሉ እንዳይሆን፣ ፍጹም ደመኛዬ፣**
**እያጣራ ይሰማ ስግብግብ ጆሮዬ።**
**ጎጂ ጠቃሚውን እያግበሰበሰ፣**
**ከጤናዬም ተርፎ ቤቴን አፈረሰ።**
**ልክስክሱን ሁሉ እያጠራቀመ፣**
**ይኼው እስከ ዛሬ አንጀቴ ታመመ።**
**ዘልቆ ሳይረዳ የጆሮን ምሥጢር፣**
**ጥሳቻን ያተርፋል ፍጡር በፍጡር።»**

"አሉ! ተባለ!" በሚል ባልተረጋገጠና ረብ የለሽ አንደበታቸው የወሬ ዘር ቋጥረው ማለዳ ላይ "በስግብግ ጆሮዎች" ማሳ ላይ ለመዝራት የሚተጉ ዜጎችን የሚወክል አንድ ታሪክ ከቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ማስታወሱ ቦታው ይመስለናል፤ እንጥቀሰው።

"እነሆ ዘሪ ሊዘራ ወጣ። እርሱም ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ፤ ወፎችም መጥተው በሉት። ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ። ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፣ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፣ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ። ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፣ እሾሁም ወጣና ኣነቀው። ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀ አንዱም መቶ፣ አንዱም ስድሳ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬ አፈራ። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።"

ይህ ግሩም ታሪክ ብዙ ቁምነገሮች ሊተላለፉበት ተፈልጎ የተነገ ምሳሌ ነው። ለጊዜው መንፈሳዊ ትርጉሙን ለእምነቱ አስተማሪዎች በመተው ምሳሌውን ለመመልከት የምንሞክረው "በአሉ!" ኮሮጆ የተሞላ የወሬ ዘር ለመዝራት ማልደው የሚወጡትን ግለሰቦች በአእምሯችን እየሳልን ይሆናል።

እነዚህ "አሉ! ወይንም ተባለ!" የሚል ዘር የሚበትኑት "የወሬ አዝማሪ" ገበሬዎች ዘራቸውን የሚበትኑት ባገኙበት ቦታ ሁሉ ነው። በጭንጫ ልብ የሚመስል ጠንካራ ሰብእና ያላቸው አንዳንድ ግለሰቦች እነዚህን መሰል የወሬ ትጉሃን የሚያስተናግዱት ጆሯቸውን ደፍነው ነው። ያወራሉ አያደምጧቸውም፤ ይቀባጥራሉ አይሰሟቸውም። ስለዚህም "የአሉ!" ማራገፊያ ስለማይሆኑ ሰብእናቸው በትንሽ በትልቁ የማይነዋወጥ ዓይነቶች ስለሆኑ ተረጋግተው ይኖራሉ።

ሌሎችም አሉ መንገድ ለመንገድ እየዞሩ "የወሬ እንክርዳዳቸውን" ሲዘሩ ቢያስተውሏቸውም ቁብ አይሰጧቸውም። እንዳላየ ሆነው ንቀው ያልፏቸዋል። አንዳንዶችም አሉ፤ "ልባቸውን በእሾህ በሚመስል" የብረት አጥር አጥረው "ለአሉ! ተባለ! ተባባሉ!" ሃሜቶችና ወሬዎች ቁብ የማይሰጡ።

እጅግ የሚያስገርሙት ግን "የአሉ! ሱስ" የተጠናወታቸውና ያልተረጋገጠ ወሬ ተቀብለው ለማቀበል ልባቸው እጅግ ለም የሆነ። የሚቀበሉትን የፈጠራ ወሬ ከድምጽ በላቀ ፍጥነት ተቀብለው "ነገሩን ሳያጣሩ ለመቶ፣ ለስልሳና ለሠላሳ" ጆሮዎች ለማፍጠን የሚተጉ። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች እንደ በካይ ቫይረስ ያልተገለጠ በሽታ ስላለባቸው ሊታዩ የሚገባቸው በጥንቃቄ ነው።

ዛሬ ሀገራችንን እያተረማመሰ ያለውን ችግር ጠለቅ ብለን ብንፈትሽ ዋናው በሽታ "በአሉ" የሚተላለፉ ወሬዎችና ሃሜቶች የሚፈጥሩት ወጀብ እንደሆነ በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ከርእሰ ብሔር እስከ ርእሰ መምህር፣ ከሃይማኖት መሪዎች እስከ ምእመን፣ ከባለ ሀብት እስከ ለፍቶ አዳሪ፣ ከምሁር እስከ ተማሪ፣ ከነጋዴ እስከ ቢሮክራት ወዘተ. ፈጠራ በታከለበት የ"አሉ" ወሬ ስሜቱ ያልተጎዳ፣ መንፈሱ ያልተሰበረ፣ አልፎም ተርፎ ለብዙዎች መዘባበቻ መሆኑ ቅስሙን ሰብሮ በጉዳት ያላነከሰ ስለመኖሩ ያጠራጥራል።

በተለይም በማሕበራዊ ሚዲያ የሚሰራጬት የወሬ ሱናሚዎች እንዴት አደብ እንደሚገዙ ሀገራዊ ምክክር ካልተደረገበት በስተቀር በዚህ ፍጥነት የሚቀጥል ከሆነ ጉዳቱ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም። አበው እንደሚሉት "ወደቀ ሲባል፤ ተሰበረ የሚሉ"፣ "ታመመ ሲባል፤ ሞቶ ተቀበረ" በማለት ሕዝብን የኀዘን ከል ለማስለበስ ሥራዬ ብለው የሚተጉት እየተለዩ አስፈላጊው የእርምት እርምጃ እስካልተወሰደ ድረስ የት አድርሶ እንደምን እንደሚያንኮታኩተን ለመገመት አይከብድም።

በመሠረቱ ሀገሪቱን እያመሰና እያተረማመሰ ያለው የወሬ ሸምቅ ተዋጊዎቹ የማሕበራዊ ሚዲያ መድረኩ ዛሬ እንደ ቀላልና እንደ ዋዛ በቸልታ ቢታለፍ ነገ ውጤቱ ሥር ከተሰደደ በኋላ እንንቀልህ ቢሉት መልሶ የሚገዳደረው ነቃዩን ስለመሆኑ አስታዋሽ አያስፈልገውም። ከቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መካከል የአንዱን አብዮተኛ ተማሪ ሁለት የግጥም ስንኝ ማስታወሱ የላይኛውን ሃሳብ ይበልጥ የሚያጎላ ይመስለናል።

**«ነቅናቂው ነቅንቆ፤ ቢያነቃንቀው፣**
**የተነቀነቀው ነቅንቆ ጣለው።»**

ዛሬ "በእንቁላል" ደረጃ የምናያቸው ችግሮች ነገ "በበሬ ወለደ" የፈጠራ ወሬ የሀገርን ዋልታ አናግተው አደጋ ላይ እንዳይጥሉን "ነግ በእኔን" ልናስብ ይገባል።

መቼም "አሉ!" እየተባለ ለሚነዛው ወሬ ሁሉ የሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ማስተባበያ ለመስጠት አይስነፍ ብለን መደምደሙ ተገቢ እንዳልሆነ አይጠፋንም። ቢሆንም ግን በሀገር ደህንነት፣ በወታደራዊ ጉዳዮች፣ በዲፕሎማሲ፣ በእምነትና በሃይማኖቶች፣ በሕዝቦች የእርስ በእርስ ጤናማ ግንኙነቶች ላይ ቤንዚን እያርከፈከፉ፣ ክብሪት እየጫሩ ጠብና አመጽ ሊቀሰቅሱ ምክንያት የሚሆኑ የ"አሉ! ተባሉ!" ወሬ ፈብራኪዎች መረጃ በማነፍነፍ በሚተጋው ክፍል በኩል ማስተባበያ ሊሰጥ፣ ሀሰቱም ሊጋለጥ ግድ ይመስለናል።

በተለይም እንደ ፋሽን በየተቋማቱ "የኮሚዩኒኬሽን ባለሙያዎች" የሚል ባጅ በደረታቸው ላይ የተንጠለጠለላቸው "ምንግዴዎች" ቢያንስ ደመወዝ የሚከፍላቸው ተቋም "በአሉ!" አልባሌ ወሬ ሲጠቃና ሲታመስ አብረው ከሚያሙ ይልቅ ሙያቸውን አክብረው እውነቱን በማሳየት የታዳጊነት ኃላፊነታቸውን ቢወጡ ጎሊናቸው ሰላም ያገኛል።

**«ዘንድሮ፣ ዘንድሮ፣ ዘንድሮ፣ ዘንድሮ፣**
**የስንቱ ተወርቶ የስንቱ ተነግሮ።**
**በዚያኛው ‹ተናደን› ጥቂት ሳንቆይ፣**
**የዚህኛው ‹ወሬ› አያስቅም ወይ?»**

እያልን "የአሉ! ተባለና ተባባሉ" የሰደድ እሳት ከስር ከስሩ ሳይስፋፋ ለማክሰም እስካልጨከንን ድረስ "ነበልባሉ" በሚሰጠን ጊዜያዊ ሙቀት "እህ!" እያልን በማድመጥ በቸልታ የምናልፍ ከሆነ መዘዙ ስለሚከፋ ውጤቱ የሚበጅ አይሆንም። "ልብ ያለው ልብ ይበል" ማጠቃለያ ምክራችን ነው።

**ሰላም ይሁን!**

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

# ከመቐለ እስከ ሰበር ችሎት የዘለቀው ፍርድ

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**



የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች በተካተቱበትና በ2007 ዓ.ም ለህትመት በበቃው መፅሐፍ ቅፅ 16 ላይ በሰነድ መለያ ቁጥር 97206 ሐምሌ 28 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት አምስት ዳኞች ከችሎቱ ላይ ተቀምጠዋል። በዚህም አመልካች አቶ አማረ መልካሙ ራሳቸው በቪዲዮ ኮንፈረንስ አማካኝነት ከመቐለ የቀረቡ ሲሆን፤ በተጠሪ አቶ ካሌብ ሕሉፍ በኩል የቀረበ አልነበረም። ታዲያ ዳኞች ሠዓቱን ጠብቀው ከችሎቱ ተሰይመውና ዳኞች መዝገቡን በጥልቀት መርምረው ፍርድ እነሆ ብለዋል።

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ በሰበር ችሎቱ ሊወሰን ይገባል ተብሎ የተያዘው ጭብጥ አመልካች የተጠሪ ንብረት የሆነውን በትግራይ ክልል ኮንስትራክሽንና መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ካላቸው ገንዘብ 612ሺ.2005 ብር በፍትሃብሄር ሥነሥርዓት ቁጥር 154/ለ/ መሠረት ማሳገዳቸው ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች የቀደምትነት መብት ያረጋግጥላቸዋል ወይ የሚለው ነው። አመልካች በተጠሪ ላይ የመሰረቱት ክስ ተከትሎ የፍርድ ባለገንዘብ መሆናቸው ተረጋግጧል።

በአመልካች ጠያቂነት ከላይ በተጠቀሰው ቢሮ የነበረውን ገንዘብም አሳግዷል። አመልካች ገንዘቡን ካሳገዱ በኋላ አሥራ ሰባት የፍርድ ባለገንዘቦች ከተወሰነ ቀን በኋላ በተመሳሳይ መንገድ የተጠሪ ገንዘብ ላይ ዕግድ እንዲሰጥ አመልክተው በፍርድ ቤት ተቀባይነት አግኝቷል። አመልካች በትግራይ ክልል መቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመለያ ቁጥር 14044 ባቀረቡት ክስ ያሳገዱትን ገንዘብ በቅድሚያ ለእሳቸው እንዲከፈል ጠይቋል። የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን ለክርክር መነሻ የሆነውን ሃብት ገንዘብ መሆኑን መሠረት በማድረግ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደው ገንዘብ ከመሆኑ አኳያ እንደማይንቀሳቀስ ንብረት የማይወሰድ ነው።

በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደው ገንዘብ ለፍርድ ባለገንዘቦች ባስፈረዱት መጠን በሬሽዎ እንዲከፋፈል በማለት ብይን ሰጥቷል። አመልካች የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ወደ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል። አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተፈጽሟል ያሉትን የሕግ አተረጓጎም ስሕተት በመዘርዘር የሰበር አቤቱታቸውን በ26-05-2006 ዓ.ም አቅርበዋል።

የአቤቱታው መሠረታዊ ይዘት የፍርድ ባለዕዳ ገንዘብ ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች ቀድመው ማሳገዳቸውን መሠረት ተደርጐ የቀደምትነት መብት እንዲከበርላቸው፤ የቀደምትነት መብት በማይንቀሳቀስ ንብረት ብቻ ሳይሆን በሚንቀሳቀስ ንብረትም ማቋቋም እንደሚቻል፤ የሥር ፍርድ ቤቶችም ክፍያ ማስፈጸም ያለባቸው የፍርድ ባለገንዘቦች ገንዘቡን ባስከበሩበት ቅደም ተከተል ሊሆን እንደሚገባ በመጥቀስ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲታረም ጠይቋል።

ተጠሪ የአመልካች አቤቱታ ከመጥሪያ ጋር የተላከላቸው ቢሆንም በአድራሻቸው ስላልተገኙ በፍርድ ቤት ቅጥር ግቢ በሚለጠፍ መጥሪያ መሠረት እንዲቀርቡ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ባለ መቅረባቸው በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል። ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል። ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች በፍርድ ባለዕዳ ገንዘብ ላይ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማስከበራቸው የቀደምትነት መብት እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም በሥር ፍርድ ቤት ተቀባይነት አላገኘም። ከላይ እንደተገለጸው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከበረው ነገር ገንዘብ ነው ይላል በክርክሩ ላይ ከቀረቡት ሃሳብ ውስጥ በግርድፉ ሲገለፅ።

የፍርድ ባለገንዘብ በፍርድ ባለዕዳ ንብረት ላይ የቀደምትነት መብት በሕግ፣ በውል እና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊያቋቁም ይችላል። ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ የቀደምትነት መብት በጋራ የንብረት ባለሃብቶች፤ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንደውሳኔውን ለማስፈጸም እንዲሁም ግራ ቀኙ ባደረጉት ሥምምነት ሊቋቋም እንደሚችል ከፍትሃብሄር ቁጥር 3043፣3044 እና 3045 ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። በሌላ በኩል በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የቀደምትነት መብት ሊቋቋም የሚችለው የፍትሃብሄር ቁጥር 2825 በሚያዘው አግባብ የፍርድ ባለዕዳው ንብረቱን ለፍርድ ባለገንዘብ ማስረከቡ ሲረጋገጥ መሆኑን ከሕጉ ንባብ የምንገነዘበው ነው።

አመልካች የቀደምትነት መብት እንዲሰጣቸው መሠረት ያደረጉት የፍትሃብሄር ሥነ ስርዓት ቁጥር 154/ለ/ ነው።

የዚህ ሕግ አንቀጽ መሠረታዊ ይዘትና ዓላማ ስንመለከተው በክርክር ላይ ባሉ ጉዳዮች የፍርድ ባለገንዘብ በመጨረሻ የረታ ከሆነ ፍርዱን ለማስፈጸም የሚያስችል ንብረት ወይም ገንዘብ እንዳይታጣ ቅድመ ጥንቃቄ ለማድረግ ነው። ከፍትሃብሄር ሥነ ስርዓት ቁጥር 154 ርዕስ እንደምንረዳው የማገድ ትዕዛዙ የሚሰጠው ለጊዜው ስለመሆኑ፤ በፍርድ ባለዕዳ ሥር ያለው ንብረት በየትኛውም መልኩ ለሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ፤ እንዳይበላሽ፤ እንዳይጠፋ ፍርድ እስከሚሰጥ ተከብሮ እንዲቆይ የማድረግ ዓላማ ያለው ነው።

አመልካች ከላይ በተገለጸው አግባብ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ማሳገዳቸው በማይንቀሳቀስና በሚንቀሳቀስ ንብረት የቀደምትነት መብት ማቋቋም በሚያስችል አግባብ ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብት አግኝቷል ወይ፤ የሚለውን የክርክር ነጥብ በአግባቡ መታየት አለበት። ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ከፍርድ በፊት በማይንቀሳቀስ ሆነ በሚንቀሳቀስ ንብረት የቀደምትነት መብት ማቋቋማቸው የሚገልጽ ነገር አላቀረቡም። አመልካች በእጃችን ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው ድንጋጌ ነው በማለት የጠቀሱት የሕግ አንቀጽ 2860 ከላይ በጠቀስነው አግባብ መያዣ/Pledge/ያቋቋሙ የፍርድ ባለገንዘቦች ያላቸውን መብት የሚያመለክት እንጂ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለው ሆኖ አልተገኘም።

አመልካች የቀደምትነት መብት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማቋቋማቸው የገለጹ ቢሆንም የፍትሃብሄር ሥነ ስርዓት ቁጥር 154/ለ/ ከሌሎች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ስንመለከተው ከዚህ የተለየ ትርጉም የሚሰጥ ሆኖ ተገኝቷል። ንብረት ለማስከበር የሚቀርብ ማመልከቻ ሊያሟላቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች የፍትሃብሄር ሥነ ስርዓት ቁጥር 379 በዝርዝር ደንግጓል። የማይንቀሳቀስ ንብረቱ ዓይነቱን በመለየት ማቅረብ ግዴታ መሆኑን፤ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሆነ ደግሞ ንብረቱን ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉ ምልክቶች መገለጽ እንዳለባቸው ንብረቱ የሚለየው በአካባቢው ውስጥ ወይም ርስተ መዝገብ ከሆነ በተራ ቁጥር በሆነ ጊዜ የወሰኑ ምልክት ወይም በመዝገብ ላይ የተሰጠው ቁጥር መግለጽ እንደሚገባ ተመልክቷል። አመልካች በፍርድ ባለዕዳ ንብረት ላይ የዕግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ማድረጋቸው ከላይ በተገለፀው አግባብ ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ የቀደምትነት መብት አቋቁመዋል ለማለት የሚቻል አይደለም።

አንድ የፍርድ ባለገንዘብ በፍትሃብሄር ሥነ ስርዓት ቁጥር 154/ለ/ መሠረት የንብረት ዕግድ ቢያሰጥ የቀደምትነት መብት የሚያቋቁም ስለመሆኑና አለመሆኑ ከአሁን በፊት የሰበር ሰሚ ችሎት በሰነድ መለያ ቁጥር 29269 እና 27808 የሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች ተመልክተናል። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በማድረግ ብድር በመስጠታቸው ምክንያት የሥር ፍርድ ቤቶች የቀደምትነት መብታቸው የነፈገ ውሳኔ በመስጠታቸው የእነዚህ አበዳሪ ተቋማት መብት የሚያስጠብቅ ውሳኔ መስጠቱ የሚያስረዱ ናቸው።

የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔዎች በተናጠል ሲንመለከታቸው በሰነድ መለያ ቁጥር 27808 የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ግለሰቦች ሲከራከሩ በመያዣ የያዘው ቤት በማሳገዳቸው ዕግዱ እንዲነሳ ሲጠይቅ ጣልቃ ገብተህ አልተከራከርክም ዕግዱ አይነሳም የሚል ውሳኔ በመስጠቱ በቀረበው አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሯል። በሌላ በኩል በሰነድ መለያ ቁጥር 29269 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አስቀድሞ ንብረት ማስከበሩ ብቻውን የቀደምትነት መብት አያሰጥም ማለታቸው ከሕግ የመነጨ የቀደምትነት መብት የነፈገ ነው ተብሎ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል።

በእነዚህ ሁለት የሰበር ውሳኔዎች አሁን በእጃችን ካለው ጉዳይ ያላቸው ተመሳሳይነት እንደተመለከትነው ከላይ የተጠቀሱ ተቋማት የቀደምትነት መብታቸው በማይንቀሳቀስ ንብረት ያቋቋሙት የቀደምትነት መብት የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ያቀረቡት ጉዳይ ግን በፍትሃብሄር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 154/ለ/ መሠረት በአንድ የመንግሥት ተቋም የተያዘው የሚንቀሳቀስ ገንዘብ የሚመለከት በመሆኑ ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የላቸውም።

የቀደምትነት መብት በሕግ፣ በውል ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ /ውሳኔ/ የሚቋቋም ስለመሆኑ ከላይ በተገለጸው የፍትሐብሄር ሕግ ተመልክቷል። አመልካች በፍርድ ባለዕዳ ላይ አስፈረደው ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች ቀድመው የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ማግኘታቸው ከሕግ፣ ውል ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ የመነጨ የቀደምትነት መብት አቋቁመዋል ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የላቸውም።

አመልካች በተጠሪ ገንዘብ የሰጡት የዕግድ ትዕዛዝ ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች የተሻለ መብት እንዳላቸው የሚያረጋግጥ አይደለም ከተባለ፤ ቀጥሎ የሚነሳውን ጥያቄ በተራ የፍርድ ባለመብቶች መካከል ያለው የክፍፍል ሥርዓት ምንመሆን አለበት የሚል ነው። ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት እንደተቻለው አመልካችን ጨምሮ በተጠሪ ገንዘብ ላይ 18 ግለሰቦች የዕግድ ትዕዛዝ አሰጥቷል። ከአንድ በላይ የፍርድ ባለመብቶች ባሉበት ጊዜ የሀብትና የንብረት ክፍፍል ሥርዓት ምን መሆን እንዳለበት የፍትሃብሄር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 403 ያስቀመጣቸው ሁኔታዎች ማየቱ ተገቢ ይሆናል። በዚህ ድንጋጌ መሰረት የፍርድ ባለገንዘቦች ተቀማጭ የሆነውን ሀብት በውሳኔው መሰረት እንዲከፋፈሉ እንደሚያደርግ ተመልክቷል።

አመልካች በተጠሪ ገንዘብ ላይ ቀድመው የዕግድ ትዕዛዝ ማስጠታቸው ግልጽ ቢሆንም ሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦችም በተከታታይ ቀናት ይህንን የማሳገድ ተግባር አከናውነዋል። አመልካች ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች የቀደምትነት መብት ያልተሰጣቸው ከሆነ ሁሉም የፍርድ ባለገንዘቦች እንደተራ ገንዘብ ጠያቂዎች የሁሉም መብት እኩል እንደሆነ የሕግ ግምት ይወሰዳል። ከላይ እንደተገለጸው አንድ የፍርድ ባለገንዘብ ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች አስቀድሞ የባለዕዳውን ንብረት በማስከበሩ ምክንያት ብቻ የቀደምትነት መብት አይሰጠውም። በመሆኑም የፍርድ ባለገንዘቦች እንደተራ የፍርድ ባለመብቶች ተወስደው ደረጃቸው (መብታቸው) እኩል መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ባስፈረዱት የገንዘብ መጠን መቶኛ ስሌት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደውን ገንዘብ እንዲከፋፈሉ ማድረጉ የሕግ መሰረት ያለው ስለመሆኑ ከፍትሃብሄር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 403 ይዘት ዓላማና መንፈስ የምንረዳው ነው።ከዚህ አንፃር የሥር ፍርድ ቤቶች የፍርድ ባለገንዘቦች በፍርድ ባለዕዳው ላይ ያላቸው የገንዘብ መጠን በመቶኛ (ሬሾዎ) እንዲከፋፈሉ ትዕዛዝ መስጠታቸው መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለመገኘቱ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል ሲል ሰነዱ አስቀምጧል።

**ው ሣ ኔ**

1. የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ.መ.ቁ.14044 በ25/04/2006 ዓ.ም የሰጠው ብይን፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኮ.መ.ቁ. 6365 በ12/05/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል።
2. አመልካች እና ሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች ባስፈረዱት መጠን ገንዘብ መቶኛ ስሌት (ሬሽዎ) ድርሻ ድርሻቸውን ይከፋፈሉ ብለናል።
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፤ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፤ ሲል ውሳኔውን አስቀምጧል ከመቐለ እስከ ፌዴራል ድረስ የተራዘመው ክርክር።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የሳይበር ፍርደኞች

**ተገኝ ብሩ**

እነዚህ ፍርደኞች እነሱ ጋር ያለ እውነት ፈጽሞ የማይታወቅ፤ ስለነሱ ተግባርና እውነት ፈፅሞ መረጃ የሌለው የሚፈርድባቸው ናቸው።እነዚህ ሚዛን አልባ ፈራጅ በመንጋ በመሆን በዘመቻ መልክ የሚበየንባቸው የማህበራዊ መገናኛ ብዙኃን ፍርደኞች ያሳስቡኛል። እነሱ አደረጉ ወይም አሉ በሚባለው ብቻ ተነስቶ ጉዳዩን ሳይመረምር ሁሉም የራሱን ፍርድ ይሰጥባቸዋል። አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር እነዚህ ላይ በእያንዳንዱ መገናኛ ብዙኃንና ማህበራዊ መገናኛዎች ሁሉ ተመሳሳይ እርግማንና ትችት ሰለባዎች ናቸው።

በነገራችን ላይ እነዚህ የሳይበር ፍርደኞች ለፍርድ ያበቃቸውን ጉዳይ ዞር ብሎ የሚመረምር ያደረጉትን ተግባር ምንነት “በትክክለኛ መረጃ ይጣራ” የሚል የዚህ ሞገድ ተሳታፊ መኖሩ እስኪያጠራጥር ድረስ በዘመቻ ይኮነናሉ። እነዚህ ጉዳያቸው ባላወቀ አካል የሚበየንባቸው በአንድነት የሚብጠለጠሉ እድለቢሶች ናቸው። የሆኑትና ሆኑ የተባሉበት ትክክለኛ ሁነት ይለያያል። እውነቱን ማወቁ ፈራጁ አያገባኝም ያለ ይመስላል። ሁሌም የሰሩት ሥራ ትክክል አለመሆኑን አንስቶ መርገም እነሱ ላይ መፍረድ ነው ዋንኛ ተግባርና ልማዱ።

ሰሞኑን በዜና መልክ በተለይ በትልልቅ መገናኛ ብዙኃን የዜና ማሰራጫ ገፃቸው ላይ አትመውት ሰዎች ሲቀባበሉበት የነበረውን ዜና አይቼ አንድ ሀሳብ ወደውስጤ ሰረፀ። ዜናው እንዲህ የሚል ነበር። “በሃሰተኛ ገንዘብ ነዳጅ ቀድቶ ለማምለጥ የሞከረው አሽከርካሪ ከቆመ ተሽከርካሪ ጋር በመጋጨቱ ሕይወቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ገለፀ።” በእርግጥ ዜናው ላይ ላዩን ሲታይ ብዙ ከማመራመር ይልቅ በማህበራዊ ድህረ ገፆች ሰዎች ሲያዘዋውሩትና አስተያየት ሲሰጡበት እንደነበረው “ይሄ አጭበርባሪ ዋጋውን አገኘ” የሚያስብል ይመስላል።

ወገን አያችሁ የብዙዎቻችን እርግማን ይህና መሰሉ ነበር። እዚህ ላይ ነው የኔ ጉዳይ ወገን። ይህ ዜና የተሰራበት መንገድ አልያ ዜናውን ያዘጋጀውና ያስተላለፈው ግለሰብ አልያም ተቋም ምን አስቦ አልያም ምን ለማስተላለፍ ፈልጎ ነው? የሚለውን ለመገመት እንሞክር። አንድም የሰውየው ከስነምግባር ውጪ መሆንና ማጭበርበሩን አንስቶ፤ ይህ ክፉ ተግባሩ በራሱ የበለጠ ክፉ ነገር አስከተለበት። ወይም በገጠመኙ አንስቶ ሌላውን ለማስተማር በማለም ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው የሚዲያው ዓላማ ብንገምት አዳዲስና የተለያየ ነገር ለአድማጩ አቅርቦ ይበልጥ አድማጭና ተመልካች ማግኘት ወይም መሰል ሌላ አላማ ሊሆን ይችላል፤ ብለን ከዚህ ብዙ ያልራቁ ብዙ ተመሳሳይ ግምቶችን እንሰጥ ይሆናል።

እኔ ዜናው ላይ ከዚህ ከላይ ከተቀመጡ አላማዎች ከፍ ያለ የሚመስለኝ ምክንያታዊ ምልከታ ማካፈል ስለፈለኩ ነው ይህንን ገጠመኝ እዚህ ጋር ማንሳቴ። እስኪ ሰውየው ጋር ከመገናኘቱ በፊት ሊሆን የሚችል ምን አልባትም ሊገጥመው የሚችልን ጉዳይ እንመልከት።

ይህ አደጋ ደርሶበት የሞተው ግለሰብን ትንሽ ወደ ኋላ መልሰን ከመሞቱ 1 ሰዓት በፊት ሊገጥመው የሚችልን ገጠመኝ ነው ብለን እናስብ ለጊዜው። እዚህ ላይ ግን እኔ ሰውየው ለማጭበርበር አልሞከረም እያልኩ አይደለም፤ግን ሰውየው ሊያጭበረብር ፈልጎ ላይሆን ይችላል ብዬ እገምታለሁ።

አደጋው የደረሰው አልያም ጉዳዩ የተፈፀመው ከለሊቱ 6፡30 አካባቢ ነው። ሰውየው የላዳ ሹፌር ነው። ምን አልባት ሰውየው እዚያ ማደያ ውስጥ ከመግባቱ ጥቂት ደቂቃዎች በፊት ለማደያው ከፍሎት የነበረው እውነተኛ ያልሆኑ የብር ኖቶች አገልግሎት ከሰጠው ሰው ተቀብሎ ቢሆንና፤ ገንዘቡ በስህተት ከሰው እንደተቀበለ አስቀምጦት ወደማደያው ሲገባ ለነዳጅ ቀጂው ሰጥቶ ሲወጣ አደጋው ደርሶበት ቢሆንስ? ብዬ አስባለሁ።

ምን አልባትም እንደተባለው ሰውየው ለማጭበርበር ሞክሮ ሲያመልጥ አደጋ ደርሶበት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ሰውየው ኖሮና ተይዞ ጉዳዩ ቢመረመርና እውነቱን ብናውቅ መልካም ነበር። ግን ደግሞ ሰውየው የሞተው እዚያው ከማደያው ብዙ ሳይርቅ ተጋጭቶ ስለሆነ የተነገረን ዜና እንዲህ ነው ሲባል ተቀብለን ሟቹን ከመርገም ባለፈ ምን አልባት እንዲህ ቢሆንስ አለማለታችን ግን አስገርሞኛል። ደግሞ ማታ ሞቶ በደንብ ምርመራና ከጀርባው ሊከሰት የሚችለው ነገር ሳይሰላ ጠዋት ነው ዜናው የታወጀው።

እኛ በተለይ በአብዛኛው የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ ከምክንያት የራቁ እጅጉን ለመንጋነት የቀረቡ ፍርድ ሰጪዎች እንጂ ጉዳዮችን ስንመለከት ምን አልባት ሌላ አይነት መነሻና ያላወቅነው ገጠመኝ ሊኖረው ይችላል ብለን ማስላቱ ላይ ብዙም ነን። ጉዳዮችን በተነገረን ልክ በቀጥታ ከማየት ይልቅ ከበስተጀርባ ሌላ ያላየነው እውነት ሊኖር ይችላል የሚል ልምድ ከእኛ ርቋል። በዚህም የመንጋ ፍርድ ፈራጆች በማናውቀው ጉዳይ ፍርድ ሰጪዎች ሆነን አርፈነዋል።

ከራሳችን ስህተት ይልቅ የሌሎች ስህተት አግዝፈን ማየታችን ብዙ ጊዜ የበለጠ ስህተት ውስጥ ይጥለናል። በምድር ላይ ስንኖር አብዛኞቻችን ስህተት መስራታችን እውነት ነው፤ፍፁምነት የሰው ልጅ ባህሪ ሊሆን አይችልም። ስህተት መቀነስ እንጂ ፈጽሞ ማጥፋትም አንችልም። ግን ደግሞ ስህተቶቻችንን ወይም የሌላውን ስህተት ለማረም የምንሞክርበት ሂደት ላይ ነው ልዩነቱ። ሰዎች መሳሳታቸው ስላገዘፍን አልያም ስለኮነን ብቻ ስህተቱ ይታረማል ማለት አይደለም።

በዚሁ ሰሞን አንዲት ታዋቂ ቴሌቪዥን ላይ ትሰራ የነበረች ጋዜጠኛ በማህበራዊ ሚዲያ የሚረግማትና ስህተትዋን አጉልቶ ለማሳየት በዚያም ውስጥ እኔ ከስህተት የራኩ ነኝ ብሎ ሊነግረን ያልሞከረ በጣም ጥቂት ነው። ልጅትዋ በይፋ የሰራችው ስህተት መሆኑንና ባላሰበችው መልክ በሌሎች ቪዲዮው መውጣቱን ገልፃም፤ለምን እንዲህ አደረገች የሚለው ወቀሳና ነቀፌታ ቀጥሎ ነበር።

አብዝተን ስህተት ውስጥ የምንወድቀው ፍፁም ትክክል ነን ብለን በምናምንበት ጉዳይ ነው። ይሄም ሁለት መልክ አለው አንደኛው እርግጠኛ የሆንበት ጉዳይ ጥንቃቄ እንዳናደርግ የበዛ የራስ መተማመን ውስጥ አድሶን አልያም ደግሞ ያወቅነው የመሰለን ጉዳይ አልያም ተረድተነዋል የምንለው ጉዳይ ብዙም ትኩረት ሰጥተን ባለማየታችን። እኛ ከስህተት የራቅን ባንሆንም ብዙ ጊዜ እነዚህ ናቸው የስህተቶቻችን መነሻ ምክንያት ።

በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የምንሳተፍ የሳይበር ፍርደኞች ደግሞ የሌላው ስህተትና ጉድፍ አብዝተን የምንተቸው እኛ ንፁህና ከስህተት የጠራን ነን ብለን በማሰባችን ነው። ነገር ግን የእያንዳንዳችን ጓዳ ቢመረመር ከምናወግዘውና ተፀይፈን ከምንገልፀው ነውር ከፍ ያለ ነውር ባለቤት ሆነን እንገኛለን። በሰዎች ላይ የምንበይነው አልያም የምንፈርደው ፍርድ አገናዝበንና ምን አልባትም እኛ ከፊት ከምናየውና እውነት ካልነው ጉዳይ በተቃራኒው የሆነ እውነት ሊኖር ይችላል ብለን መገመት ይኖርብናል።

ወገን በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ የራሳችን ፍርድ ሰጪና ተንታኝ መሆን እንዴት እንችለዋለን። እኛ የሚመለከተንና የራሳችን የሆነ ጉዳይ ካልሆነ በቀርስ እንዴት የማናውቀውን ጉዳይ መዳኘት እንችላለን። ዳኝነት ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች አሉት። የመጀመሪያው እውነት ለማወቅ መጣር፣ ትክክለኛው ጉዳይ ለመለየት መስራትና እዚያ እውነት ላይ ቆሞ ፍርድ መስጠት ነው። እኛ ዳኝነታችን አልያም ፈራጅነታችን ሁለቱን ያማከለ ካልሆነ ፍርዳችን የተዛባ ነው። አበቃሁ፤ ቸር ይግጠመን።

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ የዩክሬንን አንድ አምስተኛ መሬት መያዟን ዜሌንስኪ ተናገሩ

የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዜሌንስኪ የሩሲያ ኃይል የአገራቸውን 20 በመቶ መሬት ተቆጣጥሮ መያዙን ተናገሩ።

ሉክዘምበርግ ውስጥ ላሉ የምክር ቤት አባላት ባደረጉት ንግግር ጦርነት እየተካሄደበት ያለው ግንባር ከ1 ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ ሰፍቷል ሲሉ ተናግረዋል።

“ለጦርነት ዝግጁ የሆነ የሩሲያ ጦር በሙሉ በዚህ ወረራ ተሳታፊ ሆኗል” ሲሉ ለሉክዘምበርግ የምክር ቤት አባላት በቪዲዮ ኮንፍረንስ ተናግረዋል።

የሩሲያ ኃይሎች በዶንባሳ ግዛት የምትገኘውን ሴቬሮዶንስክ ከተማን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጥቃት ከፍተዋል።

የዩናይትድ ኪንግደም መከላከያ ኃላፊዎች ሩሲያ በርካታ የጦር አባላት እና ተተኳሾችን በዚህ ግንባር በማሰለፏ አብዛኛውን የከተማዋን ቦታዎች መያዝ ችላለች ብለዋል።

ሴቬሮዶንስክ በዶንባስ ግዛት የምትገኘው የመጨረሻዋ በዩክሬን ቁጥጥር ሥር ያለች ምስራቃዊት ከተማ ናት።

ሩሲያ ይህችን ከተማ ለመያዝ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ጥቃት መክፈቷን ዩክሬናዊው የአካባቢው ገዢ ሴርሂይ ሃኢዳኢ ተናግረዋል።

የአካባቢው ገዢ የዩክሬን ወታደሮች የሩሲያን የወደፊት ግስጋሴ ለመግታት መልሶ ማጥቃት ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።

“የዩክሬን ወታደሮች ባካሄዱቸው የመልሶ ማጥቃት እርምጃዎች የጠላት ኃይልን ከአንዳንድ አውራ ጎዳናዎች እንዲያፈገፍጉ ማድረግ ችለዋል። ብዙ ወታደሮችም ተማርከዋል” ብለዋል።

ከፍተኛ ውጊያ እያስተናገደች በምትገኘው ሴቬሮዶንስክ ከተማ ከ15 ሺህ ያላነሱ ንፁሃን መውጫ አጥተው በከተማዋ እንደሚገኙ ተገልጿል።

በተያያዘ ዜና በደቡባዊ ዩክሬን የምትገኘው እና በሩሲያ ቁጥጥር ሥር ባለችው ማሪዮፖል ንፁሃን ዜጎች በሩሲያ ወታደሮች መገደላቸው ተገልጿል።

የከተማዋ ከንቲባ በሞስኮ ከተሰየመው አስተዳደር ጋር አንተባብርም ያሉ የከተማ የመንግሥት ሰራተኞች በሩሲያ ጦር እየተገደሉ ነው ሲሉ ክስ አሰምተዋል።

ከተማዋ በሩሲያ ጦር ቁጥጥር ስር ከመውደቋ በፊት ከከተማዋ የወጡት ከንቲባ ቫደይመ ቦይቼንኮ በርካታ ሰዎች በሩሲያ ጦር ቁጥጥር ሥር እንደሚገኙ እና ስቃይ የሚደርስባቸውም ስለመኖራቸው ተናግረዋል።

ከንቲባው ባለፈው ሳምንት የሩሲያ ጦር ከተማዋን ለመያዝ ከፍቶት በነበረው ጥቃት ከ22ሺህ በላይ ሰዎች መገደላቸውን ተናግረው ነበር።

**ምንጭ ቢቢሲ**

## ናይጄሪያ የዝንጀሮ ፈንጣጣን ለመግታት የጫካ ሥጋ ሽያጭን አገደች

የናይጄሪያ መንግሥት የዝንጀሮ ፈንጣጣን ለመቆጣጠር የሚደረገውን ጥንቃቄ ለማገዝ የጫካ ሥጋ ሽያጭ ማገዱን ይፋ አደረገ።

ባለፈው አንድ ወር ውስጥ ብቻ በናይጄሪያ ስድስት በዝንጀሮ ፈንጣጣ የተያዙ ሰዎች መገኘታቸውን ባለሥልጣናቱ ገልፀው በዚህ ዓመት በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 21 ደርሷል ሲሉ ይፋ አድርገዋል።

የዝንጀሮ ፈንጣጣ በቫይረሱ የተያዘ እንስሳ ሥጋን በመመገብ ከእንስሳ ወደ ሰው ሊተላለፍ እንደሚችል ባለሙያዎች ቢናገሩም ይህ በጣም የተለመደው የመተላለፊያ መንገድ አይደለም።

የዝንጀሮ ፈንጣጣ ቀላል የቫይረስ ኢንፌክሽን ሲሆን በናይጄሪያ በስፋት ይታያል። በተለይም በገጠራማ አካባቢዎች እና በሞቃታማ የዝናብ ደኖች አቅራቢያ ቫይረሱ የበለጠ ይስፋፋል።

እ.ኤ.አ. በ 2017 ወረርሽኙ ከተከሰተ በኋላ ናይጄሪያ አልፎ አልፎ በዝንጀሮ ፈንጣጣ የተጠቁ ሰዎች አጋጥመዋታል።

ቫይረሱ በዋነኛነት በደቡብ የአገሪቱ ክፍል የተገኘ ቢሆንም ከ2020 ጀምሮ ወደ መካከለኛ፣ ምሥራቅ እና ሰሜናዊ አካባቢዎች ተዛምቷል ሲልም የዓለም ጤና ድርጅት አስታውቋል።

በዚህ ዓመት ከተረጋገጡት 21 በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች መካከል አንድ ሰው በበሽታ ሕይወቱ ማለፉ ተዘግቧል።

ነገር ግን በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ የናይጄሪያ የጤና ኃላፊዎች “ምንም አዲስ ወይም ያልተለመደ የቫይረሱ ስርጭት የሚያሳይ ማስረጃ የለም፣ እንዲሁም በክሊኒካዊ መረጃዎቻችን ላይ የተመዘገበ ለውጥ የለም” ሲሉ ተናግረዋል።

ሳይንቲስቶች በአውሮፓ በቅርቡ እየጨመረ የመጣውን የዝንጀሮ ፈንጣጣ ለማብራራት እየጣሩ ይገኛሉ። ነገር ግን ይህ ወረርሽኝ ከአፍሪካ አገሮች ከሚደረግ ጉዞ ጋር እስካሁን አልተገናኘም። ነገር ግን ሳይታወቅ ቫይረሱ ከሰው ወደ ሰው ሲሰራጭ መቆየቱን የሚያሳዩ መረጃዎች ይፋ ሆነዋል።



አንድ ሰው በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር ንክኪ ካለው ቫይረሱ ሊሰራጭ ይችላል። ቫይረሱ በተሰነጠቀ ቆዳ፣ በመተንፈሻ አካላት እና በዓይን ወደ ሰውነታችን ሊገባ ይችላል።

በዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ በዝንጀሮ ፈንጣጣ የተጠቁ ሰዎች የበሽታው ምልክት በሚያዩበት ወቅት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከመፈጸም እንዲቆጠቡ ተነግሯቸዋል።

በናይጄሪያ ለምግብነት የሚውሉ እንደ ቺምፓንዚዎች፣ የሌሊት ወፍ፣ አይጥ እና እባቦችን ጨምሮ ከጫካ አድኖ መመገብ የተለመደ ነው። ሥጋቸውም በከተሞች ይሸጣል።

ይህም በተለይም በገጠራማ የናይጄሪያ አካባቢዎች በጣም ወሳኝ የምግብ አማራጭ ሲሆን፣ በሌሎች አካባቢዎች ውስጥ ደግሞ ዘወትር ባይገኝም ተወዳጅ እና ውድ ምግብ ነው።

በዚህም ምክንያት በናይጄሪያ በርካታ የጫካ ሥጋ ገበያዎች የሚገኙ ሲሆን፣ አሁን የተጣለው እገዳ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን እስካሁን ግልፅ አይደለም።

የግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ህክምና ባለሙያዎች እና ሌሎች ባለሥልጣናት በእንስሳት ላይ ሊከሰት የሚችለውን የዝንጀሮ በሽታ ለመለየት የሚያስችል ክትትል እንዲጨምሩም መመሪያ ሰጥቷል።

የመካነ እንስሳት፣ የፓርኮች እንዲሁም የልዩ ጥበቃ ቦታዎች እና የመዝናኛ ማዕከላት አስተዳደሮች በእንስሳትና በሰዎች መካከል ምንም አይነት ግንኙነት አለመኖሩን እንዲያረጋግጡም ማሳሰቢያ ተሰጥቷል።

**ምንጭ ቢቢሲ**

# ደስታን በምን ...?



**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

መጠሪያ ስማቸው ደስታ የሆኑ ግለሰቦች ከስማቸው አወጣጥ ጀርባ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከደስታ ፍሊጋ ጋር የተገናኘ አንዳች ምክንያት የመኖሩ ምክንያት ሰፊ ነው። ደስታ በሚል ስም የሚጠራ የአጸደህጻናት ተማሪ ህጻን መምህርቱ ለምን ደስታ እንደተባለ ትጠይቀዋለች። ለጥያቄው የህጻኑ ምላሽ ዝምታ ነበር። በሌላ ቀንም በተመሳሳይ ሁኔታ መምህርቷ ህጻኑን ትጠይቀዋለች፤ በዚህ ጊዜ ህጻኑ ተማሪ ምላሽ መስጠት የሚያስችለው አቅም በማጣቱ ፊቱን አዞሮ አንገቱን ደፋ። የህጻኑ ሁናቴ ትኩረቷን የሳበው መምህርት ከህጻኑ ቤተሰብ መስማት እንዳለባት ታስብና ወላጆቹን ታስጠራለች።

በጥሪው መሰረት የልጁ እናት እንደሆነች በቅጽ ላይ ስሟ የተጠቀሰ እናት ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ይገኛሉ። መምህርቷም ህጻኑ ላይ የምታየውን ሁኔታና ለዚህ እንደ መነሻ የወሰደችው የህጻኑን የስሙን ጉዳይ መሆኑን አስረዳች። መምህርቷም “ከልጅዎ ስም ጋር በተገናኘ ልጅዎትን ስሜታዊ የሚያደርገው ጉዳይ ምን ይሆን?” ስትል በትህትና ጠየቀች። በተመሳሳይ ሁኔታ እናት ምላሽ ከመስጠት ዘገየች። በዝምታ ውስጥ ተዋጠች። አይኖቿን እምባ ሞሉት። ከለቅሶ በኋላም መናገር ጀመረች።

“የደስታ እናት እኔ አይደለሁም። እኔ አሳዳጊው ነኝ፤ የእናቱ እህት ወይንም የደስታ አክስት። እናቱ በህይወት የለችም። እናቱ በገጠማት የጤና ችግር ምክንያት ከደስታ መወለድ ጋር በተገናኘ ህይወቷን አጥታለች። ዶክተሮቹ ከእናቲቱ ወይንም ከልጁ አንዱን ማዳን ይችሉ ነበር። እናት ምርጫዋ ልጇን ማዳን ሆነ። ለልጁ ደስታ የሚል ስም አወጣችለት። ‘ደስታ ህይወቴን ሰጥቼሃለሁ፤ አንተ በደስታ ኑር፤ ህጻን ብትሆንም በአይኔ አይቼህ ባላውቅህም የአንተን ህይወት መስዋእት አድርጌ የእኔ መኖርን አልመረጥኩም’ አለች። ለልጇም ማስታወሻ ጽፋ አለፈች። ልጁም ተወለደ፤ ይህን ታሪክም ቀስ በቀስ እየሰማ እንዲያድግ አባቱ ስለፈለገ አባቱ ነገረው። እናቱን ባሰበ ጊዜ ስለተደረገለት ስጦታ ይገረማል። በልጅነት አዕምሮው ይህን ታሪክ መነገሩ ትክክል ባይመስለኝም እውነታው ግን ይህ ነው።” አለች።

መምህርቷ ይህን ታሪክ ስትሰማ ተረበሸች፤ በእርሷ ህይወት ውስጥ የሚቆጫትን አንድ የታሪኳን ገጽ አስታውሳት፤ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለች ያስወረደችውን ጽንስ። “በቅድሚያ ማርገዝ አልነበረብኝም፤ ከተረገዘ በኋላ ግን ማስወረድ አለነበረብኝም” ብላ አምርራ ትጸጸታለች። ውርጃውን በፈጸመች ጊዜ በህልም የሚያምር ህጻን እየመጣ “ለምን አልፈልግህም አልሺኝ?” እያለ ይጠይቃትም ነበር። አንዳንድ ቀን ደግሞ ከብዙ ህጻናት መካከል አንዱን ህጻን ነጥላ አውጥታ ስታባርረውና መጨረሻ ላይ ገደል ውስጥ ሲገባ እርሷ ግን ተረጋግታ ለመራመድ ስትሞክር ነገርግን ስትረበሽ ትመለከት ነበር።

የደስታ አክስት ለመምህርቷ ታሪኩን ከነገረች በኋላ ደስታን ሰላም ብላ ወደ ቤት ተመለሰች። መምህርቷም ለራሷ ‘ሁሉም ቤት ለካንስ የተለያየ ታሪክ አለ፤ አንዳንዱ ቤት የጭካኔ ሌላው ቤት ደግሞ የርህራሄ። እኔ ቤት ያለው የጭካኔ ነው’ ብላ እንደተለመደው ራሷን ወቀሰች። በእምባ በታጀበ አይኗ ሆኖ ወደ ተማሪዎች ስትመለከት ደስታ ከተማሪዎች ጋር እየተጫወተ ነው። እርሱ ዛሬ ልጅነቱን ይኖር ዘንድ መስዋእት የሆነችውን እናት አሰባት። መስዋእትነቱ ቀጥሎ የእህቷን ልጅ የምታሳድገው አክስትም። ደስታን በምን ...?

ደስታን በምን እንፍጠር፤ ደስታን በምን እናብዛ፤ ደስታን በምን እናጋባ፤ ደስታን በምን እንጠብቅ በሚሉ የጥያቄ ዝርዝር ውስጥ ሆነን ቀጥሎ ያለውን ክፍል እናንብብ። በቅድሚያ ግን ለራሳቸው መቆም ለማይችሉቱ እንዴት ደስታ መሆን እንደሚቻል የማሰብን አስፈላጊነት እናስብ።

### እናት ስለማታውቀው ደስታ

ደስታን ስናስብ ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ መሆንን እናስብ። የሚባዛ ደስታ ስለሌሎች ሲሆን በዋናነት ደግሞ ስለራሳቸው መናገር ስለማይችሉቱ። ስለራሳቸው መናገር የሚችሉት አካላት የሚባሉ አካላት ድምጽ የሌላቸውን ድምጻቸውን ሊያፍኑ ይችላሉ፤ እንዲሁም ድምጽ መሆንም ይችላሉ። ድምጽ ያላቸው በትክክለኛው ቦታ ላይ ድምጽ መሆን እንዲችሉ ማሰቡ አስፈላጊ የሚሆነው ለእዚህ ነው። ድምጽ ያላቸው ሰዎችን ማወቅ፣ መቅረብ፣ ድምጽ ስለሌላቸው ማስረዳትና ድምጽ ማድረግ ስራውን ፍሬያማ ያደርገዋል።

በዙሪያችን ያሉ ስለራሳቸው ምንም ማድረግ የማይችሉትን ማወቅ ወይንም መረዳት ቀዳሚው የደስታ ምንጭ ነው። በራሳችን ጫማ ሆነን ስናስብ በፈጣሪ ዘንድ የምንታየው ማድረግ በምንችለው ደረጃ ነውና እርሱን ማሰብ አለብን። አንድ ህጻን ልጅ ከአንድ አዋቂ ጋር እኩል ልናይ አንችልም፤ ወጣትን ከ ባልቴት ጋር እኩል ልናይ አንችልም፤ ድምጽ ያላቸውን ከሌላቸው የምናይበት ብዙ መንገድ አለን። ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ ለመሆን የምናወጣው ሃብት ውስን በመሆኑ ድምጽ የሌላቸውን መለየት ያስፈልጋልና ትኩረታችን ይሰጠው።

በመቀጠል ደስታን ለመጠበቅ የሚረዳንን ነጥብ እናንሳ። ከጎደለው ይልቅ የሞላውን የመመልከት አተያይ።

### የሞላውን መመልከት

እንደ አንድ ዜጋ በአገራችን ውስጥ የጎደለን ነገርን እንዘርዝር ብንል መዳረሻችን ቀላል አይመስልም። የተወሰኑትን እንጥቀስ ብንል ድህነት፣ የትምህርት ተደራሽነት፣ ጎጂ ባህሎች፣ የሴት ልጅ መደፈር፣ የሥራአጥ ቁጥር፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ወዘተ ብለን ልንዘረዝር እንችላለን። ለእያንዳንዱ የጉድለት ዝርዝር ተገቢውን መፍትሄ የመፈለጉ ሂደት ስንገባ የመሰረት ጉዳይ አግጦ ይወጣል።

የጎደለው ሰላም ከሆነ የውስጥ ሰላም ያላቸው ሰዎች መብዛት የመፍትሄው መንገድ እንደሆነ ማህተመ ጋንዲ ይናገራሉ። “በአገራት መካከል ሊኖር የሚገባ ሰላም በግለሰቦች መካከል ባለ መሰረት ያለው ፍቅር ይመሰረታል” ይላሉ ማህተመ ጋንዲ። አገራት የግለሰቦች ስብስብ ናቸው። ግለሰቦች በውስጣቸው የሚሆን ሰላምና ፍቅር መሰረት ሆኖ ወደ ሰላም ያደርሳል። እያንዳንዱን ግለሰብ የሰላም ሰው አድርጎ የማሳደግ በድምር ውጤቱ የአገርን እንዲሁም የአገራትን ሰላም መጠበቅ ነው። ይህም ደስታን ለመጠበቅ እንዲሁም ለማብዛት የራሱን አስተዋጾ ይኖረዋል።

በሳሙኤል አዳምስ አገላለጽ ደግሞ “ለህዝብ ነጻነትና ደስተኝነት ሃይማኖትና የሞራል ሰው መሆን ጥብቅ መሰረት ነው።” ደስታን ለማግኘት ከጉድለት በላይ የሞላውን ለማየት ከተለመደው ስሌታዊ ኑሮ ወጥቶ የእምነትን ወይንም የሃይማኖትን መንገድ ማሰብ ተገቢነት እንዳለው የሚያስረዳ አባባል ነው።

የጉደለውን ነገር በሚገባ ዘርዝሮ ማስረዳት ለሁላችንም የቀለለ ይመስላል። የመፍትሄ መንገዱን ግን መፈለግ ለሁሉም ቀላል ነው፤ እርሱም መሰረትን መመስረት ነው። መሰረቱ ጠንካራ በሆነ ቁጥር የሚታነጽበት ከፍታው ይጨምራል። ከህንጻው ውጫዊ ውበት በላይ ሸክምን በመሸከሙ የምንደነቅበት መሰረቱ ላይ ነው።

አተያይን ከጎደለው ወደ ሞላው በማድረግ፤ ላለን ነገር ቦታን በመስጠት ደስታን እናብዛ። አጠገባችን ያለው ሰው ከጎደለው ይልቅ ያለውን ነገር እንመልከትለት። እምቅ አቅምን በመረዳት ውስጥ የሚፈጠር ደስታ።

### አቅምን በመመንዘር

ማንም ተራ ሰው በምድር ገጽ ላይ የለም። በትላንት መንገድ አቅማችን እንደምንጠብቀው የተመነዘረ ላይሆን ይችላል። ነገርግን ደስታን ከመፍጠርና ከማብዛት አንጻር ሊሆን ግን እድል አለው። ደስታን ማብዛት ሲታሰብ የሚሆነው ሌላ ነገር እምቅ አቅምን ማውጣት መቻል ነው። ሰው እምቅ አቅሙን በአግባቡ ማውጣት የሚችልበት እድልን ቢያገኝ ውጤታማ መሆኑ ጥርጥር የለውም። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የወጣት አገር ውስጥ እምቅ አቅምን ማውጣት አለመቻል ከአገር እድገት አንጻር ያለው ኪሳራ ከፍተኛ ነው። ከኪሳራውም መካከል ደስታ የራቀው ህዝብ መብዛት አንዱ ነው። የሰው ኃይል አንዱ የኢኮኖሚ ማሳለጫ ግብዓት በመሆኑ እምቅአቅምን ወደ ውጤት መቀየር የመቻል አካሄድ ትርጉሙ ላቅ ያለ ነው። ጠንካራ የሰው ሃይል ሲኖር ሌላውን የኢኮኖሚ ማሳለጫ ካፒታልን፣ መሬትን እንዲሁም ቴክኖሎጂን የሚያንቀሳቅስ ሆኖ እናገኘዋለን።

እምቅ አቅማችን እንዲወጣ የሚፈልገው አጋጣሚ አለ። ያን አጋጣሚ ዛሬ ያለበት የምቾት ቀጠና መዳረሻችን አድርገን ልንይዘው አይገባም። በመሆኑም እምቅ አቅማችንን ለማውጣት ስናስብ መገፋትን አብረን ልናየው እንችላለን። በመገፋት ምክንያት እምቅ አቅማቸውን የሚገድሉትን አይተን ይሆናል። በመነሻ ታሪካችን ላይ ያለው ደስታ ከተደረገለት ታላቅ ስጦታ ተነስቶ እርሱም በጊዜው እምቅ አቅሙን ለመልካም ነገር ሊያውለው ራእይ ይሰንቅ ይሆናል። በደስታ ውስጥ ያለው ሃዘንም እንዲሁ ሌላ አቅም ነው። ጆን ስትሪልንግ የተባሉ ሰው እንዲህ አሉ “ሃዘን የራሱ የሆነ ውድ የሆነ ሃሴት ነው፤ መንቀሳቀስ ሲጀምር ጠንካራ የሆነ የህይወት ውስጣዊ ክፍል መንቀሳቀስ ይጀምራል።” ትላንት ውስጥ የመጣንበት ሃዘንም እንዲሁ ጠንካራ የሆነውን ውስጣዊ ክፍላችንን ያንቀሳቅሰዋል። አንቀሳቅሶትም ለአላማችን ጨካኝ ሊያደርገን ይችላል፤ በፈተና ውስጥ ጥርሳችንን ነክሰን በጽናት እንድንቆም እንዲሁ።

ልንረዳው የሚገባ እውነት እምቅ አቅም የሌለው ሰው የለም። ሁሉም ሰው ሊወጣና ሊመነዘር የሚችል እምቅ አቅም አለው። አቅሙን እንዴት ባለመንገድ ማውጣት እንዳለበት መረዳት አይኖረው ይሆናል እንጂ አቅም ሳይኖረው የሚኖር ሰው የለም። ሃዘን ከሌለ ዘምባባ የለም፤ ወጀብ ከሌለ ዙፋን የለም፤ የሚያበሳጭ ሳይኖር ክብር የለም፤ መስቀል ሳይኖር አክሊል የለም ብለን ስናስብ የሚገጥመን እያንዳንዱ መገፋት ወደ ተሻለ ነገር ሊያስገባን ዋዜማው ላይ እንዳለን እንረዳለን።

እምቅ አቅም መውጣት ሲጀምር ለውጥ በህይወታችን እንዲሁም በሌሎች ፊት ይሆናል። እምቅ አቅምን በሌሎች ጫማ ውስጥ ለመቆም መጠቀም ደግሞ ወሳኙ ተግባር ነው። ሌሎች እምቅ አቅማቸውን አውጥተው እንዲመነዝሩት በማድረግ ደስታን የሚያበዛ።

### አንዳችን በሌላችን ጫማ ውስጥ

መዳረሻችን ደስታ የሞላበትን ግለሰባዊ፣ ቤተሰባዊ፣ ማህበረሰባዊ ኑሮን መኖር ከሆነ ለሌሎች በመኖር ውስጥ ደስታን መፈለግ አለብን። ይህም አንዳችን በሌላችን ጫማ ውስጥ በመኖር የሚገለጽ ሆኖ እናገኘዋለን። በመጪው ህዳር ወር የሚጀመረውን አገራዊ መግባባት ስናስብ እንደ አገር መግባባት እንዲሆን የምናሻው ነገር እንዳለ ሆኖ አድካሚ ጉዞ የሚጠብቀን መሆኑ ግን አያጠያይቅም። አንዳንዶች የአገራዊ ምክክር ሂደቱ አስር አመት ሊፈጅ ይችላሉ ሲሉም ከወዲሁ ሲገምቱ እናደምጣለን። አስርም አመት ይፍጅ ሦስት አመት ቀላል ሂደት አለመሆኑ ግን ለሁላችንም ግልጽ ይመስላል። የተለየ ሃሳብን ሰምቶ ማስተናገድ የሚያስችል ባህል በሌለን ሁኔታ ውስጥ ሆነን ሳለ ሂደቱ ቀላል ሊሆን እንደሚችል አናስብም። መፍትሄ የሌለው ስጋት ግን አይደለም። አንዳችን በሌላችን ጫማ ውስጥ መሆንን እሴት ባደረግን ጊዜ ወደፊት ማለትን እንችላለን፤ ምክክሩ ወደ ማህበረሰባዊ እድገትና ሰላም ሊያደርሰን ይችላል።

አንዳችን በሌላችን ቁስል ውስጥ ስንሆን በመረዳዳት ላይ የተመሰረተ መቀራረብ መፍጠር እንችላለን። ይህም ወደ ማህበረሰባዊ ደስታ ያደርሰናል። ችግርን እንኳን በሚዛኑ በመዳኘት ችግርን በፍጥነትና በጥራት እየፈቱ አንዱ ስለሌላው እየኖረ በጋራ ደስታን የሚፈጥሩበት፤ የሚጠብቁበት ህይወት።

### ችግርን በብልሃት

የደስታ ተቃራኒው ሃዘን ነው። ሃዘን ደግሞ ማንም አይፈልገውም። በችግር ውስጥ አልፎ መገኘት ፍላጎታችን ባይሆንም የምናልፍበት ግን ነው። ደስታን ማብዛትን ስናስብ፤ ደስታን መጠበቅን ስናስብ ችግርን የምናይበትንና የምንፈታበትን መንገድ እያሰብን ነው።

የደስታ ሰዎች ችግርን ሲፈቱ ግለሰቡን ከችግሩ ለይተው ይመለከታሉ። ግጭት የሚመጣው በሰው በኩል መሆኑ ግልጽ ነው። ነገርግን ግጭትን ለመፍታት እንቅስቃሴ ስናደርግ የግጭቱ ምክንያት የሆነው ነገር ላይ በማተኮር መፍትሄን መስጠት። ይህ መንገድ ደስታን ቶሎ ለመመለስና ለማጽናት ይረዳል። ነገሮችን ከገለልተኛ አቅጣጫ ማየት ሌላው የጠፋብንን ደስታ መልሰን እንድናገኝ በሚያደርግ ሁኔታ ችግርን ለመፍታት የሚረዳ ነው።

በሆነ ነገር አተያያችን ሚዛናዊ ካልሆነ ወይንም ገለልተኛ ካልሆነ ሙሉ ምስሉን ማግኘት ስለማንችል አስቸጋሪ ቢሆንም በገለልተኛ ሜዳ ላይ ራሳችንን ብናስቀምጥ ወደ ደስታችን ያደርሰናል። ደስታችንን ከነጠቀው ከችግሩ ይልቅ የመፍትሄን መንገድ ማየት ላይ ማተኮር ሌላው የችግርን በብልሃት ነጥብ ነው።

ሁልጊዜ በተለመደው መንገድ ውስጥ ብቻ ነገሮችን ማድረግን ከማሰብ፤ ከተለመደው መንገድ ውጭ መፍትሄ ሊኖር እንደሚቻል ማመን ያስፈልጋል። ችግርን ለመፍታት ስንነሳ አማራጭ የችግር መውጫ ሃሳቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ በማመን መንቀሳቀስ ተገቢነት ይኖረዋል። ግጭቱ መፍትሄ የሌለው አድርጎ ከመቁጠር ይልቅ የመፍትሔ መንገዶችን ሊኖሩ እንደሚችሉ አስቦ መንገዶችን በመፈለግ መስራትን ይጠይቃል። የመጀመሪያውም ሁለተኛውም የዓለም ጦርነት ከችግሩ ይልቅ መፍትሄው ላይ በማተኩር መንገድ ወደ እልባት መድረስ ትምህርት የተወሰደባቸው ናቸው። ችግር ውስጥ በመቆየት ሰፊ ውድመት ይከተል ይሆናል እንጂ ወደ መፍትሄ አያደርስም። ዛሬም ደስታችንን ለመጠበቅና ለማብዛት ከችግሩ ውስብስብነት ይልቅ የመፍትሄ መንገድ ላይ እናተኩር። ችግሩ አስሬ ቢወራ በራሱ መፍትሄ አይደለምና።

አስቸጋሪ ቢሆንም ሰላማችንን ለማግኘት ደስታችንን ለመጨመር መፍትሔዎች ላይ ለመስማማት አስተዋጾ ማድረግ አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ሰዎች ግጭት ለመፍታት ተነስተው ነገርግን የመስማሚያ ነጥቡ ላይ በአቋም መድረሳቸውን መቀበል ሳይፈልጉ ይታያሉ። ነገርግን ብዙ አማራጮችን ካዩ በኋላ ወደ መፍትሄ የደረሱበትን መንገድ ተቀብሎ እውቅና መስጠት ተገቢ ነው። መፍትሔ ላይ ተደርሷል ተብሎ ነገርግን በቀጣይ እዚያው ቦታ ላይ በመገኘት ችግሩ እንዲያገረሽ የሚያደርገው የተወሰደው የመፍትሔ መንገድ ላይ እውቅና አለመስጠት ሲሆን ነው። ስለሆነም መፍትሔ ላይ የተደረሰበትን ነጥብ እውቅና ሰጥቶ መነሳት ተገቢነት ይኖረዋል።

ዛሬ ደስታችንን ፈትሸን ደስታችንን ላይ የተፈጠረ ችግር ካለ ምንጩን እንፈትሽ። የምናገኘውም ምላሽ ደስታን በምን ብለን የጠየቅናቸውን ጥያቄዎች የሚመለስ ይሁን። ደስታ ከውስጥ የሚመነጭ ስለሆነ ከውስጣችን ሰላም ጋር እንስማማ። ሌሎችን እንደ እራሳችን ቆጥረን በመቀበል ሳይሆን በመስጠት ውስጥ የደስችንን ትርጉም እናስፋ። ዛሬም ሆነ ነገ የደስታ ሰዎች ሆነን እንድንገኝ ለሁላችሁ መልእክቴ ይህ ነው።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

## ስኬትን ያጎናፀፈ የነፍስ ጥሪ

ፍሬሕይወት አወቀ



ወይዘሮ ፍቅርተ ታደሰ



ጋርመንቱ ዩኒፎርሞችንና የወንድ ሸሚዞችን ያመርታል

በደቡብ ጎንደር ደብረ ታቦር ከተማ ነው ተወልዳ ያደገችው። የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷንም በዚያው አካባቢ ተከታትላለች። ወደ አዲስ አበባ አቅንታም በቀድሞው ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአሁኑ ሜትሮ ፖሊቲያን ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ድግሪዋን አግኝታለች። የቢዝነስ ማኔጅመንት ትምህርቷን በመከታተልም ሁለተኛ ዲግሪዋን መያዝ ችላለች።

አጠር ያለው ቁመቷ ቀጠን ካለው ሰውነቷ ጋር ተደምሮ ቀልጠፍ ያለ እንቅስቃሴ እንዲኖራት አግዟታል። ለተመለከታት ገና በቤተሰብ ቁጥጥር ያለች ትመስላለች፤ የአንድ ድርጅት ሠራተኞችን የምታስተዳድርም አትመስልም፤ ይሁን እንጂ እሷ ግን ቤተሰብ ከማስተዳደር ባለፈ ድርጅት የምትመራ ናት፤ የፍቅር ጋርመንት ድርጅት ባለቤትና ስራ አስኪያጅ ወይዘሮ ፍቅርተ ታደለ።

በ30ዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ የምትገኘው ወይዘሮ ፍቅርተ ባለትዳርና የሶስት ልጆች እናት ናት። ከፍተኛ የሥራ ሞራል አላት፤ ነገ ትልቅ ደረጃ ለመድረስ ብዙ ተስፋ የሰነቀችና በየጊዜው ሥራዋን ለማዘመንና ለማሳደግ ጥረቶችን የምታደርግ ናት። ወይዘሮ ፍቅርተ በጋርመንትና ጨርቃጨርቅ የሥራ ዘርፍ ውስጥ ከትንሽ ተነስታ ትልቅ ቦታ የደረሰችበት መንገድ እንዲሁም እየሠራቻቸው ያሉት አዳዲስና ወቅታዊ ሥራዎቿ ለሌችም ተሞክሮ ይሆናሉ ብለን የዕለቱ የስኬት እንግዳችን አድርገናታል።

የፍቅር ጋርመንት ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ፍቅርተ ታደለ፤ ገና ተማሪ እያለች የእጅ ሥራዎችንና ጥልፎችን ትሞክር ነበር። ሙከራዋንም የአስረኛ ክፍል ተማሪ በነበረችበት ወቅት በተግባር አውጥታ ማሳየት የምትችልበትን ዕድል በማግኘቷ ከትምህርቷ ጎን ለጎን ትርፍ ጊዜዋን ሁሉ የእጅ ሥራ በመሥራት ማሳለፍ ውስጥ ገባች። የመጀመሪያ ዲግሪዋን ባገኘችበት የመምህርነት ሙያም በኦሮሚያ ክልል ለሚ በቾ በሚባል ከተማ ለአንድ ዓመት ያህል አገልግላለች። ታዲያ በአንድ ዓመት የመምህርነት ቆይታዋም ጥሩ የምትለውን ጊዜ ማሳለፏን ታስታውሳለች።

ከአንድ ዓመት የመምህርነት ሥራ በኋላ ግን በውስጧ ያለውን የእጅ ሥራ በማሳደግ በጋርመንትና ጨርቃጨርቅ ዘርፍ ለመሰማራት ወስና የመምህርነት ሥራዋን በፈቃዷ ለቃ ፊቷን ሙሉ ለሙሉ ወደ ልብስ ስፌት አዞረች። ሥራዋን የለቀቀችው ወይዘሮ ፍቅርተ፤ በቀጥታ በጋርመንት ሥራ ተቀጥራ መስራት ጀመረች። በወቅቱም ያላትን አቅምና ችሎታ አውጥታ በመጠቀም ዘርፉ የነብሷ ጥሪ ስለመሆኑ ታረጋግጣለች። ከቅጥር በኋላም በዘርፉ ወደ ተሰማሩ ዘመዶቿ በመጠጋት በስፌት፣ በጥልፍ፣ በዲዛይንና በአስተዳደር ጭምር ሠርታለች።

በይበልጥ በአስተዳደሩ ላይ ሰርቻለሁ የምትለው ወይዘሮ ፍቅርተ፤ ከምታውቃቸው ሰዎች ጋር በሠራችበት ጊዜ በአስተዳደር ዘርፉ ላይ በዲዛይንና አዳዲስ ነገሮችን በመፍጠር ጥሩ ተሰጥኦ እንዳለት ተረዳች፤ በዚህም ሥራውን እንዴት ማሳደግ እንደሚቻል ያላትን ጥልቅ ዕውቀት ለመረዳት የሚያስችል ምቹ ሁኔታም ፈጠረላት።

በቆይታዋም ወደ አእምሮዋ የሚመጡ አዳዲስ ነገሮችን ወደ ሥራ በመቀየር ችሎታዋን በማዳበር አንድ እርምጃ ወደ ፊት የቀደመችው ወይዘሮ ፍቅርተ፤ የራሷን ሥራ ለመሥራት ሙከራ ላድርግ ብላ በግሏ ለመሥራት አምስት ሺ ብር ካፒታል በመያዝ ወደ ሥራው ገባች። በእጇ ያለውን ሙያ ተጠቅማ አንድ የስፌት መኪና ይዛ የተለያዩ አልባሳትን መስፋት ትጀምራለች፤ ፍቅር ጋርመንት በሚል የጀመረችው የጋርመንት ሥራዋ በአሁኑ ወቅት በተሻለ እንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ ሆኗል።

ተቀጥራ ትሰራ የነበረችው ወይዘሮ ፍቅርተ በፍቅር ጋርመንት በኩል በአሁኑ ወቅት ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል ለማስገኘት ችላለች። በፍቅር ጋርመንት የተማሪዎችን እና የመንግሥትና የግል ድርጅቶች የደንብ ልብሶችን /ዩኒፎርም/ እንዲሁም የወንዶች ሸሚዝ በስፋት ይመረታሉ። ዩኒፎርም ከምታቀርብላቸው ድርጅቶች መካከልም ሆቴሎች ቀዳሚ ሲሆኑ ለአብነትም ደብረዘይት ቶሚ ኢንተርናሽናል ሆቴል፣ አዲስ አበባ ከተማ ራዲሰን ብሉ ኢንተርናሽናል ሆቴል፣ ካፍቴሪያዎችና ሌሎችም ይገኙበታል።

በመደበኛነት ከሚመረቱት እነዚህ ምርቶች በተጨማሪም የህጻናት አልባሳትን በአዲስ መልክ ለማምረት ዝግጅቷን ያጠናቀቀችው ወይዘሮ ፍቅርተ፤ የህጻናቱ አልባሳትም ምቾት ያላቸው ስለመሆናቸው ትናገራለች። የህጻናቱን አልባሳት ለመሥራት ታዲያ ፈጠራን ከመጠቀም ባለፈ በተለያዩ ፊልሞች ላይ የሚታዩ አሻንጉሊቶች የሚለብሱትን በመመልከት ተመሳሳዩን ዲዛይን በማድረግ እየሠራች መሆኑን አጫውታናለች።

የህጻናቱ አልባሳት ምቾት ያለውና እንደሚፈለገው አይነት ተደርጎ የሚመረት በመሆኑ ብዙዎች ይፈልጉታል። ዘርፉ ብዙ ሥራ ሊሠራበት የሚችል ነውና በቀጣይም ይህንኑ የሕጻናት አልባሳት በስፋትና በጥራት በማምረት ከውጭ የሚገባውን ለማስቀረት የበኩሏን እንደምታደርግ ወይዘሮ ፍቅርተ ትናገራለች። ይህም የሚቻልና ቀላል እንደሆነ ነው ያስረዳችው።

‹‹ማንኛውም ምርት በጥራት ከተመረተ ህዝቡ ይወደውና ይቀበለዋል›› የምትለው ወይዘሮ ፍቅርተ፤ እርሷም ቅድሚያ ለጥራት ሰጥታ ማምረት በመቻሏ ገበያው ውስጥ በስፋት እየገባች መሆኑን ትናገራለች። ለአብነትም ባሳለፍነው የፋሲካ በዓል በኤግዚብሽን ማዕከል ምርቶቿን ይዛ በመቅረብ ጥሩ ገበያ አግኝታለች። በተለይም የወንዶች ሸሚዝ ጥራት ያለውን ምርት ባማረ አጨራረስ ማቅረብ በመቻሏ ሰፊ የገበያ ትስስር ተፈጥሮላታል።

ደንበኞቿ በጥሩ ሥራዎቿ አማካኝነት ሌሎች ደንበኞችን እየፈጠሩላት እንደሆነ ያነሳችው ወይዘሮ ፍቅርተ፤ በጨረታ ከምታገኘው ገበያ ይበልጥ በደንበኞቿ ምክንያት የምታገኘው ገበያ ሰፊ እንደሆነ ነው የምትናገረው። ለዚህም በየዕለቱ ጥራት ያለው ምርት ለማምረት በመትጋት ተወዳዳሪ ሆና ቀጥላለች።

ጥቂት የስፌት መኪናዎችን በመያዝ በኪራይ ቤት በ2005 ዓ.ም ወደ ጋርመንት ሥራው የገባችው ወይዘሮ ፍቅርተ፤ ሰሚት አካባቢ 250 ካሬ ሜትር ቦታ በሊዝ በመግዛት 190 ካሬ ሜትር የሚሆነውን ቦታ ሙሉ ለሙሉ ማምረቻ አድርጋዋለች። በዚሁ ቦታ ላይም የተለያዩ አውቶማቲክና ሲንግል የሚባሉ በድምሩ 60 ማሽኖችን በማቆም የጋርመንት ሥራዋን እያቀላጠፈች ትገኛለች።

የስፌት መኪኖቹ 50 ሲሆኑ፤ ስምንቱ ደግሞ ኢምብሮደሪ የሚባል ማተም የሚችሉ ዘመናዊ የስፌት ማሽኖች ናቸው። ይህ ዘመናዊ የህትመት ሥራን የሚያቀላጥፈው ማሽን በአሁኑ ወቅት ዘመኑ የደረሰበት ቴክኖሎጂ መሆኑን ነው የምትገልጸው። ማንኛውንም በኮምፒዩተር የተሠራለትን ዲዛይን በፍላሽ ተቀብሎ የሚፈለገውን ውጤት በልብሱ ላይ በክር መጥለፍ ይችላል። የቀረቡለትን የተለያዩ ክሮችን በቦታ በቦታቸው በማስገባት የሚፈለገውን አይነት ጥልፍ ይሰራል። ይህ ማሽንም አሁን ባለው ገበያ አንድ ሚሊዮን ብር ያወጣል። ማሽኑ በአንድ ጊዜ ስምንት ዲዛይን ማምረት ይችላል። ይህም ማለት አንድ ዲዛይን ስምንት ልብሶች ላይ አትሞ ያወጣል እንደማለት ነው።

በኪራይ ቤት ከአንድ ሁለት፤ አምስትና አስር ማሽን እያለች በአሁኑ ወቅት 60 ዘመናዊ የስፌት ማሽኖችን ማፍራት የቻለችው ወይዘሮ ፍቅርተ፤ 22 አካባቢ ጊዜያዊ የመሸጫ ቦታ አላት። በቅርቡም ሰሚት እና ቄራ አካባቢ ሌሎች የመሸጫ ቦታዎችን ለመክፈት አቅዳለች። በተለይም ባደረገችው የገበያ ጥናት መሰረት በአሁኑ ወቅት የህጻናት አልባሳት ኮንፈርት ተፈላጊ ነው፤ በዚህም ላይ በስፋት ወደ ማምረት መግባትና ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ የክልል ከተሞችም ለማከፋፈል በሚያስችላት ቁመና ላይ መሆኗን ነው የጠቆመችው።

ወይዘሮ ፍቅርተ እንዳለችው፤ በቋሚነት ለ30 ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር እንዲሁም ባመረቱት ልክ ለሚከፈላቸው 30 ሰዎች የኮንትራት ሥራም ፈጥራለች። ከአስተዳደር ሠራተኞች ውጭ በማምረት ሥራ ብቻ በድምሩ ለ60 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችላለች። በእዚህ የሰው ኃይል በቀን ከ500 እስከ 700 የሚደርሱ አልባሳትን ማምረት እንደሚቻል የምትናገረው ወይዘሮ ፍቅርተ፤ አንዳንድ ሥራዎች እጅ የሚይዙ ባይሆኑባት ድርጅቱ ከዛም በላይ የማምረት አቅም ያለው መሆኑን ትናገራለች።

በአስር ዓመት የጋርመንት ሥራ እንቅስቃሴዋ መሰረት በመጣል ውጤታማ መሆን የቻለችው ወይዘሮ ፍቅርተ፤ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ከዓለም አልፎ በአገሪቱ በተከሰተበት ወቅት ዘርፉ በተወሰነ መጠን ተቀዛቅዞ እንደነበር ታስታውሳለች። እንዲያም ሆኖ ግን እጆቿን አጣጥፋ አልተቀመጠችም፤ ፈተናውን እንደ መውጫ ተጠቅማበታለች፤ በወቅቱ አስፈላጊ የሆነውን የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ማምረት ውስጥ ገብታለች። ያመረተቻቸውን ጭምብሎችም ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት በወረዳ አማካኝነት በአካባቢው ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ ማድረግ ችላለች። ለመከላከያ ድጋፍ በማድረግ፣ ለአባይ ቦንድ በመግዛትና በሌሎችም አገራዊ ለሆኑ ጥሪዎች ምላሽ በመስጠት ማኅበራዊ ኃላፊነቷን እየተወጣች ትገኛለች።

ወይዘሮ ፍቅርተ በተለይም በውጭ ምንዛሬ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ አልባሳት በአገር ውስጥ ምርት መተካት እንደሚቻል ታስገነዝባለች። ጥራት ያለው ምርት በተገቢው መጠን በማምረት እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለማህበረሰቡ በማቅረብ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን ምርት ማስቀረት ባይቻል እንኳን የመቀነስ ፍላጎት አላት። በዚህ በኩል ብዙ ሊሠራበት እንደሚገባም ነው የምትመክረው።

በአምስት ሺ ብር የጀመረችው የጋርመንት ሥራም በአሁኑ ወቅት ከሃምሳ ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል ማፍራት አስችሏታል። በአሁኑ ወቅትም የኢንቨስትመንት ፈቃድ በማውጣት ፋብሪካ ለመገንባት በሂደት ላይ ናት። ፋብሪካ በመገንባት ሰፊ ቁጥር ላለው የሰው ኃይል የሥራ ዕድል በመፍጠር ትርጉም ያለው ሥራ ሠርታ አገሯን የማስጠራት ራዕይም አላት። ይህን ራዕይ ለማሳካትም በተለይም ጥራት ላይ ትኩረት አድርጋ እየሰራች መሆኑን ትገልጻለች።

የአገር ውስጥ አልባሳት በብዛት አጨራረሳቸው ያማረ እንዳልሆነም ጠቅሳ፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ ያለውን ክፍተት ለመድፈን ዘመናዊ ማሽን ከመጠቀም ጀምሮ የጥራት ተቆጣጣሪዎችን በመቅጠር ውጤቱን ማምጣት እንደሚቻል ታስረዳለች። ‹‹የምንጠቀማቸው ማሽኖች ደረጃቸውን የጠበቁና ሲሰፋባቸው ክር የማያዝረከርኩ ጥርት አድርገው የሚያወጡ ናቸው›› የምትለው ወይዘሮ ፍቅርተ፣ እነዚህን ማሽኖች በመጠቀም እንዲሁም በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይልን በማሳተፍ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ነው የምትናገረው። በአሁኑ ወቅት ያለው ዘመናዊ የስፌት ማሽንም መሰል ችግሮችን ሊያቃልል እንደሚችል ጠቁማለች።

በአገር ውስጥ የተመረቱ አልባሳት የሌሎች አገራትን ስም ለጥፈው ለገበያ እንደሚቀርቡም ተናግራ፣ የፍቅር ጋርመንት ምርቶች በሙሉ ፍቅር በሚለው የንግድ ምልክት ስም ብቻ የሚወጡ እንደሆኑ አጫውታናለች። ማህበረሰቡ ለውጭ አልባሳት ፍላጎት ቢያሳድርም በጥራት ሠርቶ ማሳመን ያስፈልጋል የምትለው ወይዘሮ ፍቅርተ፣ ይህም ጊዜ ሊወስድ ይችል ይሆናል እንጂ ተቀባይነቱ ይመጣል ባይ ናት። ያኔ የአገር ውስጥ ምርትን ከመጠቀም ባለፈ አገርን በማስተዋወቅ በኩልም የላቀ ድርሻ ይኖረዋል ትላለች።

ለአብነትም በአሁኑ ወቅት በስፋት እየገባችበት ያለው የህጻናት ኮንፈርት እጅግ ውብና ማራኪ እንደሆነ ገልጻ፣ ከውጭ አገር ከሚመጣው ምንም ልዩነት የሌለው ስለመሆኑም ነው የምትናገረው። ይህ ምርቷን እጅግ ተፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ ለክልሎች ጭምር ለማከፋፈል ዝግጁ ናት።

በአልባሳት ዘርፉ በስፋት የተሰማሩት ሴቶች መሆናቸውን በመጥቀስ እነዚህ ሴቶች የግል ቢዝነሳቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ከመንግሥትም ይሁን ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ቢገኝ መልካም መሆኑን አስገንዝባ፣ በርካታ ተደብቀው ያሉና ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ የሚችሉ ሰዎች ስለመኖራቸውም ትናገራለች። እነዚህ ያልታዩ ሰዎችን ማየት ከተቻለ አቅማቸውን በመጠቀም ዘርፉን ማሳደግ እንደሚቻል ነው የምትመክረው።

‹‹ጊዜዬን በአግባቡ ተጠቅሜ ውጤታማ መሆን ችያለሁ›› የምትለው ወይዘሮ ፍቅርተ፤ ለጊዜ ትልቅ ቦታ ያላት በመሆኑ ወጣቶችም ወጣትነታቸውን በአግባቡ ተጠቅመው ካሰቡት እንዲደርሱ ታስገነዝባለች። የተለያዩ ፈታኝና አስቸጋሪ ሁኔታዎች ቢገጥማቸውም ተስፋ ሳይቆርጡ ከጣሩ ማንኛውንም ችግር ማለፍ ይችላሉ ስትል ከተሞክሮዋ ባጋራችው ሀሳብ አበቃን።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ አሰራር የሚሻው የመዲናዋ የመንገዶች ግንባታ

መላኩ ኤሮሴ



የመንገድ ግንባታዎች የሀገር ልማት መሆናቸውን ተገንዝቦ በተያዘላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ አብሮ መስራት ይገባል፤

ባለፉት ጥቂት ዓመታት የአዲስ አበባ ከተማን የመንገድ ሽፋን የሚያሳድጉና የተቀላጠፈ የትራፊክ ፍሰት እንዲኖር የሚያስችሉ የመንገድ ግንባታዎች በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች ተከናውነዋል። ባለፈው በጀት ዓመት ብቻ 24 የሚደርሱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ግንባታ ተጠናቀው ለአገልግሎት ክፍት መደረጋቸው ይታወሳል። በተያዘው በጀት ዓመትም የከተማዋ መንገዶች ባለስልጣን በርካታ መንገዶችን አጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት አድርጓል።

ተጨማሪ የመንገድ ግንባታዎችን አጠናቆ ለትራፊክ ክፍት ለማድረግ ርብርብ እየተደረገ ነው። በድምሩ ከ100 በላይ መንገዶች በአሁኑ ወቅት ግንባታቸው እየተከናወነ መሆኑን የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን መረጃዎች ያሳያሉ። የመንገድ ፕሮጀክቶቹ በተለያየ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው።

ፕሮጀክቶቹ የደረሱበት ደረጃ እንደፕሮጀክቶቹ የተለያየ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ የተሻለ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ እንደሚገኙ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ አፈጻጸማቸው መካከለኛ ደረጃ ላይ መሆናቸውንና መጓተት የታየባቸውም እንዳሉ የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ኢያሱ ሰለሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያብራራሉ።

ለመንገዶች ግንባታ መጓተት መንስኤ የሚሆኑ በርካታ ምክንያቶች እንዳሉም ጠቅሰው፣ ዋንኛው ምክንያት ግን የወሰን ማስከበር ችግሮች መሆናቸውን ይጠቅሳሉ። አንዳንድ ፕሮጀክቶች በተመሳሳይ ወቅት ተጀምረው፣ ከወሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ ባሉ ጉዳዮች ምክንያት የፕሮጀክቶች አፈጻጸም እጅግ የተራራቀ ሆኖ ይታያል ይላሉ። የወሰን ማስከበር ችግር ያላጋጠማቸው ፕሮጀክቶች ግንባታ በከፍተኛ ፍጥነት ሲከናወን የወሰን ማስከበር ችግር ያጋጠማቸው ፕሮጀክቶች ግን ከፍተኛ መጓተት እየተስተዋለባቸው መሆኑን ያብራራሉ። ይህንንም በተመሳሳይ ወቅት ተጀምረው አፈጻጸማቸው በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሁለት ፕሮጀክቶችን ለአብነት በማንሳት ምክትል ሥራ አስኪያጁ ያስረዳሉ። እንደ እሳቸው ገለጻ፤ እነዚህ ፕሮጀክቶች ከአሌክሳንደር ፑሽኪን ተነስቶ በቄራ ወደ ጎተራ ማሳለጫ የሚሄደው የመንገድ ፕሮጀክት እና አውቶብስ ተራ - መሳለሚያ - 18 ማዞሪያ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ናቸው። ሁለቱም ፕሮጀክቶች በ2012 ዓ.ም የተጀመሩ ናቸው። ሁለቱም ፕሮጀክቶች የረጅም ጊዜ የመንገድ ግንባታ ልምድ ባላቸው ተቋራጮች ነው ግንባታቸው እየተከናወነ ያለው።

እንደ ምክትል ሥራ አስኪያጁ ገለጻ፤ በ2012 ግንባታው የተጀመረው ከአሌክሳንደር ፑሽኪን አደባባይ / ሳር ቤት / ተነስቶ በቄራ ወደ ጎተራ ማሳለጫ የሚሄደው የመንገድ ፕሮጀክት የዋሻ ውስጥ መተላለፊያን ጨምሮ ተሸጋጋሪ ድልድይና የፈጣን አውቶብስ መመላለሻ ኮሪደርን አካቶ እየተገነባ የሚገኝ ነው። ይህ የመንገድ ፕሮጀክት 3 ነጥብ 8 ኪሎ ሜትር ርዝመትና ከ30 እስከ 45 ሜትር የሚሆን የጎን ስፋት አለው። በአሁኑ ወቅት ከ90 በመቶ በላይ የግንባታ ሥራው ተጠናቋል። በከተማዋ በፍጥነት ከተከናወኑ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች አንዱ ነው። በቀጣይ ጊዜያት ቀሪ ሥራዎቹ ተጠናቀው ሙሉ በሙሉ ለትራፊክ ክፍት እንዲሆን ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ ነው።

የአውቶብስ ተራ - መሳለሚያ - አስራ ስምንት ማዞሪያ ፕሮጀክት ግን በተመሳሳይ በ2012 ዓ.ም በሁለት ዓመት ውስጥ ለማጠናቀቅ የጊዜ ቀጠሮ ተይዞለት ግንባታው የተጀመረ ቢሆንም፣ ሁለት ዓመት ከአምስት ወር ገደማ አስቆጥሮም ግንባታው ገና 12 በመቶ ላይ ይገኛል። ፕሮጀክቱ ከፍተኛ መጓተት ከታየባቸው የመዲናዋ የመንገድ ፕሮጀክቶች አንዱ ነው።

ለዚህ ፕሮጀክት መጓተት ዋነኛው ምክንያት ደግሞ የወሰን ማስከበር ችግር ነው የሚሉት አቶ ኢያሱ ፤ እስካሁን ድረስ ከአውቶብስ ተራ ወደ መሳለሚያ ባለው ወደ 800 ሜትር የሚደርስ የመንገድ ክፍል የመጀመሪያ ደረጃ አስፋልት ለማልበስ ጥረት የተደረገ ቢሆንም ፤ ከዚያ በኋላ ባለው የመንገዱ ክፍል ላይ ሰፊ የወሰን ማስከበር ችግሮች አጋጥመዋል ይላሉ። የወሰን ማስከበር ችግሩ ከግለሰብ የመኖሪያ ቤቶች ጀምሮ የመንግሥት የልማት ተቋማት መሰረተ ልማቶችን በጊዜው ባለማንሳታቸው የመንገድ ግንባታውን በተያዘው የጊዜ ቀጠሮ መሰረት ሊከናወን አለመቻሉን አቶ እያሱ ያነሳሉ።

እንደ አቶ እያሱ ማብራሪያ ፤ መነሳት ያለባቸው የመንግሥት ልማት ተቋማት በጊዜው አለመነሳት በተለይም እንደ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ያሉ ተቋማት መሰረተ ልማቶች አለመነሳት የመንገድ ግንባታ ሥራው እንዳይካሄድ እንቅፋት ሆኗል። እንዲሁም የመኖሪያ ቤቶች እና የንግድ ድርጅቶች ያላቸው አካላት በጊዜው አለመነሳት ሌላኛው እንቅፋት ነበር። የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት የወሰን ማስከበር ችግሮች በመንገድ ግንባታ ሥራዎች ላይ እያሳደረ ያለው ተፅዕኖ ማሳያ ተደርገው ሊወሰዱ ከሚችሉ ፕሮጀክት አንዱ ነው።

የመኖሪያ ቤት እጥረት የመዲናዋ ትልቁ ችግር በሆነበት በዚህ ወቅት ቤት ለማግኘት ቆጥበው እየተጠባበቁ ካሉት የከተማዋ ነዋሪዎች ጎን ለጎን ለልማት ተነሺዎች ቤት ማቅረብ ለመንግሥት ፈተና ሆኖ ቆይቷል የሚሉት አቶ ኢያሱ፣ ለመንገድ ልማት ተነሺዎች ቤት ማቅረብ አለመቻል የልማት ተነሺዎችን ከሚኖሩባቸው አካባቢዎች በጊዜው ለማንሳት ፈተና ሆኗል ይላሉ። ለመንገድ ግንባታ ተነሺዎች ምትክ ቤትና ምትክ ቦታ ማቅረብ አለመቻል ተነሺዎችን ማንሳት እንዳይቻል አድርጎ መቆየቱን ጠቅሰው፣ የመንገድ ግንባታው እንዲፋጠን ምትክ ቦታና ቤት ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባሉ።

ምክትል ሥራ አስኪያጁ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት በሚመለከታቸው አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ወሳኝ መሆኑን አስታውቀው፣ የወሰን ማስከበር ችግርን ለመፍታት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የመንገድ ግንባታው የሀገር ልማት አካል መሆኑን በመገንዘብ ያለ ማንም ጫና መሰረተ ልማቶችን ሊያስነሱ ይገባል ሲሉ ያመለክታሉ።

በሌላም በኩል የሚገነባው መንገድ የመላው የከተማው ነዋሪ ሀብት መሆኑን በመገንዘብ የልማት ተነሺዎች ትብብር ሊያደርጉ እንደሚገባም ነው የሚያስገነዝቡት። ለእነዚህ አካላት ምትክ ቦታና ቤት የሚያቀርብ አካልም ለጉዳዩ ትኩረት በማድረግ ምትክ በመስጠት ተነሺዎቹ እንዲነሱ እና የመንገድ ግንባታው እንዲፋጠን ሊያደርግ ይገባል ብለዋል አቶ ኢያሱ።

እንደ ምክትል ሥራ አስኪያጁ ገለጻ፤ ከአውቶብስ ተራ- መሳለሚያ- 18 ማዞሪያ መንገድ በተጨማሪ በታቀደላቸው ጊዜ የግንባታ ሥራቸው ያልተከናወነ ሌሎች የተጓተቱ ፕሮጀክቶችም አሉ። ለአብነት የቃሊቲ ቱሉ ዲምቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት አንዱ ነው፤ ፕሮጀክቱ በ2009 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን በ2012 ዓ.ም ተጠናቆ ወደ አገልግሎት እንዲገባ ታቅዶ ለግንባታውም ሁለት ቢሊዮን ብር ተበጅቶለታል። በቻይና ኤግዚም ባንክ የበጀት ድጋፍ ከሚከናወኑ የመንገድ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ የሆነው በቂሊንጦ ፣ በቡልቡላ በኩል አድርጎ ቃሊቲ ማሰልጠኛ አካባቢ የሚገኝ የመንገድ ፕሮጀክትም የዚሁ አካል ነው።

የቃሊቲ ቱሉ ዲምቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ወደ 11 ኪሎ ሜትር ይሸፍናል። ከዚህ ውስጥ ሶስት ቦታዎች ላይ ከ240 ሜትር እስከ 50 ሜትር ርዝመት ያላቸው ሶስት የማሳለጫ ድልድዮችን ጨምሮ በቀኝ በኩል ያለው የመንገዱ ክፍል የመጀመሪያ ደረጃ አስፋልት ለብሶ አገልግሎት እየሰጠ ነው። ነገር ግን በመንገዱ ግራ ክፍል በኩል በተለይም በማሰልጠኛ በኩል ትልቅ የውሃ መስመር በመኖሩ ምክንያት የወሰን ማስከበር ተግዳሮት አጋጥሞ ነበር። የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ከረጅም ጊዜ መጓተት በኋላ በዚህ ዓመት የውሃ መስመሩን ቀይሯል።

ለረጅም ጊዜ ለመንገድ ግንባታው እንቅፋት ሆኖ የቆው ይህ የውሃ መስመር በመነሳቱ አሁን የመንገድ ግንባታውን ለማጠናቀቅ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ይላሉ። በዚሁ ሂደት ውስጥ በቻይና ኤግዚም ባንክ ለኮንትራክተሩ መከፈል ያለበት ባለመከፈሉ ከፋይናንስ ጋር ተያይዞ የገጠሙ ችግሮች እንዳሉም ይገልጻሉ። ይህንን ችግር ለመፍታትም የከተማ አስተዳደሩ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ በቅርቡ አንድ መፍትሄ ተቀምጦለት ወደ ግንባታ ይገባል ብለዋል።

በተለያዩ ምክንያቶች ሲጓተት የቆየው የኮተቤ- ካራ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት አንዱ መሆኑን ምክትል ሥራ አስኪያጁ ይጠቁማሉ። ኮተቤ ካራ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በ 2009 ዓመተ ምህረት መጨረሻዎቹ ወራት የተጀመረ መሆኑን አስታውሰው፣ ሙሉ ግንባታው በ3 ዓመት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ታስቦ እንደነበረና ግንባታው አስከ አሁንም እንዳልተጠናቀቀ ያብራራሉ።

እንደ አቶ ኢያሱ ማብራሪያ ፤ ለዚህ ፕሮጀክት ችግር መፍትሄ ለመስጠት ጥረት እየተደረገ ነው። መንገዱ ስድስት ኪሎ ሜትር አካባቢ የሚሸፍን ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ወደ 5 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር የሚሸፍነው የመንገዱ ክፍል ሙሉ በሙሉ አስፋልት ለብሶ አገልግሎት እየሰጠ ነው። በቀሪው አንድ ኪሎ ሜትር ውስጥ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት የመጀመሪያ 400 ሜትር መንገዱን የመጀመሪያ አስፋልት የማልበስ ሥራ እየተሰራ ነው።

600 ሜትር በሚሆን የመንገድ ክፍል ላይ በተለይ ከኮተቤ ሜትሮ ፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ወደ ካራ አካባቢ ያሉ ነዋሪዎች ያነሱትን ጥያቄ መመለስ ባለመቻሉ ግንባታው ሊጓተት ችሏል ይላሉ። ህብረተሰቡ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ምክንያታዊ ስለሆኑ ጥያቄዎቹን ሰምቶ መፍትሄ መስጠት አስፈላጊ ስለሆነ መፍትሄ የመስጠት ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው። መፍትሄ ከተሰጠ በኋላ ቀሪ ሥራዎችን ለመስራት ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

የወሰን ማስከበር ችግሮች በአፋጣኝ እልባት እንዳያገኙ የሚያደርገው አንዱ ምክንያት የፍርድ ቤት እግድ መሆኑን የባለስልጣኑ መረጃዎች ያሳያሉ። ከወሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ የሚነሱ አለመግባባቶች ወደ ፍርድ ቤት ሲወሰዱ ለረጅም ጊዜ ጉዳዩ እልባት ሳያገኝ የሚቀርባቸው ሁኔታዎች አሉ። በሌላ በኩል የካሳ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ቶሎ ለመነሳት ፈቃደኛ ያለመሆን አዝማሚያዎችም የመንገድ ፕሮጀክቶች እንዲጓተቱ ምክንያት ሲሆን ይስተዋላል።

በአጠቃላይ በመዲናዋ በመንገድ ግንባታ ዘርፍ የሚተስዋለውን የወሰን ማስከበር ችግር ለመቅረፍ ሁሉም አካላት በትብብር ሊሰሩ ይገባል። ፍርድ ቤቶችም ከወሰን ማስከበር ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ውዝግቦች በአጭር ጊዜ ውሳኔዎች የሚሰጥበትን አሰራር ቢከተል መልካም ነው።

የከተማዋ ነዋሪዎችም የመንገድ ግንባታዎች የመላው ከተሜ እና የመላ ሀገሪቱ ልማት መሆኑን በመገንዘብ ለልማቱ ያላቸውን ቀናዒነት ማሳየት አለባቸው። ለመንገድ ግንባታ ለሚነሱ የከተማዋ ነዋሪዎች ምትክ መሬትና ቤት የሚያቀርበው አካልም ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ ይገባል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ ለሰላሟም ለልማቷም ለምታርገው ጥረት እውቅና መስጠት ይገባል

አገር እንደ አገር ለመቀጠል ሰላም እና መረጋጋት በእጅጉ ያስፈልጋታል፤ ዜጎቿን ልታኖር የሚያስችላት የጠነከረ ኢኮኖሚም ሊኖራት የግድ ይላታል። የሰው ልጆችም በሕይወት ለመኖራቸው እንደ አንድ ምክንያት ከሚጠቀሱ ጉዳዮች መካከል አንዱ በልቶ የማደር ጉዳይ ሲሆን፤ ሌላኛው ከሰላምና ፀጥታ ጋር የሚጎዳኘው የደህንነታቸው ሁኔታ ነው። በዚህ ረገድ አገር እንደ አገር ልትቀጥል፤ የሰው ልጅን በሕይወት ለመኖሩ ምክንያት ከሚሆኑት ጉዳዮች መካከል ሰላም እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የጋራ አጀንዳዎች ሆነው እናገኛቸዋለን።

ዛሬ ላይ በአንድ በኩል በልጽገውና ሰላማቸው ሰፍኖ የምናያቸው አገራትና ሕዝቦች፤ በሌላ በኩል በድህነት እየማቀቁና በጦርነት እየታመሱ የምናስተውላቸው አገራትና ሕዝቦቻቸው የእነዚህ ሁለት ጉዳዮች ውጤቶች ናቸው። ሰላምና መረጋጋት ለአገርም፣ ለዜጎችም ትልቁና መሰረታዊ ነገር ነው። በአንጻሩ ኢኮኖሚያዊ አቅምን ማጎልበት እና የዜጎችን በልቶ የማደር ፍላጎት ማሟላት ለነገ ይደር የማይባል ወሳኝ ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው ሰላም የራቃቸው አገራት ለሌሎች ኃያላን መንግስታት በራቸውን ክፍት ሲያደርጉና ሉዓላዊነታቸውን ሲያስደፍሩ የሚስተዋሉት። በተመሳሳይ በኢኮኖሚ የላሸቁና ዜጎቻቸውን መመገብ ያቃታቸው አገራትም ለበለጸጉት አገራት የሰብዓዊ ድጋፍ በራቸውን ወለል አድርገው ማንነትና ክብራቸውን ሲያስረግጡ ይታያል።

እንደ ኢትዮጵያ አይነት አገራት፣ እንደ ኢትዮጵያውያን አይነት ሕዝቦች ደግሞ ይሄንን ተጻራሪ እውነት ተሸክሞ መሄድን አሜን ብለው ባለመቀበል ለሰላማቸውም፣ ለልማታቸውም እውን መሆን ደፋ ቀና ሲሉ ይስተዋላል። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ከጥንት እስከዛሬ ሰላሟን በራሷ አቅም አስጠብቃ የኖረች፤ በኢኮኖሚዋም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ እጅ ሰጥታ በለጋሾች እጅ ላይ ወድቃ እንዳሻቸው ሊያሾሯት ያልቻለች አገር ናት። ምንም እንኳን ምሉዕ ነው ባይባልም ሕዝቦቿም ቢሆኑ ስለ ሰላማቸው ሲዋደቁ፤ ስለ ልማትና ብልጽግናቸው ሲታትሩ የሚታዩ ናቸው።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ሰላም መሆን እና በኢኮኖሚዋ ከፍ ማለት እረፍት የሚነሳቸው የውጪ ጠላቶች እና የውስጥ ተላላኪ አሸባሪ ባንዳዎች ተቀናጅተው፤ የተረጋጋ ሰላም እንዳይኖራት ዘወትር ጦር አንግተው በመውጋት፣ የልማቷን መሰረት ጡብ ስታኖር ተከታትለው ለማክሰም ሲሯሯጡ ይታያሉ።

በዚህ ረገድ አሸባሪው ሕወሓትና ጀሌዎቹ ከውጪ ጋላቢዎቻቸው ጋር የሚፈጽሙት ደባ ዓብይ ማሳያ ነው። ምክንያቱም ይህ ቡድን ግማሽ ምዕተ ዓመት ለሚሆን ጊዜ ኢትዮጵያን ሲወጋም፤ ሃብት ንብረቷንም ሲዘርፍና ሲያወድም የኖረ፤ አሁንም በዚሁ እኩይ ተግባሩ ያለ ነውና።




በተለይ ከ2010ሩ ሃገራዊ ለውጥ ማግስት ይሄ እኩይ ተግባሩ አደባባይ ወጥቶ አገር ወደለየለት ጦርነት እንድትገባ አድርጓል። ኢኮኖሚዋንም በእጅጉ እንዲላሽቅ የሚችለውን ሁሉ አድርጓል። ሆኖም ይህ የሕወሓት እኩይ ተግባር ኢትዮጵያ ፈረሰች ሲሏት የምትጸና፤ ደኸየች ሲሏት የምትበለጽግ ስለሆነች፤ ኢትዮጵያውያንም ተበተኑ ሲሏቸው የሚሰባሰቡ፤ ተጎሳቆሉ ሲባል ተባብረው ችግርን መሻገርና ልማትን ማፋጠን የሚያውቁ፤ መንግስትም ሰላሙን እያሰፈነ ልማቱን ማስኬድን የተካነ መሆናቸውን በተመሳሳይ ወቅት እንዲገልጡ አደረገ።

እናም ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን በአንድ በኩል ሕልውናቸውን ሲያረጋግጡ፤ በሌላ በኩል የችግሮቻቸው ሁሉ ምንጭ የሆነውን ድህነት ለመርታት የሚያስችላቸውን ልማት በሁሉም መስክ ማቀላጠፉን ተያያዙት። በዚህ ረገድ "ኢትዮጵያ ታምርት" ብለው በኢንዱስትሪውም፣ በግብርናውም፣... መስኮች ማምረት ጀመሩ። ጅምራቸውም በውጤት ታጅቦ ስንዴን ከውጪ መለመን የሚያቋሙበት ጊዜ ቅርብ መሆኑን ማሳየት ቻሉ።

በአፍሪካ ሕብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ እና የቀድሞው የናይጄሪያ ፕሬዚዳንት ኦሊሴጉን ኦባሳንጆ ሰሞኑን በኢትዮጵያ እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሥራዎች በተለይም በባሌ እየተካሄደ ያለውን የሰብል ልማት በጎበኙበት ወቅት "ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ እያከናወነች የሚገኘው ተግባር ለአፍሪካ አገራት ተሞክሮ መሆን የሚችል ነው። ዓለም ስለ ኢትዮጵያ ያለው አረዳድና ትርክት ሊቀየር ይገባዋልም" ሲሉ ይሄንኑ ሃቅ አስረድተዋል። ከዚህም በተጨማሪ የአፍሪካ አገራት ለግብርናው ዘርፍ ትኩረት ሰጥተው ከሰሩ የምግብ ዋስትናቸውን ከማረጋገጥ ባሻገር ምርታቸውን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ኢኮኖሚያቸውን ሊያሻሽሉ እንደሚችሉም ነበር ያስረዱት።

ኦባሳንጆ ይሄን ያሉት፣ ኢትዮጵያ እያከናወነች ያለውን የሰላምም የልማትም ጥረት በአካል ተገኝተው ስላዩ ብቻ ሳይሆን፤ ጥረትና ውጤቱን አሰናስለው እውነቱን ለመረዳት ስለቻሉ ነው። ይሁን እንጂ ዛሬም ኢትዮጵያ ሰላም መሆኗ፣ በልማት ጎዳና ላይ መራመዷ የማይዋጥላቸው አገራትና ተቋማት ስለ ኢትዮጵያ ሰላም ማውራት፣ ስለ ልማቷም ጉዞ መመስከር ከሞት በላይ ሞት ሆኖባቸው ይታያል። ከሰላሟ ይልቅ ስለ ኹከትዋና ጦርነት አታሞ መደለቅ፤ ከልማቷ ይልቅ ስለ ረሃብና ጉስቅልናዋ መተረክ ይቀናቸዋል። ይህ የተዛባ ትርክታቸውና ምኞታቸው ምንም እንኳን ኢትዮጵያውያንን ከሰላም ጥረታቸው፣ ከልማት ግስጋሴያቸው የሚገታቸው ባይሆንም፤ ኢትዮጵያ እንደ አገር ለሰላሟም፣ ለልማቷ የምታደርገውን ጥረት በልኩ ተገንዝቦ እውቅና መስጠት ከሁሉም የሚጠበቅ ሰብዓዊ እሴት ነውና ይሄን ማድረጉ ተገቢ ይሆናል!

---

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# በስክነት እና በምክኒያታዊነት ወደ መፍትሄ

ተገኝ ብሩ

ምክንያታዊነት እውነትን ከሀሰት፤ ትክክለኛው ከተሳሳተው መለየት የሚያስችል የአስተሳሰብ አድማስ ነው። በዚህ አስተሳሰብ ከተመራን እያንዳንዱን ጉዳይ የምንመረምረው ምክንያታዊ ና ሚዛናዊ በሆነ አስተሳሰብ ማእቀፍ ውስጥ ሆነን ነው። ፍትሀዊነት መላበስና ከግልብነት መራቅ መነሻው በትክክለኛ አመክንዮ ማመን ነው።

ፍትሀዊነት ላይ ከቆምን አተያያችን የተቃናና ሚዛኑን የጠበቀ ስለሚሆን ጉዳዮች የምናይበት መነፅር የጎደፈ አይሆንም። የእይታ መነፅራችን የፀዳና እውነትን አጥርቶ የሚያሳይ ስለሚሆን ተግባራችን ከስህተት የጠራ ውጤቱም ከውድቀት የራቀ ይሆናል።

በምክንያታዊ አስተሳሰብ ውስጥ እያንዳንዱ ጉዳይ የሚታየው በስክነት ነው። ጉዳይ ከመነሻው እስከ ውጤቱ ተለይቶ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን በተለያየ አተያይ ይመረመራል። በምክንያታዊነት ውስጥ ስሌት የገዘፈ ስፍራውን ይይዛል። ወደዚህ መድረክ የመጡ ጉዳዮች ሁሉ የሚመረመሩት በሰከነ መንፈስና በሰላ አስተሳሰብ ነው። ለምን? የሚል መነሾ ከፊት ስለሚቀድም በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ተግባር የሚያመጣ ውጤት ድርጊት የሚያስከትለው ግኝት ቀድሞ ይገመታል፤ ይመረመራልም።

ስለሆነም በምክንያታዊ አስተሳሰብና ተግባር ውስጥ የተሳሳተ ውጤት ቦታ አይኖረውም። ምክንያቱም ቀድሞ ስለ ጉዳዩ ምንነት በእርጋታ ይመረመራል፣ ስለ ተግባሩ መነሻ ይጠናል። እያንዳንዱ ጉዳይ በቂ የሆነ መነሻና መድረሻ ይኖረዋል። ምክንያታዊ መሆን የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። ከስሜት መራቅና ጉዳዮች በስሌት መመልከት የሚገባን ከውድቀትና ከጥፋት እራሳችንን ለመጠበቅ ነው።

በምክንያታዊነት የተመራ ትውልድ በአስተሳሰቡ ሚዛናዊ የሆነ ማህበረሰብ ይፈጥራል። ለዚህ ማህበረሰብ አገራዊ ለውጥና ሁለንተናዊ ከፍታ ላይ መድረስ እጅጉን ይቀለዋል። መግባባትና አንድነቱ ይጠነክራል። እዚህ ጋር በስክነት የሚከወን ስሌት ስላለ ተግባር ብዙን ጊዜ ባማረ ውጤት የታጀበ ድል ያስገኛል።

በአንፃሩ ደግሞ ምክንያት አልባነት ከዚህ የተለየ ውጤት ላይ ያደርሳል። እዚህ ላይ ስሜት እንጂ ስሌት ዋንኛ መሰረት ስለሌለው መድረሻው ጥፋት ውጤቱ ያልታሰበ ይሆናል። በዚህ አስተሳሰብና ተግባር የሚገኘው ውጤት ቀድሞውኑ ያልታሰበበት ስለሚሆን አሉታዊነቱ እሙን ነው። ምክንያት አልባነት የሚያስመለክተው ስሜትን እንጂ እውነት አይደለም። ስሜት ደግሞ በደመነፍስ መነዳት እንጂ በጥበብ አንድም እርምጃ አያራምድም። ለዚህም ነው፤ ምክንያት አልባ ትውልድ ዘመኑን በራሱ የሚበላው።

ምክንያት አልባነት ግልብነት ነውና ውጤቱ አክሳሪ ነው። ላለመግባባትና ግጭት ዋንኛ መንስኤ በመሆኑ ለአብሮነት ትልቁ መሰናክል ይፈጥራል። ከምክንያታዊ አስተሳሰብ መራቅ በትውልድ ዑደት ውስጥ በሚፈጥረው አሉታዊ ተፅዕኖ ምክንያት ችግሮች ይደራረባሉ። ትውልዱ ጥያቄና ተግባሩ የሚጣረስ ፍላጎትና ማሳኪያ መንገዱ የተቃረነ ይሆናል።

በምክንያት የተመራ ጉዳዮችን አመዛዝኖ የሚያይ ትውልድ ከስህተት የራቀና ከውድመት የተረፈ ይሆናል። ምክንያቱም እዚህ ጋር ስሌት ከስሜት ይልቅ ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል። የሚያደርገውና የሚከውነው ሁሉ ከስሜት በራቀ መልኩ በስክነት አስልቶ ነውና። እያንዳንዱ ሀሳብና ተግባራቱ በስክነት የተሞሉ ይሆናሉ። እዚህ ስክነት ላይ ተቁሞ የነገሮችን ሁሉ መፍትሄ ማሰብ ብሎም መተግበር ይቀላል። በዚህ ውስጥ አገር ትረጋለች በዚህ ውስጥ ለውጥና እድገት ይቀላል።

አገራችን በዘርፈ ብዙ ትግል ውስጥ መሆንዋ ለሁላችን ግልፅና ልንሸፋፍነው የማንችለው ሀቅ ነው። ያሉብንን ማህበራዊና ፖለካዊ ችግሮች መፍቻ ቁልፉ ደግሞ እኛው እጅ ላይ ነው። ይህ በሰከነ መልኩ ለመግባባት እራሳችንን ዝግጁ ማድረግ። ይህንን የሁለንተናዊ ችግራችን መፍትሄ የሆነን ቁልፍ በትክክል መጠቀም ደግሞ የእኛው ፋንታ ነው። ለችግራችን መፍትሄ የሚሆኑ ጉዳዮችን በስክነት መለየት ብሎም መተግበር ይገባናል።

ትልቅ አገርና ብዝሀነት መለያው የሆነ ማህበረሰብ ውስጥ የሀሳብ ልዩነት መኖሩን ሀቅ ነው። በሀሳብ ልዩነት ምክንያት የሚቀርቡ ጉዳዮችን በምክንያታዊ አስተሳሰብ ላይ ቆሞ መመርመር ይገባል። የራስን ሀሳብ ከሌላው ጋር ማስታረቅና ሰጥቶ በመቀበል መርህ መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልጋል።

እንኳን አገራዊ ጉዳይ ግለሰባዊ ጉዳይ በስሜት ከተመራ አቅጣጫውን ይስታል። ለጋራ መፍትሄ ስክነት ለተግባቦት መደማመጥ ያሻል። እያንዳንዳችን አገራዊ አንድነት ተጠናክሮ ለሁላችንም ምቹ የሆነችና በእያንዳንዳችን ላይ የሚታይ ለውጥ መጎናፀፍ እንፈልጋለን። ለዚህ መፍትሄው ደግሞ የጋራ ለውጥ ላይ መረባረብ አገራዊ እድገት ላይ በአንድነት መስራት ቀዳሚ ተግባር ነው። አንድ ሆኖ ወደፊት ለመራመድ ደግሞ አንድነትን የሚያጠነክሩ መለያየትን የሚያርቁ ጉዳዮች ቀድሞ መፍታት ያስፈልጋል።

ያለችን አንድ አገር ናት። ህልውናዋን አንድ ሆኖ ማስጠበቅ ደግሞ የእኛ የዜጎች ግዴታ ነው። ኢትዮጵያችን ለሁላችንም የምትበቃ በጋራ መቆም አንድነታችን ማጠንከር ካወቅንበት ከራሳችን አልፋ ለሌላው የምትተርፍ ኃያል አገር ናት። በእስዋ ውስጥ አብረን በጋራ ተሳስረን መኖር ግድ ይለናል። አገራችን ለልጆችዋ ምቹ በእድገት ወደፊት የተራመደች፣ በፅኑ መሰረት ላይ የፀና ኢኮኖሚያዊ እድገት ያረጋገጠችና ዲሞክራሲና ፍትህ የነገሰባት ትሆን ዘንድ የአመለካከት ለውጥ መላበስ ይኖርብናል። ይህ የአመለካከት ለውጥ ደግሞ የተሻለች አገር ለመፍጠር ያስችላል።

በአገር ደረጃ ይካሄዳል ተብሎ እየተሰራበት ያለው አገራዊ ውይይት ፍሬያማ ይሆን ዘንድ መስራት ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል። ውይይቱ መግባባት ላይ ያደርሰን ዘንድ እንደ ዜጋ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቀው ቀና እሳቤና አገራዊ የተቆርቋሪነት ስሜት መላበስ ነው። ለውይይት ስነቀርብ ምክንያታዊ አስተሳሰብ ተላብሰን ፍትህና አንድነት የጋራ አጀንዳችን አድርገን አገራዊ ለውጥን በመናፈቅ ሊሆን ይገባል።

ከስሜት በራቀ መልኩ በምክንያታዊነት መመራት ለመፍትሄ ያቃርባል። ለመግባባት ከራስ ባለፈ ወገኔ ከግል ጥቅም ባየለ አገሬን ማለት ይኖርብናል። ከሁላችን በላይ ቀድማ መቆም ያለባት ኢትዮጵያ ናትና የእኛ እሳቤና አመለካከት በእርስዋ ውስጥ በተንሰላሰለ መልኩ የሚተገበር ከሌላው ጋር መግባባትና መተሳሰር የሚያስችል መሆን ይኖርበታል። የእኛን ለሌላው መስጠት እንደምንፈልገው ሁሉ መቀበል፤ እንዲከበር እንደምንፈልገው ሁሉ የሌላን እሴትና አመለካከት ማክበርና አብሮነትን ማፅናት ይገባናል፡፡

እንደ አገር ወዳድ ዜጋ አገራዊ አንድነት ማፅናትና ፍትሀዊ የሆነ አስተሳሰብ መላበስ የእኛ መቆሚያ ሊሆን ይገባል። የምንጠይቀውን በትክክል ማወቅ የተሰጠንን አገራዊ ኃላፊነት በአግባቡ መወጣትና አገራዊ መግባባቱን ውጤት ላይ ለማድረስ ምክንያታዊ አስተሳሰብ መላበስ ለመልካም ውጤት እንደሚያቀርብ መረዳት ያሻል። በአገራዊ መግባባት ውስጥ የሚገኙ መልካም ፍሬዎች መቋደስ እንድንችል የሚያግባቡን ጉዳዮች ላይ ጠንክረን መስራት፤ በሀሳብ የሚያለያዩን ደግሞ በጥበብ መፍታት ቀዳሚው የቤት ስራችን ነው። ይህ ስራችን ደግሞ የህዝባችን አንድነት የሚያጠነክር የአገራችን ህልውና የሚያስጠብቅና ሰላማችን የሚያረጋግጥ በጥበብ የተመራ ይሁን። አበቃሁ፤ ቸር ይሰማን።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የህይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ኑሮ - ከቤተመንግስት እስከ ጎዳና

መልካምሥራ አፈወርቅ

### የወልዲያው ጉብል

የጁ- ‹‹የእግዜር መሀል እጁ›› ከሚባልበት መሀል ወልዲያ ተወልደው አድገዋል። በእሳቸው ዘመን ‹‹ህይወት እንዳሁኑ አልከበደም። ‹‹ቀላልና መልካም ነበር›› ይላሉ። አቶ ዮሀንስ ሀይሉ። የዛኔ ያሻቸውን አላጡም። የፈለጉት ጉዳይ ከእጃቸው የራቀ አልነበረም።

የወልዲያው ዮሀንስ ልጅነታቸውን በየጁና አካባቢው በደስታ ቦርቀውበታል። ዕድያሜቸው ከፍ ማለት ሲጀምር ደግሞ ከትውልድ አገራቸው የጁ መራቅ ፈለጉ። በወቅቱ እሳቸውን መሰል እኩዮቻቸው ከከተማ ዘልቀው ህይወታቸውን እንደሚቀይሩ ያውቁ ነበር። እናም ዮሀንስ የእነሱን መንገድ ሊከተሉ አማራቸው። ያሰቡት አልቀረም። አንድ ቀን ጓዛቸውን ሸክፈው ተነሱ።

ወቅቱ የአጼ ኃይለሥላሴ ዘመን ነበር። በንጉሱ ጊዜ እንደአሁኑ ከተማ አልሰፋም፣ ህዝብ አልበዛም። የእሳቸው ዘመዶች በአዲስ አበባ ይኖራሉ። አክስቶቻቸው እንግዳውን ጉብል ለመቀበል ፊታቸውን አያዞሩም። ይህን አሳምረው የሚያውቁት አፍላው ዮሀንስ በእርግጠኝነት ጉዞ ጀመሩ። የጁ ወልዲያን ተሰናብተው፣ ደሴ ኮምቦልቻን አልፈው፣ ከሸዋ ምድር ሲደርሱ እግራቸው ከደብረብርሀን አላለፈም። ደብረብርሀን የወታደሮች ካምፕ መኖሩን ሰምተዋል። ‹‹ጠባሴ›› ከተባለው ስፍራ ደርሰው ወደካምፑ አመሩ።

የጦር ካምፑ ሰዎች ወጣቱን ዮሀንስ አልገፏቸውም። በበጎ ተቀብለው ለእሳቸው የሚሆን ስራ ሰጧቸው። ልጅነት ከፍላጎት ተዳምሮ ጥረታቸው ሲጎላ የጦር ካምፑ ቋሚ ተቀጣሪ ሆኑ። በየወሩም ደሞዝ ይከፈላቸው ያዘ።

ዮሀንስ ‹‹እንጀራዬ›› ብለው በያዙት መተዳደሪያ ራስን ማገዝ አወቁበት። ወጣትነት፣ ከአፍላ ጉልበት ታክሎ የጦር ካምፑ ቆይታ በጥንካሬ ተገፋ። ዓመታት እየጨመሩ፣ ጊዜው መክነፍ፣ መንጎድ ያዘ። እንደዋዛ አስራስምንት የስራ ዓመታት ተቆጠሩ።

### 1953 ዓ.ም አዲስ አበባ

አስራስምንት ዓመታትን በጠባሴ የጦር ካምፕ ያሳለፉት አቶ ዮሀንስ 1953 ዓ.ም ሲጀምር አዲስ አበባ መግባት አማራቸው። አዲስ አበባ ከደብረብርሀን ቅርብ በመሆኑ በመንገድ ብዛት አልደከሙም። በከተማው ደርሰው ነዋሪውን መሰሉ። እንግዳው ጥቂት ቀናት ቆይተው አዲስ ስራ ተገኘላቸው። ዕድላቸው መልካም፣ እግራቸው እርጥብ ሆነ። ያገኙት ስራ ከጃንሆይ ዕልፍኝ፣ ከቤተመንግስቱ አደረሳቸው።

ራስ መስፍን ስለሺ ዮሀንስን ገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ባስገቧቸው ጊዜ ውስጣቸው በደስታ ተሞላ። ለስራ ፈላጊው ቤተመንግስት ይሉት እውነት አዲስ የሚባል ህይወት ነው። እሳቸው ከዚህ ቀድሞ በእንዲህ አይነቱ ልማድ አላለፉም። ስራውን በደስታ ተቀበሉ። ጥቂት ቆዩና ወደእዮቤልዩ ቤተመንግስት ተዛወሩ።


በቤተመንግስቱ እንደሌላው ዘው፣ ስተት ተብሎ አይገባም። ስፍራው የራሱ በሆነ ንጉሳዊ ስርዓት ይመራል። በውስጡ የሚመላለሱ እንግዶች ተራ የሚባሉ አይደሉም። ገቢ ወጪው ሁሉ ለንጉሱና ቤተሰቦቻቸው፣ ለባለሚሎቻው ጭምር ‹‹ ለጥ ›› እያለ እጅ ይነሳል።

ዮሀንስና 1953 ዓ.ም በቤተመንግስት ሲገናኙ ወቅቱ ፈታኝ የሚባል አጋጣሚን ፈጠረ። የንጉሱን ሥርዓት አጥብቀው የሚቃወሙ ኃይሎች መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ ሞከሩ። የታህሳሱ ግርግር የፈጠረው ነውጥ እሳቸውን ጨምሮ ለመላ ኢትዮጵያውን ታላቅ ትኩረት ሳበ። ወንድማማቾቹ ገርማሜና መንግስቱ ንዋይ ለውጥ ሽተው ታሪክ ሊቀይሩ መነሳታቸው ደምቆና ጎልቶ ተሰማ።

ከጊዚያት በኋላ የታህሳሱ ግርግር በመንግስት ኃይሎች መክሸፉ ታወጀ። አገር ተረጋግቶ ህይወት እንደቀድሞው ቀጠለ። በወቅቱ አቶ ዮሀንስ በቤተመንግስቱ በተሰጣቸው የመዝገብ ቤት ስራ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ነበር። የዛኔ በግቢው የሚካሄደው ስርዓት በእጅጉ ይለያል። በዙፋን ችሎት የሚዘጋጀው ግብር በሶስት አይነት ደረጃ የተከፈለ ነው።

በመጀመሪያው ደረጃ የንጉሳውያን ቤተሰቦችና አቻዎቻቸው ሲቀመጡ በሁለተኛውና ሶስተኛው ደረጃ ደግሞ መካከለኞቹና ተከታዮቻቸው ይሰየሙ ነበር። በተመሳሳይም በማዕድ ገበታ ላይ የነበረው ስርዓት በደረጃ የተለየና በወጉ የተወሰነ እንደነበር ያስታውሳሉ።

በወቅቱ ዮሀንስ ከጃንሆይ ዓይን ቢገቡ የተለየ ሞገስ አገኙ። በተሰጣቸው ደረጃ ከገበታው እየታደሙ፣



አቶ ዮሐንስ ሀይሉ፤

ከሚቸራቸው ስጦታ በረከቱን እያገኙ በደስታ ዘለቁ። ጃንሆይ ዮሀንስን ባዩዋቸው ጊዜ የፍቅራቸውን ሊያደርጉላቸው አልሰሰቱም። በፋሪ፣ አጋሮና ጅማ ከተሞች የነበሩ ሰፋፊ ይዞታዎችን በጋሻ መሬት አስለክተው አበርከቱላቸው።

የዛኔ የልጅነት ዕድሜ ታክሎበት ስለነገ መጨነቅን አያውቁትም። ቦታውን ሸጠውና ለውጠው የመጠቀም ሀሳብ አልነበራቸውምና በዕድሉ አልተጠቀሙም። ስጦታዎቻቸውን በምስጋና እየተቀበሉ የቤተመንግስት ህይወታቸውን ቀጠሉ።

### 1966 ዓ.ም የአብዮቱ ፍንዳታ

አሁን በአገረ ኢትዮጵያ ሥር ነቀል ለውጥ አስፈልጓል። ሥርአቱን በሚቃወሙ አብዮታውያን ግፊት መስከረም 2 ቀን 1966 ዓም አብዮቱ ፈነዳ። ድንገቴው የመንግስት ለውጥ የብዙዎችን ህይወት ቀያየረ። ንጉሱ ከዙፋናቸው እንደወረዱ ዮሀንስን መሰል ሰራተኞች ከቤተመንግስቱ ሊለቁ ግድ ሆነ።

ዮሀንስ አሁንም ጎበዝ ጎልማሳ ናቸው። ያሉበት ዕድሜ ሰርቶ ለመግባት፣ ሮጦ ለማደር ብቁ ነው። ከጃንሆይ የተበረከተላቸው ጥቂት የማይባል ጋሻ መሬት እንደተበላ ዕቁብ ሆኗል። ደርግ ‹‹መሬት ለአራሹ›› ሲል ባወጣው አዋጅ የእሳቸውን ጨምሮ የበርካቶች ሀብት ንብረት ተነጥቋል።

እስከዛሬ ከንጉሱ በስጦታ የተበረከተላቸው ጋሻ መሬት ከእጃቸው አልገባም። አሁን ከስም በቀር ያተረፉት የለም። ደግነቱ ለአንገታቸው ማስገቢያ፣ የቀበሌ ቤት አላጡም። ከለውጡ በኋላ ስራ መፈለግ የጀመሩት ዮሀንስ አንድቀን የልባቸውን መሻት ሞላ። አውራ ጎዳና ይባል ከነበረው መስሪያቤት ተቀጠሩና ደሞዝተኛ ሆኑ።

ስራቸው ከበርካቶች ጋር ያገናኛል። የዛኔ ከአንድሺህ አምስት መቶ በላይ ሰራተኞችን ያስተዳድሩና ይመሩ ነበር። ዮሀንስ ረጅሙን ዓመታት በመስሪያቤት አሳለፉ፡ በኃላፊነት የተሰጣቸውን እየከወኑ፣ በታዛዥነት ግዴታቸውን እየተወጡ የስራ ዓለም ቆይታቸውን አጠናቀቁ። ዕድሜያቸው ደርሶ በጡረታ ሲሰናበቱ በውስጣቸው የኖረው የመስራት ፍላጎት አልቀዘቀዘም።

### ከጡረታ ማግስት ...

ገና በአፍላ ዕድሜ ካገራቸው የወጡት ዮሀንስ ዓመታትን በስራ ዓለም ቆይተው በጡረታ ተሰናብተዋል። አሁን ዕድሜያቸው ጨምሯል፡ የቀድሞው መልክና ቁመና ከእሳቸው ጋር አይደለም። እንደቀድሞው ባይሆኑም ለስንፍና እጅ አልሰጡም። ከመስራት ፍላጎት ጋር ኑሮን ሊጋፈጡ ስራ መፈለግ ይዘዋል።

ለጡረታ የሚሰጣቸው ገንዘብ እዚህ ግባ አይባልም። ኑሮ ሲጨምር ህይወት መክበድ ይዟል። ይህ እውነት በዙሪያቸው ያለው ዮሀንስ ገቢያቸውን ከወጪ እያዛመዱ ደጋግመው አሰቡ። ከጎናቸው ማንም የለም። ትዳር ይዘው ቤተሰብ አልመሰረቱም። ጎጆ ቀልሰው ወግ ማዕረግ አላዩም። አንዳንዴ አንዳንድ ሁኔታዎች በዓይናቸው ውል እያሉ ይፈትኗቸዋል። ያም ሆኖ ብቸኝነት ብቻውን አልበገራቸውም።

### ትዳር በማምሻ ዕድሜ ...

ዮሀንስ በጡረታ ተሰናብተው ከቤት ውለዋል። መሮጥ ለማይሠለቻቸው ብርቱ ያለስራ መቀመጡ እያስጨነቃቸው ነው። ይህ አጋጣሚ ግን መልካም ዕድል ያመጣ ይመስላል። ለአዛውንቱ አባት ጎናቸውን የምታሞቅ፣ ቤታቸውን የምታደምቅ ግራኅን ተገኝታለች። ይህ እውነት እስከዛሬ ትዳር ይሉትን ላልሞከሩት ሰው ታላቅ ለውጥ ሆኗል።

በዮሀንስ ህይወት ብቸኝነት ተወግዷል። ከሆቴል መብላት፣ ከውጭ አምሽቶ መግባት በነበር ተረስቷል። አሁን በቤት ያለችው ወይዘሮ ስለ ጓዳዋ ታስባለች፣ ስለባሏ ትጨነቃለች። ጥንዶቹ የዕድሜ አቻዎች አይደሉም። ያም ሆኖ ተሳስበው፣ ተከባብረው ይኖራሉ። አሁን ለዓመታት ተዘግቶ የኖረው ቤት ወግ ደርሶታል። እንደሌሎች በር ተከፍቶ ይውላል። ዝምታ የዋጠው ጎጆ ቤተዘመድ ይጎበኘዋል፣ ወዳጅ ጎረቤት ያየዋል።

በዮሀንስ ኑሮ አዲስ ምዕራፍ እየተጀመረ ነው። ጡረተኛው አባወራ የማምሻ ዕድሜያቸው ሌላ በረከት አስከትሏል። ህይወታቸው በልጅ ስጦታ ታድሷል። የትዳራቸው ፍሬ፣ ወንድ ልጅ አሳቅፏቸዋል። አዛውንቱ አባት ኑሮን እንደ አዲስ ይመሩት ያጣጣሙት ይዘዋል።

ዓመታትን የዘለቀው ትዳር በልጅ በረከት ሲታደስ የኑሮ ትርጉሙ ተለየ። ዮሀንስ ስለልጃቸው ያስቡ ይጨነቁ ያዙ። አሁን ሌላ ነፍስ ቤታቸውን ተቀላቅሏል። ለጨቅላውና ለጎጇቸው ተጨማሪ ገቢ ያሻል። በእርግጥ ጥቂት የጡረታ አበል ከኪሳቸው ይደርሳል። ይህ ብቻ ግን በቂ አይሆንም። ይህን ያወቁት አዛውንት በዝምታ አልተቀመጡም። ለባለጉዳዮች ጉዳይ ማስፈጸም ጀምረዋል።

ጥቂት ቆየና የባለቤታቸው ጤና አሳሳቢ ሆነ። የጨቅላው እናት ሆስፒታል መመላስ ያዙ። እያደር ሰላም የነሳቸው ህመም ከአልጋ ማዋል ጀመረ። ከሰሞኑ የሆነው ግን ከሌላው ቀን ተለየ። ወይዘሮዋ በእጅጉ ታመዋል፡ ሁኔታቸው አስጊ እየሆነ ነው። ብዙዎች ስለሳቸው ያስባሉ፣ ይጨነቃሉ። የተፈራው አልቀረም። የአቶ ዮሀንስ ባለቤት በህይወት ወደቤታቸው አልተመለሱም። ጨቅላ ልጃቸውን ትተው፤ ቤት ትዳራቸውን አራግፈው እስከወዲያኛው አሸለቡ፤

### ህይወት በሌላ ገጽ

ዛሬ እንደትናንቱ አልሆነም። ህይወት በሌላ መልክ ተቀይሯል። የጎጆው ድባብ ዝምታ ውጦታል። የአዛውንቱን ትዳር ሞት ፈቶታል። አባወራው የማምሻው ዓለማቸው እንደጅማሬው አልሰመረም። አሁን በቤቱ የወይዘሮዋ ድምጽ የለም። የትንሹ ልጅ ሳቅና ለቅሶ አይሰማም። ዮሀንስ ግራ ገብቷቸዋል። አንድዬ ልጃቸው ከአያቱ እጅ ገብቷል። ብቸኝነት፣ ሀዘንና ብሶት ከቧቸዋል።

ህይወት እየከበደ፣ ኑሮ እያሻቀበ ነው። ትልቁ ሰው ከሆቴል መብላት ጀምረዋል። ውለው ሲገቡ በፈገግታ የሚቀበላቸው የለም። ድምጻቸው ቢጠፋ፣ በወጡበት ቢቀሩ አስታዋሽ የላቸውም። በየቀኑ የባለጉዳዮችን ዶሴ ይዘው ይወጣሉ። ለሰሩበት ጥቂት ይከፈላቸዋል። የሚያገኙትን ገንዘብ በዕለት ይጎርሱበታል። ሲነጋ ለሌላ ስራ ዓይናቸው ይማትራል። ካገኙ ለኪሳቸው አያጡም።

ከሀምሳ አራት ዓመት በላይ የኖሩበት የአራት ኪሎ ሰፈር ለልማት ተፈልጎ መነሳት ጀምሯል። የዮሀንስ የቀበሌ ቤት ከመፍረስ አልዳነም። እሳቸውም እንደሌሎቹ ምትክ ቤት አግኝተው ከስፍራው ለቀዋል። ይህ መሆኑ አዛውንቱን አላስጨነቀም። የግለሰብ ቤት ተከራይተዋል። የተጠየቁትን ክፍያ አሟልተው የጋራ ቤቱን ተረክበዋል።

### እርጅና ብቻህን « ና »

ህይወት በብቸኝነት ቀጥሏል። ዮሀንስ እንደቀድሞው አይደሉም። ዕድሜያቸው ገፍቷል። አካላቸው ደክሟል። እያሰለሰ የሚያስታውሳቸው ሕመም ጤና እየነሳቸው ነው። በአንድ ወቅት ያጋጠማቸው የመኪና አደጋ ጉዳት ቀን ቆጥሮ ይሰማቸው ይዟል። በህክምና ስህተት ‹‹ጠፍቷል›› የሚሉት አንድ ዓይናቸው ታሟል። ሲራመዱ በዝግታ ነው። አካባቢውን ከለቀቁ ወዲህ የሞካከሩት የቤት ኪራይ ምቾት የለውም።

ቦሌ ቡልቡላ የተሰጣቸውን ቤት አልፎ አልፎ ያዩታል። ቤቱ ቢከራይ ገቢው ይጦራቸዋል። ቢቆይ ደግሞ ለልጃቸው ይሆናል። ልጁ አሁንም አያቶቹ ዘንድ እየኖረ ይማራል። ከእሳቸው አንዳች አይፈልግም። ዮሀንስ ዛሬም ከህይወት ግብግብ ይዘዋል። ዕድሜቸው ቢገፋም፣ እጅ መስጠት አይሹም። መቀመጥ ይሉትን አይወዱም። ቢደክማቸውም ይዞራሉ። ባይሰሩም ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል። ለመኖር መብላት አለባቸው።

### ያመኑት ፈረሰ...

አሁን መውጣት መውረዱ አዝሏቸዋል። በተሰጣቸው ቤት ባይኖሩም መጠቀም እንዳለባቸው ያምናሉ። በቤቱ ጉዳይ የልባቸውን እንዳይደርስ ዕድሜቸው ፈተና ሆኗል። እንዲያም ቢሆን መፍትሄ አላጡም። ለውጣውረዱ ወኪል ቢኖራቸው የሀሳባቸው ይሞላል። ዮሀንስ አውጥተው አውርደው ከአንድ ሰው ደረሱ። ለውክልና ያሰቧት የቅርብ ጓደኛቸውን ልጅ ሆነ። ይህች ሴት እንደሳቸው ሆና የሀሳባቸውን ትከውናለች። በቤቱ በሚኖረው ጉዳይ ሁሉ ውክልናውን ትወስዳለች።

አቶ ዮሀንስ በሙሉ አመኔታ በእጃቸው ያለውን ዶሴ ለተወካያቸው አስረከቡ፡፤ ወኪሏ ለቤቱ እንደሳቸው ልትሆን ቃል ገብታ ኃላፊነቱን ወሰደች። ጊዚያት ተቆጠሩ። ዮሀንስ፡ አሁን ስለ ቤቱ ማሰብ ትተዋል። ለዕለት ጉርሳቸው አላጡም። ለኪሳቸው የሚተርፍ ጥቂት ገንዘብ ከእጃቸው ይገባል።

አንድ ቀን ዮሀንስ ድንገት ለጆሯቸው የደረሰውን እውነት ማመን ተሳናቸው፡፤ የሚሰሙት ሁሉ ሀሰት ቢመስላቸው በርካቶችን ደጋግመው ጠየቁ። የሁሉም ምላሽ አንድ ሆነ። የባልንጀራቸው ልጅ፣ በዕምነት የሰጧትን ቤት በውክልናዋ ተጠቅማ ሸጣዋለች። የሰሙትን ባለማመን ያመኗትን ሴት በፍለጋ አሰሱ። አላገኟዋትም።

እንደዋዘ ከእጃቸው የተነጠቀውን ሀብታቸውን እያሰቡ በትካዜ አንገት ደፉ። ውስጣቸው አረረ፣ ሀዘናቸው ከፋ። በእጃቸው የቀረ አንዳች ሰነድ ያለመኖሩን አሰቡ። ሁሉንም በህጋዊ ውክልና በህገወጥ ሂደት ተዘርፈዋል። ዕድሜቻቸውን አሰቡት። ሸምግለዋል። ለሩጫ የሚተርፍ፣ ለሙግት የሚበረታ ጉልበት ከእሳቸው የለም። ተወካያቸውን አጥብቀው ፈለጓት፣ አስፈለጓት። የግል ቤቷን ሸጣ ከአካባቢው መራቋ ተነገራቸው። ቆይተው የእሳቸው ኮንዶሚኒየም ከተለያዩ ሰዎች አርፎ ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ ስለመሸጡ አወቁ። አንዳች ማድረግ አልቻሉም። ከእንግዲህ ጥርስ የሌለው አንበሳ ሆነዋል።

### ኑሮን በእንክርት...

ዛሬ አቶ ዮሀንስ ኑሮ በእጅጉ ከብዷቸዋል። ከጎናቸው ወዳጅ ዘመድ የለም። በእጃቸው ጥሪት አልተረፈም። ከእንግዲህ ተከራይተው መኖር አይችሉም። ከሆነላቸው በቀን አንዴ ይጎርሳሉ። ሁሌም በአንድ አይነት ልብስ ይታያሉ። ጥቁር ካፖርታቸው የሩቅ መለያቸው ነው።

ዛሬ ላይ ቆመው ትናንትን ያስባሉ። ቀድሞ በሳንቲም የሚመገቡበት ቤት አሁን በመቶብሮች ይጠየቃል። መኖሪያ ማደሪያ የላቸውም። ለነፍስ ያሉ በሚቸሯቸው ገንዘብ ከቤርጎ አድረው ጎናቸውን ያሳርፋሉ። አንዳንዴ ከአውቶቡስ ፌርማታ ለማደር ጋደም ይላሉ። ትናንት የሚያውቋቸው አንዳንዶች ስለሳቸው ግድ ባላቸው ጊዜ ከእነሱ ጥግ እንዲያድሩ ይፈቅዱላቸዋል። ቆፍጣናው ዮሀንስ እጅን ለልመና መዘርጋት ሞታቸው ነው። ገንዘብ ሲሰጧቸው ይበሳጫሉ፣ ቁጣ ቁጣ ይላቸዋል።

### ክረምቱ ደረሰ - ቤት ያላችሁ ግቡ

ሽማግሌው ኑሮ በእጅጉ ከብዷቸዋል። አንድዬ ልጃቸው ኮሌጅ ተምሮ መመረቁን ያውቃሉ። ስራ ባለመያዙ ለችግራቸው አልደረሰም። አሁን ሰኔ ግም ሊል ክረምቱ ሊመጣ ነው። ቤት የለሹ ዮሀንስ ዝናቡ፣ ብርዱ ያሳስባቸዋል። ነገ የሚሆነውን አያውቁም። የዕድሜ ጫና፣ የሰዎች ክፋትና ያለባቸው ችግር ከጎዳና ሊገፈትራቸው አሰፍስፏል።

አሁን ዮሀንስ ተመልካች ዓይኖችን ይሻሉ። በቀን አንዴ ብቻ ለሚጠቀሙት እህልውሀ፣ ለሚያድሩበት ቤርጎ ይከፍሉት የላቸውም። ጎዳና እየወጡ ነው። አጥተዋል፣ ነጥተዋል። እንዲህ ለመኖር ለሚውተረተሩት አዛውንት እጃችችን ይረባረቡ። ‹‹አለንዎ›› እንበላቸው። የአገር ባለውለታ ናቸውና።

# ስፖርት



# አዲስ አበባ የፈካችበት የኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክ

**ቦጋለ አበበ**

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክ በሐዋሳ መካሄድ ከጀመረ ዛሬ ሰባተኛ ቀኑን አስቆጥሯል። በተለያዩ የውድድር ቦታዎች የሚካሄዱ በርካታ የስፖርት አይነቶች በጠንካራ ፉክክር ታጅበው የቀጠሉ ሲሆን ብዙዎቹ ፍጻሜ እያገኙም ነው። በውድድሩ አንድ ሳምንት ቆይታ ከመጀመሪያው ቀን አንስቶ የፍጻሜ ፉክክር በተደረገባቸው ውድድሮች ተሳታፊ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ሜዳሊያዎችን ለመሰብሰብ የሚያደርጉት ፉክክር ተጠባቂ ነው። ከዚህ ቀደም በሚካሄዱ የተለያዩ አገር አቀፍ ውድድሮች የበርካታ ስፖርተኞች መቀመጫ የሆነችው አዲስ አበባ ከተማ ከተፎካካሪነት ባሻገር በውጤታማነት ጎልታ ስትወጣ አለመታየቷ በብዙዎች ዘንድ ጥያቄ ያስነሳ እንደነበር ይታወቃል። ይህ የመጀመሪያ ወጣቶች ኦሊምፒክ ውድድሩ ገና አንድ ሳምንት በሚቀረው በዚህ ወቅት በርካታ ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ አጠቃላይ አሸናፊ የሚሆነውን መገመት ቢከብድም ባለፈው አንድ ሳምንት በተካሄዱ የተለያዩ የፍጻሜ ፉክክሮች አዲስ አበባ ከተማ ከወትሮው ጎልታ የታየችበትን ውጤት እያስመዘገበች ትገኛለች። በቀሪው አንድ ሳምንት በዚሁ ውጤታማነት ከቀጠለችም አጠቃላይ አሸናፊ የምትሆንበት እድል መኖሩን እስካሁን የሰበሰበችው በርካታ ሜዳሊያ ፍንጭ ይሰጣል።

ከትናንት በስቲያ ከተጠናቀቁ ውድድሮች ስንጀምር በ3ለ3 የግማሽ ሜዳ ቅርጫት ኳስ ውድድር በሴቶች አዲስ አበባ የወርቅ ሜዳልያ አሸናፊ ስትሆን ደቡብና ሲዳማ ክልሎች የብርና የነሐስ ሜዳሊያውን ወስደዋል። በተመሳሳይ ውድድር በወንዶች ሲዳማ ክልል ወርቁን ሲወስድ አዲስ አበባ የብርና ደቡብ ክልል የነሐስ ሜዳሊያውን የግላቸው አድርገዋል።

አዲስ አበባ የወርቅና የብር ሜዳሊያ የወሰደችበት ሌላኛው ውድድር በአትሌቲክስ 8 መቶ ሜትር ወንዶች ተጠቃሽ ሲሆን የነሐሱን ሜዳሊያ ደቡብ ክልል ወስዷል። በተመሳሳይ በሴቶች ኦሮሚያ ክልል የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ ሲሆን አዲስ አበባና ደቡብ የብርና የነሐስ ሜዳሊያውን ወስደዋል። ከኦሊምፒክ ስፖርቶች ውጪ ፉክክር የተደረገበት የኢንተርናሽናል ቴኳንዶ ውድድር ፍጻሜውን ሲያገኝ አዲስ አበባ የሜዳሊያ ስብስቧን ያደመቀችበት ወርቅ የግሏ አድርጋለች። ሐረሪና ድሬዳዋም በዚህ ውድድር ብርና ነሐስ አጥልቀዋል። በሌላ የአትሌቲክስ 100 ሜትር መሠናክል ውድድር አዲስ አበባ ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ በመውጣት ወርቅ፣ ብርና ነሐስ ያገኘችበት ውጤት በጉልህ የሚጠቀስ ነው። በሜዳ ተግባር በሴቶች የርዝመት ዝላይ ወርቅ፣ በሴቶች 400 ሜትር ብር ማስመዝገቧ ይታወቃል። በዲስከስ ውርወራ በሴቶች ወርቅ፣ በወንዶች ሱልስ ዝላይ የነሐስ ሜዳሊያ ከማስመዝገቧ ባሻገር በብስክሌት የቡድን ክሮኖ ሜትር በሴቶች 20 ኪሎ ሜትር በሸፈነና፣ በወንዶች 30 ኪሎ ሜትር በሸፈነ ውድድር በሁለቱም ጾታ ሁለት የወርቅ ሜዳልያ ማስመዝገብ ችላለች። ትናንት የተካሄዱ የፍጻሜ ውድድሮችን ውጤት ሳይጨምር አዲስ አበባ አስራ አንድ የወርቅ ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ አጠቃላይ አሸናፊ ሆና ለማጠናቀቅ በተሻለ መንገድ ላይ እየተጓዘች ትገኛለች።

ተሳታፊዎች በርካታ ሜዳሊያዎችን ለመሰብሰብ ከተዘጋጁባቸው ስፖርቶች መካከል የኦሊምፒክ ስፖርት የሆነው የወርልድ ቴኳንዶ ውድድር ትናንት በሐዋሳ መምህራን ኮሌጅ በይፋ የተጀመረ ሲሆን በውድድሩ አዲስ አበባንና ድሬዳዋን ጨምሮ 8 ክልሎች በአስር የተለያዩ ካታጎሪዎች፣ በወንድና በሴት ከ15 እስከ 18 ዕድሜ ክልል ያሉ መቶ ስፖርተኞች የሚሳተፉበት ይሆናሉ። በሌላኛው



አዲስ አበባ በወጣቶች ኦሊምፒክ በሁለቱም ጾታ ወርቅ ካገኘችባቸው ስፖርቶች መካከል ብስክሌት ቀዳሚው ነው፣

የኦሊምፒክ ስፖርት የቦክስ ውድድር ትናንት ከሰአት ጀምሮ የተለያዩ የፍጻሜ ፍልሚያዎች እየተከናወኑ ይገኛል። አዲስ አበባም በነዚህ ስፖርቶች ተጨማሪ ወርቆችን ለመሰብሰብ ተዘጋጅተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የስፖርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳዊት ትርፉ "የአዲስ አበባ ልዑክ በቆይታው በመልካም ሁኔታ ላይ ይገኛል፣ እስካሁን ያደረግናቸው ውድድሮች በአንፃሩ ጥሩ ቢሆኑም ቀን በቀን በሚካሄዱ ውድድሮችና የሜዳሊያ ፍፃሜዎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መወዳደር ይገባል" በማለት አዲስ አበባ በኦሊምፒኩ እያስመዘገበች ስለሚገኘው ስኬት አስተያየት ሰጥተዋል።

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክ "እውነተኛ ዕድሜ ለኢትዮጵያ ስፖርት ዕድገት" በሚል መሪ ቃል ከኦሊምፒክ ስፖርቶች በአትሌቲክስ፣ እግር ኳስ፣ መረብ ኳስ፣ ቅርጫት ኳስ፣ እጅ ኳስ፣ ብስክሌት፣ ቦክስ፣ ጅምናስቲክና ወርልድ ቴኳንዶ ፉክክሮችን እያስተናገደ ይገኛል። ከኦሊምፒክ ስፖርቶች ውጪም ቼዝ፣ ኢንተርናሽናል ቴኳንዶና ውሹ ስፖርቶች ፉክክር የሚደረግባቸው ሆነዋል።


## የቅጥር ማስታወቂያ

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከዚህ በታች በተገለፀው ክፍት የሥራ መደብ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተፈላጊ ችሎታ መመሪያ መሰረት አመልካቾችን አወዳድሮ በቋሚነት መቅጠር ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም መስፈርቱን የምታሟሉ አመልካቾች የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃችሁን ዋናና የማይመለስ ፎቶ ኮፒውን በመያዝ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ ዋናው መ/ቤት የሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 206 በመቅረብ ማመልከት የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

| ተ.ቁ. | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የሥራ ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | የትምህርት አይነት | የሥራ ልምዱ ለማግኘት የሚጠይቀው ጊዜ | ልምዱ የሚገኝበት የሥራ ዓይት | ብዛት | ደመወዝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሶሻል ወርክ ባለሙያ II | IX | የመጀመሪያ ዲግሪ | በሳይኮሎጂ ሶሺዮሎጂ፣ ሶሻል ወርክ | 2 ዓመት | ከህጻናት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች በማህበራዊ ጉዳዮች ያለው (ያላት) | 6 | 4609 |

**ማሳሰቢያ**

1. በማስታወቂያው ላይ ከተጠቀሰት የትምህርት ዓይነቶችና የሥራ ልምዶች ውጪ የሚቀርቡ ማስረጃዎች ተቀባይነት የላቸውም፡፡
2. መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ለሚቀርቡ የሥራ ልምድ የመንግስት የሥራ ግብር የተከፈለበት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. የጽሁፍና የቃል ፈተና የሚሰጥበት ጊዜ በውስጥ ማስታወቂያ ይገለጻል፡፡
4.ከተገለጸው መስፈርት በላይ ያላችሁ አመልካቾችም መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡
5. **የስራ ቦታ**- አዲስ አበባ
6. ሴት አመልካቾች ይበረታታሉ፡፡

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር፡**- 0118694478

## የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት



## የአዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ከበደ ሽዋፈራ ወጋየሁ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A77885 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAAKP34H6H7P12304 ሞዴል NPR6SN የሞተር ቁጥር 4HG1*673109 የሊብሬ ቁጥር 316958 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ24/9/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርከሪ**
**ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ልደታ ቅ/ጽ/ቤት**



የባለንብረት ስም ለይኩን ብርሃኑ ጌጡ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A04570 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር VF7N1RFN173668921 ሞዴል 201-16U የሞተር ቁጥር PSABFN10LH2906763920 የሊብሬ ቁጥር 434973 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ24/9/2014 አመልክተዋል:: የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርከሪ ፈቃድና**
**ቁጥጥር ባለስልጣን አራዳ ቅ/ጽ/ቤት**



የባለንብረት ስም ጌታነህ ጌታቸው አበበ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-8535 የተሽከርካሪው ዓይነት ሞተር ብስክሌት የሻንሲ ቁጥር MD625DF44F1N62894 ሞዴል TVS VICTOR GLX የሞተር ቁጥር AF4NF1022043 የሊብሬ ቁጥር 251825 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ /ሊብሬ/ የጠፋባቸው መሆኑን ገልጸው ተለዋጭ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ሊብሬ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል ፡፡ይህንን /ሊብሬ የባለቤትነት ደብተር/ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለፅ/ቤቱ ሪፖርት እንድታደርጉ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርከሪ**
**ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የየካ ቅ/ጽ/ቤት**



በከሣሽ ሕብረት ኢንሹራንስ አ/ማ እና በተከሣሽ ወ/ሮ ሙሉአለም ኢቲቻ ተጠሪ ጣልቃ ገቦች 1. አቶ እንድሪያስ ኩሣ 2. አቶ አብርሃም ወርቁ መካከል ስላለው የፍ/ብሄር ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች መከሰሳቸውን አውቀው የክስ ማስረጃዎችን ከሬጅስትራር ጽ/ቤት በመውሰድ መልሳቸውን አዘጋጅተው ለ16/10/2014 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት ሬጅስትራር ቢ.ቁ. 13 በኩል መልስዎን ከመዝገብ ጋር እንዲያያይዙ በተጨማሪም ክስ ለመስማት ለ23/10/2014 ዓ.ም. በ4፡30 ሰዓት የተቀጠረ መሆኑን አውቃችሁ በፌ/ከ/ፍ/ቤት 8ኛ ንግድ ችሎት ፎቅ ቁጥር 1ኛ ቢሮ ቁጥር 104 እንድትቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳያችሁ በሌላችሁበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት**